ተሠሐዲ

እና

ሸርሐ

ዝግጅት

ሳዱት ከማል

የመጅመሪያ እትም

1438 ዓ. ሂ. / 2009 በኢትዮጵያ አቆጣጠር

ምስጋና

ከሁሉም በፊት አስቀድሜ ለእስልምና እና ለሱና የመራኝን ከአፈጣጠሬ ጀምሮ ውለታው ያልተለየኝን ከፍጡራኑ ሁሉ በላይ ከአርሽ በላይ ያለውን፣ እውቀቱ፣ ማየቱ፣ መስማቱ፣ ፍጡራኑን ሁሉ ያካበበውን ሃያል ብቸኛ ጌታ አንድ አምላክ፣ እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ ለሆነው አላህ የሚገባውን ያህል ስፍር ቁጥር የሌለው ምስጋና ይድረሰው።

በመቀጠል “ፍጡርን የማያመሰግን ፈጣሪን አያመሰግንም” ተብሏልና ለስኬቴ ሁሉ ሰበብ የሆኑ አካላትን ማመስገን እውዳለሁ፡፡ በተለይም “የእዝነትን ክንፍን ዝቅ አድርጉላቸው” የተባልነውን በልጅነቴ ከእኔ ምንንም ጥቅም ሳይፈልጉ በእዝነትና በጭንቀት እራሳቸውን ጥለው ያሳደጉኝን ወላጆቼን ታላቅ ባለውለታዎቼ ናቸውና ከልብ አመሰግናለሁ።

ይህንን ማስታወሻ በመገምገም እና እርማት በመስጠት ለተባበራችሁኝ አቡ መህዲ ሸይኽ ሙሐመድ አወል ሰዒድ፣ ሸይኽ ሐሰን ገላው፣ ኡስታዝ ዩሱፍ አህመድ፣ ኡስታዝ ሰዒድ ሙሳ እና ሌሎችም ወንድሞች የልብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አላህ ምንዳችሁን እጥፍ ድርብ አድርጎ ይክፈልልኝ። ወንድም ሰኢድ ሙሐመድ የመፅሀፍ ሽፋን በመስራት ለተባበርከኝ አላህ ልብስህ የሆነችውን ሷሊሐ ሚስት እንዲሰጥህ መልካም ፍሬዎችን ላንተም ለእኛም እንዲለግሰን ጌታዬን እማፀነዋለሁ።

በመጨረሻም በጣም ላመሰግናቸው የምወደው በቅርቤና በዙርያዬ ያሉ ቤተሰቦቼን እና የሱና ወንድም እና እህቶቼን በጠቅላላ ነው።

بسم الله الرحمن الرحيم

إن الحمد لله نحمده ونستعينه ونستهديه ونستغفره ونتوب إليه ونعوذ بالله من شرور أنفسنا و سيئات أعمالنا من يهده الله فلا مضل له ومن يضلل فلا هادي له وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له وأشهد أن محمدا عبده ورسوله وبعد : فقد قرأت وتصفحت الرسالة التي كتبها أخونا الفاضل سادات كمال – حفظه الله تعالى ورعاه – ورزقه الثبات والسداد . بين فيها أهمية التوحيد وأنواع الشرك وخطورته ، وأدى الأمانة ونصح الأمة ، فألفيتها رسالة مفيدة لأنها اشتملت على أهم عقيدة المسلم ، والأمانة العظمى ، فجزاه الله خير الجزاء ، وأثابه على ما قدمه للأمة من بيان للتوحيد وقمع للشرك وأهله ، وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم .



كبته : حسن بن غلاو حسن

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው፡፡ እናመሰግነዋለን በእርሱም እንታገዛለን ቅኑን ጉዳና ምህረቱንም እንጠይቀለን ወደ እርሱም ተጸጽተን እንመለሳለን፡፡ ከነፍስያችን ተንኮልና ከመጥፎ ስራችን በእርሱ እንጠበቃለን፡፡ አላህ የመራውን ማንም አያጠመውም፡፡ አላህ ያጠመመውን ማንም አይመራውም፡፡ ከአላህ በቀር በሀቅ የሚመለክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ አገልጋይና መልክተኛ መሆናቸውን እንደዚሁ፡፡ የተከበረው ወንድማችን ሳዳት ከማል - አላህ ይጠብቀው፣ ይንከባከበው ጽናትን እና ቀጥተኝነትንም ይለግሰው - የፃፈውን መፅሐፍ አንድ በአንድ አንብቤዋለሁ፡፡ (በመጽሐፈ ውስጥ) የተውሒድን አንገብጋቢነት ፣ የሽርክን አይነቶች እና አደገኝነቱን ግልጽ አድርጓል፡፡ በዚህም አደራውን ተወጥቷል፡፡ ለማህበረሰቡም (ትክክለኛውን) መክሯል፡፡ ይህ መጽሐፍ አንገብጋቢ እና ታላቁ (የሰው ልጆች) አማና የሆነውን የሙስሊሞች አቂዳ ያቀፈ በመሆኑ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ አላህ ጀዛውን በመልካም ይመንዳው፤ ለዚህ ማህበረሰብ ተውሒድን ግልጽ በማድረግ፣ ሽርክን እና የሽርክ ባለቤቶችን አንገት በማስደፋት ላደረገው አስተዋጽኦ አላህ ምንዳውን ይክፈለው፡፡

ጸሐፊ ሐሰን ገላው ሐሰን

بسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله رب العالمين وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وأصحابه ومن اقتدى بهداه ودعا بدعوته إلى يوم الدين أما بعد : فقد قرئت علي رسالة صغيرة المبنى كثيرة المعنى في التوحيد وما يضادها أو ينقصها من الشركيات والبدع ، كتبها أخونا سادات كمال سدد الله خطاه وأجزل مثوبته ، فوجدتها مفيدة لكونها كتبت على ضوء الكتاب والسنة وفهم سلف هذه الأمة ، أرجو أن تطبع جيدا ، ليعم نفعها كل من يريد الحق والإتباع بإذن الله ، والله أعلم . وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين .



كتبه : محمد أول سعيد

ምስጋና ለአለማት ጌታ አላህ ይገባው:: በነብዩ ሙሐመድ ፣ በቤተሰቦቻቸው ፣ በሶሃቦች፣ በእርሳቸው መመሪያ በተከተሉት እና በእርሳቸው ዳዕዋ በተጣሩት ላይ ሁሉ የአላህ ሶለዋት እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ይውረድ::

ከዚህ በመቀጠል፡ በወምድማቾን ሳዳት ከማል አማካኝነት በተውሒድ ፣ ተውሒድን በሚቃረኑ እና በሚሸረሽሩ ሽርኮች እና ቢድዓ ዙርያ የተጻፈውን ቃላቶቹ እጥር ምጥን ያሉ ፤ ትርጉሙ ሰፊ የሆነ መጽሐፍ ተነቦልኛል:: አላህ እርምጃውን ያስተካክልለት ፤ ምንዳውንም ያነባብርለት:: ይህ መጽሐፍ ለዚህ ማህበረሰብ የቀደምቶችን ግንዛቤ ቁርኣን እና ሀዲስን መሰረት በማድረግ የተጻፈ መጽሐፍ በመሆኑ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቶዋለሁ::በጥሩ ሁኔታ ከታተመ ሀቅን ለሚፈልግ እና ለሚከተል ሁሉ ጥቅሙ በአላህ ፍቃድ ሰፊ እንደሚሆን እረዳለሁ::

በነብዩ ሙሐመድ ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በአጠቃላይ የአላህ ሶለዋት ይውረድ::

ጸሐፊ : ሙሐመድአወል ሰዒድ

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው፡፡ በአላህ መልዕክተኛ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እና በእርሳቸው መመሪያ ላይ ለተጓዘ ሁሉ ሶላት እና ሰላምታ ይስፈን፡፡

ሩሱሎች የተውሒድን መልዕክት አንግበው ወደ ህዝብ ሲላኩ የተውሒድ ጠላት የሆኑ አካላት በስድብ፣ ከአገር በማባረር የተለያዩ እንግልቶችን እንደሚያደርሱባቸው የነብያቶችን ታሪክ ላነበበ ሁሉ የሚሰወር አይመስለኝም፡፡ አሁንም “***ታሪክ እራሱን ይደግማል***” እንደሚባለው በተውሒድ ጥሪ ላይ በሚንቀሳቀሱ ዳዒያን ላይ ስቃዩ፣ እንግልቱ፣ ስድቡ እና መታሰሩ የተለመደ ሆኗል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ባለቤት የሆነው ሳዳት - ሓፊዞሁሏህ - ከቅርብ ጊዜ ወዲህ *የወቃሽን ወቀሳ* ሳይፈሩ በተውሒድ እና ሽርክ ዙርያ ህብረተሰብን ከሚጣሩ ውስን ወጣት ዳዒያን መካከል አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህም ምክንያት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ “***ሽርክ ለምን ተነካ***” በሚል አባዜ ሙስሊም ነን ከሚሉ ሰዎች ሳይቀር ከፍተኛ ተቃውሞዎች ደርሰውበታል፡፡ በሬ ወለድ ወሬዎችን አውርተውበታል፡፡ በቤተሰብ መካከል ገብተው ሰላም ነስተውታል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ወንድማችን ይህ ሁሉ ሳይበግረው አላህ በሰጠው የተውሒድ እውቀት ግንዛቤ የተውሒድን አንገብጋቢነት እንዲሁም የሽርክን አስከፊነት ያለምንም ስጋት በአለም የሚገኙ ወገኖቻችን እንዲሰሙት አድርጓል፡፡ በዚህም የጠላ ቢጠላ ወገኖቹን ከገቡበት የሽርክ እና ቢድዓ አረንቋ እንዲወጡ በአላህ ፈቃድ ታድጓል፡፡ በርካታ ሰዎች ከተኙበት እንዲነቁ አድርጓል፡፡ ይህ ወንድማችን በተለያዩ አጋጣሚዎች እና መንገዶች ከሚሰጣቸው የተውሒድ ትምህርቶች ባሻገር በቅርቡ “*ተውሒድ እና ሽርክ*” በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ “***የጻፍኩት መጽሐፍ አለና ለሀትመት ከመግባቱ በፊት እስኪ እናንተ ባሀርዳር የምትገኙ ወንድሞች መጽሐፏን ተመልከቱና እርምት ካላችሁ እርምት ሰጡኝ***” ብሎ የመጽሐፉን ኮፒ በላከልኝ መሰረት የመጽሐፉን ይዘት ለመመልከት ምክሪያለሁ፡፡ አንዳንድ የተመለከትኳቸውን የቃላት ይሁን የትርጉም ግድፈቶችንም እንዲያስተካክል ሐሳብ ሰጥቻለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ መጽሐፍ የተውሒድን እና የሽርክን ልዩነት በቀላሉ እንዲገነዘቡት ለአንባቢ ቀላልና ግልጽ በሆነ መልኩ የቀረበ፣ በተለይም ከመጽሐፉ መጨረሻ በጥያቄ እና መልስ የተዘጋጀው ትምህርት አቂዳን ለማስተካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ ስለማስብ ሁሉም ሙስሊም መጽሐፉን ገዝቶ እንዲያነበው በዚሁ አጋጣሚ አደራ እላለሁ፡፡

ወንድም ሳዳት ከማል በተውሒድ ላይ የሚያደርገውን ዳዕዋ አጠናክሮ እንዲቀጥልበት፣ የሚሰራቸውን ስራዎች ሁሉ ለአላህ እንዲያደርግለት፣ የተነባበረ መልካም ምንዳን እንዲመነዳው፣ በመጽሐፉም ሙስሊሙ ህብረተሰብ እንዲጠቀምበት ፤ ሁላችንንም በተውሒድ አስጀምሮ በተውሒድ እንዲያስጨርሰን አሏሁ - ሱብሓነሁ ወተዓላን - እለምናለሁ፡፡



ዩሱፍ አሕመድ 28/04/2009

ማውጫ

ተውሒድ እና ሺርክ.....1

1. የተውሒድ እውቀት ከየትኛውም እውቀት በፊት ይቀደማል.....1
2. ተውሒድ ምንድን ነው?.....1
3. ተውሒድ የተፈጠርንበት አላማ ነው።.....3
4. አላህ በጌትነቱ አንድ እንደሆነ ሁሉ በአምላክነቱም አንድ ነው።.....4
5. አየቱል-ኩርሲይ እና ሶስቱ የተውሒድ ክፍሎች.....6
6. መልክተኞች ሁሉ የተላኩት ተውሒድን ለማስተማር ነው።.....8
7. መጽሐፍቶች ሁሉ የወረዱበት ዋናው አላማ ተውሒድ ነው።.....9
8. አላህ አልወለደም፣ አልተወለደም፣ የዘር ሀረግም የለውም።.....10
9. የተውሒድ ፋይዳዎች.....11
10. የላኢላሃ ኢለላህ መስፈርቶች.....20
11. ሺርክ ምንድን ነው? አይነቶቹስ?.....23
12. የሺርክ አደጋዎች.....30
13. በችግር ጊዜ አላህን እያመለኩ በሰላሙ ጊዜ ማጋራት ተውሒድ አይባልም።.....39
14. “የአባቶቻችን መንገድ”.....40
15. አማኞቹ ጂኖች በአላህ ላይ አናጋራም ማለታቸው።.....41
16. አላህ በላጭ ነውን? ወይስ ያ የሚያጋሩት?.....42
17. አላህ የአደም ልጆችን ሁሉ ከሺርክ፣ ከሰይጣን አምልኮ እንዲርቁ መክሯል።.....44
18. ከኢጋሪያን መገለጫ ውስጥ አላህ በብቸኝነት ሲወሳ ልባቸው መሸማቀቁ ነው።.....45
19. ሺርክና ሙሽሪኮች በምሳሌ፡-.....46
20. ተውሒድ የአንድነት ዋና መሰረት ነው.....50
21. አንድነት በተውሒድ ከድንቅ ምሳሌ ጋር.....54
22. አማኝ ጦሀራ ነው፣ ሙሽሪክ ነጃሳ ነው.....56

23. የቀኑ ኸይር ሰራተኛ.....57
24. በተውሒድና በሺርክ የሰዎች ማንነት ሲራራቅ.....58
25. ተውሒድ እና ሐጅ.....59
26. አማኝና ከሃዲ ከሞት አፋፍ ላይ.....60
27. የተዘነጋው አላማ.....62
28. ነብዩ ዒሳ፣ ትእዛዞቸው ክፉኛ የተጣሰው የተውሒድ አስተማሪ.....63
29. ከባድ ጥያቄ ድንቅ መልስ።.....64
30. የተንሰራፋው የጂን አምልኮ.....66
31. ኢብራሂም በተውሒድ ምክንያት “ኢማም (መሪ)” ተብሎ ተጠርቷል.....67
32. ተውሒድ የኢብራሂም ጎዳና.....67
33. ትዳር ሊመሰረት የሚገባው ተውሒድ ካለው ሰው ጋር ነው።.....68
34. በተውሒድ ላይ ፅናት.....69
35. የተውሒድ አደራ!.....70
36. ፍፃሜህ በተውሒድ ላይ ይሁን!!.....72
37. የእምነት ጥያቄና መልሶች.....73
38. ተውሒድን ለልጆች ማስተማር.....84
39. ማጠቃለያ.....91

መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርሕሩሕ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው። እናመሰግነዋለን፣ እገዛን እንጠይቀዋለን፣ ምህረትንም እንጠይቀዋለን። ከነፍሳችን ተንኮል፣ ከመጥፎ ስራዎቻችንም በአላህ እንጠበቃለን። አላህ የመራውን ሰው የሚያጠመው የለም፣ ያጠመመውን የሚመራው የለም።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل عمران: ١٠٢

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት። እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ።" [አሊ ዒምራን፡ 102]

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ وَخَلَقَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا وَبَثَّ مِنۡهُمَا رِجَالٗا كَثِيرٗا وَنِسَآءٗۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِي تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلۡأَرۡحَامَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيۡكُمۡ رَقِيبٗا ١ ﴾ النساء: ١

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጀዋን (ሀዋን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ። ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ። አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና።" (አን-ኒሳእ ፡ ፩)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَقُولُواْ قَوۡلٗا سَدِيدٗا ٧٠ يُصۡلِحۡ لَكُمۡ أَعۡمَٰلَكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۗ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَقَدۡ فَازَ فَوۡزًا عَظِيمًا ٧١ ﴾ الأحزاب: ٧٠ – ٧١

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ። ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና። ኀጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል። አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ።" (አል አሕዛብ፡ 70-71)

በመቀጠልም ከንግግር ሁሉ በላጭ የአላህ ንግግር ነው፣ ምርጥ የሚባለው መመሪያ የሙሐመድ ﷺ መመርያ ነው፤ ከነገሮች ሁሉ የከፋው (በዲን ላይ) ፈጠራ ነው፤ ፈጠራ የተባለ ሁሉ ቢድዐ ነው፤ ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነው፤ ጥመት ሁሉ የእሳት ነው።

ይህች አጠር ያለች መፅሐፍ በአላህ ፍቃድ ስለ ተውሒድ ምንነት፣ ወሳኝነት፣ ለተውሒድ ባለቤቶች አላህ ያስቀመጠውን ሽልማት በአጭሩ የዘረዘርኩባት በተቃራኒው የሽርክን ምንነት፣ አደጋውን፣ የሽርክ ባለቤቶች ላይ የተዛተውን ዛቻም አጠር ባለ መልኩ ያስቀመጥኩባት ናት። ማስረጃዎቼን ከስህተት ከፀዳው የአላህ ቃል ቁርኣን፣ የአላህ ጥበቃ ከማይለያቸው መልክተኛው ﷺ ሱና፣ ከመልካም ቀደምቶች እና የነሱን መልካም አርዓያ የተከተሉትን አስተምህሮት ለማድረግ መርጫለሁ። ምክንያቱም ከጥመት የመዳኛው ብቸኛው መንገድ ይህ ስለሆነ። የአላህ ባርያዎች ሆይ! አላህ ዲንን እንዲያስገነዝበን እየለመንኩ፣ የሰው ስራ ከስህተት አይጠራምና መፀሐፉን አስመልክቶ ስህተት ካገኛችሁ በሚከተለው የኢሜል አድራሻዬ ብትጠቁሙኝ ደስተኛ ነኝ።

sadatkemal@gmail.com

ተውሒድ እና ሺርክ

1. የተውሒድ እውቀት ከየትኛውም እውቀት በፊት ይቀደማል

አላህ ለነብዩ ﷺ እንዲህ ይላቸዋል፡-

﴿ فَٱعۡلَمۡ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لِذَنۢبِكَ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مُتَقَلَّبَكُمۡ وَمَثۡوَىٰكُمۡ ١٩ ﴾ محمد: ١٩.

"እነሆ ከአላህ ሌላ በሃቅ የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ሰለ ሰህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን። አላህም መዘዋወሪያቸሁን፣ መርጊያቸሁንም ያውቃልና።" [ሙሐመድ፡ 19]

ከታላላቅ የኢስላም ሊቃውምት ውስጥ ተውሒድን **"ታላቁ እውቀት" /ፊቅሁል አክበር/** ብለው የጠሩት አሉ። ይህም ይህ የእውቀት ዘርፍ ያለውን የላቀ ደረጃ አመላካች ነው።

ነብዩ ﷺ እንዳሉት **"<u>አላህ መልካም የሻለት ሰው ዲኑን ያስገነዝበዋል</u>።"** [ቡኻሪና ሙስሊም] የአምልኮ ሁሉ ቁንጮ ተውሒድ ከሆነ ከእውቀት ሁሉ ቁንጮው ደግሞ የተውሒድ እውቀት ነው።

2. ተውሒድ ምንድን ነው?

በቋንቋ ደረጃ ተውሒድ ማለት ፡- የሆነን ነገር አንድ ማድረግ ማለት ነው።

በሸሪዓዊ ትርጉሙ ደግሞ፡- **ተውሒድ ማለት አላህን ብቸኛ በሆነባቸው ሐቆቹ በብቸኝነት መነጠል ነው።** ለምሳሌ አላህ በጌትነቱ፣ በፈጣሪነቱ፣ በአስተናባሪነቱ፣ ህያው

በማድረጉ፣ በመግደሉ፣ በተመላኪነቱ፣ ለእርሱ ምሉዕ የሆኑ ስምና መገለጫዎች በመኖራቸው ላይ **<u>ያለ አጋር ብቸኛ ነው</u>**። ተውሒድ አልኡሉሂያ ማለት ደግሞ **<u>አላህን በእርሱ ላይ ማንንም ምንንም ሳያጋሩ አምልኮን ለርሱ ብቻ መፈፀም ነው</u>**። እስቲ የሚከተለውን የተውሒድ ቃላት ውስጡ በዝርዝር ምን እንደያዘ እንይ፡-

"لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ يُحْيِي وَيُمِيتُ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ".

"ላኢላሃ ኢልለ-ሏህ ወህደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል-ሙልኩ ወለሁል-ሐምዱ ዩሕይ ወዩሚቱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር።"

<u>ትርጉም</u>

"<u>ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ አምላክ የለም</u>። <u>ብቸኛ ነው</u>። <u>አጋር የለውም</u>። <u>ንግስና (ባለቤትነት) ለእርሱ ናት</u>። <u>ምስጋናም ለእርሱ ነው</u>። <u>ህያው ያደርጋል</u>። <u>ይገድላልም</u>። <u>ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ነው</u>።"

ይህቺ ቃል የያዘችው መልእክት፡-

- **<u>ጌትነቱ (ተውሒድ አርሩቡቢያህ)</u>** ፡- ብቸኛ ፈጣሪና ሁሉን አድራጊ አስተናባሪ፣ ንግስና በጠቅላላ የእርሱ ነች፣ ህያው ያደርጋል፣ ይገድላል፣ ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ይህ የተውሒድ ክፍል ተውሒድ አርሩቡቢያህ ይባላል። ከሶስቱ የተውሒድ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው።

- **<u>አምላክነቱ (ተውሒድ አልኡሉሂያ)</u>** ፡- ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ አምላክ የለም፣ አላህ ብቸኛ ተመላኪ መሆኑን ማረጋገጥ። ይህ የተውሒድ ክፍል ተውሒድ አልኡሉሂያ ይባላል። ከሶስቱ የተውሒድ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው።

- **<u>ስምና መገለጫዎቹ (ተውሒድ አልአስማእ ወስሲፋት)</u>** ፡- “ቻይ” ፣ “ገዳይ” ፣ “ህያው አድራጊ” የሚሉት ምርጥ ምርጥ የአላህ ስሞችና መገለጫዎቹ ሲሆኑ ሌሎችም **አላህ ለራሱ ወይንም መልክተኛው ﷺ ለርሱ ያረጋገጧቸውን** መልካም ስሞችና መገለጫዎች **<u>ትርጉሙን ሳንቀይር</u>፣ <u>ሳናራቁት</u>፣ <u>ሁኔታው እንዲህ ነው ሳንል (ከይፍያ ሳንሰጥ)</u> ፣ <u>ሳናመሳስል</u>፣ <u>ትርጉሙ አይታወቅም ሳንል (ተፍዊድ ሳናደርግ)</u> <u>በመጣበት እውነታ ማፅደቅ ይገባል</u>።** ይህ የተውሒድ ክፍል ተውሒድ አልአስማእ ወስስሲፋት ይባላል። ከሶስቱ የተውሒድ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው።[1]

3. ተውሒድ የተፈጠርንበት አላማ ነው።

አላሁ ሱብሓነሁ ወተዓላ እኛንም ጂኖችንም የፈጠረበት አላማ ተውሒድ እንደሆነ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦ ﴾ الذاريات: ٥٦

“ጂኖችንም ይሁን የሰው ልጆችን <u>እኔን በብቸኝነት እንዲያመልኩኝ እንጂ አልፈጠርኳቸውም</u>።” [አዝ-ዛርያት 56]

በምድር ያለውን ሁሉ ግን የፈጠረው ለእኛ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

---

[1] አንዳንዶች ተውሒዱልሓኪሚያህ የሚል አራተኛ ክፍል የሚጨምሩ አሉ። ይህ ግን እራሱን ችሎ የሚቆጠር የተውሒድ ክፍል ሳይሆን ካሳለፍናቸው የተውሒድ ክፍሎች ውስጥ የሚካተት ነጥብ ነው። ከዚህ ነጥብ የተፈለገው በቁርኣንና በሐዲሥ መዳኘትን እና ሌሎችን አራግፎ ለነሱ ታዛዥ መሆንን ከሆነ ይሄ ከተውሒዱልኡሉሂያህ የሚወጣ አጀንዳ አይደለም። ምክንያቱም የትኛውም አምልኮት ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ የግድ አላህን ብቻ አስቦ በሱናው መሰረት መስራት ያስፈልጋልና። ከዚህ ተውሒድ የተፈለገው ህግ የማውጣት ስልጣኑ የአላህ ብቻ እንደሆነ ለመግለፅ ከሆነ መልእክቱ ከተውሒዱርሩቡቢያህ ውስጥ የሚካተት ነው። ስለዚህ በሁለቱም መልኩ ብናየው ተውሒዱልሓኪሚያህ ከሁለቱ የተውሒድ ክፍሎች አይወጣም። [መጃሊሰትተዝኪሪያህ፡ 195-196]

﴿ هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ لَكُم مَّا فِى ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعًا ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰٓ إِلَى ٱلسَّمَآءِ فَسَوَّىٰهُنَّ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٍۚ وَهُوَ بِكُلِّ شَىۡءٍ عَلِيمٌ ﴿٢٩﴾ ﴾ البقرة: ٢٩

"እርሱ (አላህ) ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው። ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ። ሰባት ሰማያትም አደረጋቸው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።" [አል-በቀራህ፡ 29]

4. አላህ በጌትነቱ አንድ እንደሆነ ሁሉ በአምላክነቱም አንድ ነው።

ሁለት ወይንም ሶስት የሚባሉ አምልኮ የሚገባቸው አካላት እንደሌሉ አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል።

﴿ لَوۡ كَانَ فِيهِمَآ ءَالِهَةٌ إِلَّا ٱللَّهُ لَفَسَدَتَاۚ فَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ رَبِّ ٱلۡعَرۡشِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٢٢﴾ ﴾ الأنبياء: ٢٢

"በሁለቱ (በሰማያትና በምድር) ውስጥ <u>ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ በተበላሹ ነበር።</u> የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ።" [አል-አንዓም፡ 22]

እዚህ ጋር መታወቅ ያለበት ዋና ቁም ነገር ቢኖር ማንኛውም አጋሪ **"ለምን ከአላህ ሌላ ታመልካለህ?"** ተብሎ ቢጠየቅ **"እኛ እኮ ፈጣሪ ናቸው አላልንም"** ፣ **"እኛ እኮ አምላክ ናቸው አላልንም"** ፣ **"አማላጅ እንዲሆኑን እንጂ ሌላ አላልንም"** ፣ **"ወደ አላህ እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አይደለም"** እና የመሳሰለውን ሊል ይችላል።

ዋናው ነገር ለአላህ የሚገባውን አምልኮ ለፍጡር ለማንም ይሁን ለማን አሳልፎ መስጠት <u>ሺርክ (በአላህ ላይ ማጋራት)</u> መሆኑን ማወቅና መጠንቀቅ ነው። **ከአላህ ውጭ ያለውን አካል አምላክ ብሎ ጠራውም አልጠራውም፤ ወደ አላህ እንዲያቃርቡን ነው ብሎ ይሞግትም አይሞግትም። አላህ ከእርሱ ውጭ ማንንም እንዲመለክ ስልጣን አልሰጠም። የቅርብ መላእክም ይሁን ጂብሪልን ይመስል፣ የመልክተኞች ፈርጥ ነብዩን ﷺ ይመስል።**

ታድያ ለነዚህ ሁለት ምርጦች የአላህን አንዱንም መብት አሳልፎ መስጠት ካልተቻለ እንዴት ይሆን ለሌሎች የአላህን መብት አሳልፎ የሚሰጠው?

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ١٨ ﴾ الجن: ١٨

"እነሆ መሰገጃዎችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ።" [አል ጂን፡ 18]

አንድንም አትገዙ የሚለው በደንብ ይሰመርበት። ከአላህ ውጭ መላእክትም፣ ነብይም፣ ጂንም፣ የሚታይም የማይታይም፣ በህይወት ያለም፣ በህይወት የሌለም፣ ማንም ይሁን ማን አምልኮ አይገባውም።

﴿ أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلۡخَالِصُۚ وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ مَا نَعۡبُدُهُمۡ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلۡفَىٰٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَحۡكُمُ بَيۡنَهُمۡ فِي مَا هُمۡ فِيهِ يَخۡتَلِفُونَۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي مَنۡ هُوَ كَٰذِبٞ كَفَّارٞ ٣ ﴾ الزمر: ٣

"ንቁ! ፍጹም ጥሩ የሆነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች አድርገው የያዙት "ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም" (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የሆነን ሰው ሊያቀናም። [አዝ-ዙመር፡ 3]

5. አየቱል-ኩርሲይ እና ሶስቱ የተውሒድ ክፍሎች

ታላቋ የቁርአን አንቀፅ የተባለችው አየቱል-ኩርሲይ[2] እንደሚከተለው የአላህን **ስምና መገለጫ፣ ጌትነቱን፣ ብቸኛ ተመላኪነቱን** ታረጋግጣለች።

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ٢٥٥ ﴾ البقرة: ٢٥٥

- ✓ ***አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው።***

ብቸኛ ተመላኪነቱን ለእርሱ ስምና መገለጫ እንዳሉት አስረጂ ነው።

- ✓ ***ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።***

ለምን? ህይወቱና ህይሉ ምሉእ፣ እንከን የለሽ ስለሆነ ነው። እዚህ ላይ ደግሞ አሏሁ ሱብሓነሁ ወተዓላ ላይ ጎዶሎነትን የምናጠራበት ነው። አላህ ከጎዶሎ ባህሪ ሁሉ የፀዳ ነው። የሚያንገላጀው፣ የሚተኛው ደካማ ብቻ ነው። ጌታችን አላህ ግን ከማንገላጀት፣

---

[2] የአላህ መልክተኛ ﷺ ኡበይ ብኑ ከዕብን (ረድየላሁ አንሁ) **"ከቁርአን ውስጥ ታላቋ አንቀፅ የትኛዋ ናት?"** ብለው ጠየቁ። እሳቸውም **"አላህና መልክተኛው ያውቃሉ"** ሲሉ መለሱ። ከዛ ደግመው ሲጠይቋቸው **"አየቱል-ኩርሲይ"** ሲሉ መለሱ። የአላህ መልክተኛም ﷺ **"እውቀት ያስደስትህ የሙንዚር አባት ሆይ"** አሏቸው [ሙስሊም ዘግበውታል] ። ኡበይ (ረድየላሁ አንሁ) ቁርአንን ሙሉ በሙሉ ሸምድደዋል። ከ6 ሺ በላይ አንቀፆችን ሸምድደው፣ **"ከቁርአን ውስጥ ታላቋ አንቀፅ የትኛዋ ናት?"** ሲባሉ **"አያቱል-ኩርሲ"** ብለው መመለሳቸው **ሰሃባዎች ለተውሒድ ምን ያህል እውቀት እንደነበራቸው ያሳያል**። ተውሒድ ደግሞ የሁለት አገር የስኬት ቁልፍ ነው። ከእያንዳንዱ ፈርድ ሰላት በኋላ የቀራትም (ያነበባትም) ሰው በእሱና በጀነት መካከል ሞት ብቻ መኖሩን የአላህ መልክተኛ ﷺ ነግረውናል። የአላህ ባርያዎች ሆይ! ከፈርድ ሰላት በኋላ ይህችን አንቀፅ በማንበብ ላይ ነፍሴንም እናንተንም አደራ እላለሁ።

ከመድከም፣ ከመተኛት ሁሉ የጠራ ነው። ሰባት ሰማያት፣ ሰባት ምድሮችን በውስጡ ያሉትንም ፈጥሮ ድካም አላገኘውም። ከሚያጋሩበት ሁሉ ጠራ።

- ✓ ***በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው።***

  ይሄ ጌትነቱን የሚያመላክት ነው።

- ✓ ***ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን ነው?***

  <u>ምልጃ ከአላህ ፈቃድ በኋላ ብቻ እንደሚሆን የሚያስረዳ ነው</u>። ምክንያቱም ምልጃ (ሸፈዓህ) የርሱ ንብረት (ሚልክ) ናትና።

- ✓ ***(ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል።***

  ሁሉን አዋቂ አላህ የበፊቱንም የኋለኛውንም ነገር ሁሉ በጥቅልም በዝርዝርም እንደሚያውቅ ማስረጃ ነው።

- ✓ ***በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)።***

  አላህ ካሳወቃቸው በቀር መልክተኞቹም ይሁን ማንም ከዕውቀቱ ምንንም ነገር አያውቁም።

- ✓ ***መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ።***

  ኩርስይ ከሰማያትና ምድር የሰፋ መሆኑን አላህ ገለፀ።

- ✓ ***ጥበቃቸውም አያቅተውም።***

  አላህ ሰማያትና ምድር ጥበቃቸው አያቅተውም።

- ✓ ***እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።*** [አል-በቀራህ፡ 255]

  እውነትም አላህ ከሁሉ በላይ ታላቅ ነው።

6. መልክተኞች ሁሉ የተላኩት ተውሒድን ለማስተማር ነው።

አላህ ምስጋና ሁሉ ለእርሱ ይገባውና ፈጥሮ ብቻ አልተወንም። ከእናታችን ሆድ ጀምሮ የምንበላውን የምንጠጣውን በመለገስ እየተንከባከበን ነው። በምድር ላይ ያለውን ሁሉ ለእኛው አገራልን። የተፈጠርንበትን ዋና አላማ እናሳካ ዘንድ ደግሞ በየዘመኑ መልክተኞችን ተውሒድን አስይዞ ልኳል። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَۖ ﴾ النحل: ٣٦

<u>በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ</u> ***<u>"አላህን (በብቸኝነት) ተገዙ፤ ጣዖትንም [3] ራቁ" በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።"</u>*** [አን-ነሕል 36]

የነብያት ሁሉ መደምደሚያ ነብዩ ሙሐመድም ﷺ እንዲሁ በዚሁ ጉዳይ ታዘዋል። ከሳቸው በፊት ወደ ነበሩት ነብያት መለኮታዊ ራእይ (ወህይ) እንዳወረደው ሁሉ እሳቸውም ላይ ማውረዱን አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል።

[3] ታላቁ ዓሊም ኢብኑል ቀይም ረሂመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- "ጣዖት ማለት ከሚመለከ ወይንም ከሚከተሉት ወይንም ከሚታዘዙት ሁሉ፣ ባርያ ወሰን ያለፈበት ነው።" [ኢዕላሙል ሙወቂዒን፡ 1/64]

አሁንም በመቀጠል እንዲህ ይላሉ፡- "ጣዖታት ብዙ አይነት ናቸው። ቁንጮዎቹ ግን አምስት ናቸው። ኢብሊስ (ዲያቢሎስ) አላህ (ከእዝነቱ) ያርቀውና፣ እየወደደ የተመለከ፣ ከሩቅ እውቀት ውስጥ የሆነን ነገር የሞገተ፣ ሰዎችን ወደራሱ አምልኮ የተጣራ እና አላህ ባላወረደው የፈረደ ናቸው።"

﴿ إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَٰرُونَ وَسُلَيۡمَٰنَۚ وَءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ زَبُورٗا ١٦٣ ﴾ النساء: ١٦٣

"እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ሁሉ ወደ አንተም አወረድን። ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ኢስሓቅም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶቹም፣ ወደ ዒሳም፣ ወደ አዩብም፣ ወደ ዩኑስም፣ ወደ ሃሩንና፣ ወደ ሱለይማንም አወረድን። ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው።" [አን-ኒሳእ፡ 163]

ነብዩ ﷺ የተላኩት ለመላው የሰው ዘር ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٨ ﴾ سبأ: ٢٨

"አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢሆን እንጂ አልላክንህም። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።" [ሰበእ፡ 28]

7. መጽሐፍቶች ሁሉ የወረዱበት ዋናው አላማ ተውሒድ ነው።

በመልክተኞች ላይ የሚወርዱ መለኮታዊ መጽሐፍት ቀዳሚ መልእክታቸው ተውሒድ እንደሆነ አላህ እንዲህ ይገልፀዋል፡-

﴿ يُنَزِّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ بِٱلرُّوحِ مِنۡ أَمۡرِهِۦ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦٓ أَنۡ أَنذِرُوٓاْ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱتَّقُونِ ٢ ﴾ النحل: ٢

"ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ <u>መላእክትን ከራእይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል</u> (ከሐዲዎችን በቅጣት) ለማስጠንቀቂያ፤ <u>እነሆ ከእኔ በቀር በሃቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የለም</u>፤ ፍሩኝም ማለትን (ለሰዓታውቁ በማለት ያወርዳል) ።" [አን-ነሕል: 2]

8. አላህ አልወለደም፣ አልተወለደም፣ የዘር ሀረግም የለውም።

አይሁዳዎች ኡዘይርን የአላህ ልጅ ነው ሲሉ፣ ነሷራዎች ደግሞ ዒሳን (ዐለይሂ ሰላም) የአላህ ልጅ ነው አሉ። የዐረብ አጋሪዎች ደግሞ ነብዩን ﷺ **<u>"የጌታህ የዘር ሀረግ ምንድን ነው?"</u>** ሲሉ ጠየቁ። አላህም ሱረቱል-ኢኽላስን መልስ አድርጎ አወረደ።

﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۝١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۝٢ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۝٣ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ۝٤ ﴾ الإخلاص: ١ – ٤

"በል፡ ጌርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። <u>አልወለደም</u>፤ <u>አልተወለደምም</u>። ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።'" [አል ኢኽላስ: 1-4]

በአላህ ስምና መገለጫ፣ በጌትነቱ፣ በብቸኛ ተመላኪነቱ እርሱን መነጠል የተውሒድ ቁንጮ ነው። የዚች ምእራፍ ዋጋ የላቀው ለዋዛ አይደለም። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል:-

"من قرأ (قل هو الله أحد) حتى يختمها عشر مرات بنى الله له قصرا في الجنة"

"ቁል ሁወላሁ አሐድን ሙሉውን 10 ጊዜ ያነበበ ሰው፣ <u>አላህ ጀነት ውስጥ ህንፃ ይገነባለታል</u>።" [አስሶሂሃ: 589]

ይህቺ ምዕራፍ የቁርአን ሲሶን (1/3) ትስተካከላለች።[4] አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ (ረዲየላሁ አንሁ) ባስተላለፉት የአላህ መልክተኛ ﷺ ለባልደረባዎቻቸው **"በአንድ ለሊት የቁርአን አንድ ሶስተኛ (ሲሶውን) ማንበብ የሚችል የለምን?"** አሉ። በጣም ከባድ ሆነባቸውና **"የአላህ መልክተኛ ማን ነው ይህን የሚችለው?"** አሉ። እሳቸውም **"ቁል ሁወላሁ አሃድ (ሱረቱል አል-ኢኽላስ) የቁርአን ሲሶ (አንድ ሶስተኛ) ነው"** አሉ። [አል-ቡኻሪ፡4629]

እንግዲያውስ የአላህ ባርያዎች ይህንን ብስራት ለሌሎች የአላህ ባርያዎች አዳርሱት። ተውሒድ ይህን ያህል ጀነትን ከነ ድልቦቿ ታወርሳለች።

9. የተውሒድ ፋይዳዎች

9.1. ተውሒድ የታሪክ መዝገብን ይቀይራል

ተውሒድ ወንጀሎችን ከማስማርም ባሻገር ወንጀሎችን ወደ መልካም ስራ መዝገብ ይቀይራል። አንድ ሰው እስልምናን ከመቀበሉ በፊት የሰራውን ሁሉ ወንጀል ተውሒድን ሲቀበል ያ ሁሉ ወንጀሉ ይሰረዝለታል። እንዲያውም ወንጀሉ ወደ መልካም ስራ ይቀየርለታል። ነብዩ ﷺ ለዐምር ኢብኑል ዓስ እንዲህ ብለውታል፡-

أَمَا عَلِمْتَ أَنَّ الإِسْلاَمَ يَهْدِمُ مَا كَانَ قَبْلَهُ؟

[4] [ቡኻሪ: 5014፣ ሙስሊም፡ 1922]

“ኢስላም ከእርሱ በፊት (እስልምናን ከመቀበል በፊት) ያለውን እንደሚያብስ አላወቅክምን?” እንደሚታወቀው የኢስላም አንኳር ነጥቡ ተውሒድ ነው። ተውሒድ የሌለው ኢስላም የለውምና።

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَٰلِحًا فَأُوْلَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمْ حَسَنَٰتٍ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٧٠﴾ ﴾ الفرقان: ٧٠.

“ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር። እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል። አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው።” [አል ፉርቃን፡ 70]

﴿ قُل لِّلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِن يَنتَهُواْ يُغۡفَرۡ لَهُم مَّا قَدۡ سَلَفَ وَإِن يَعُودُواْ فَقَدۡ مَضَتۡ سُنَّتُ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٣٨﴾ ﴾ الأنفال: ٣٨.

“ለነዚያ ለካዱት በላቸው፡- ቢከለከሉ ለእነርሱ በእርግጥ ያለፈውን (ሥራ) ምሕረት ይደረግላቸዋል። (ወደ መጋደል) ቢመለሱም (እናጠፋቸዋለን)። የቀድሞዎቹ ሕዝቦች ልማድ በእርግጥ አልፋለችና።” [አል አንፋል፡ 38]

9.2. ተውሒድ የደህንነትና የሲሳይ ዋስትና ነው

አላህ አንዲትን ከተማ እንዲህ ሲል ምሳሌ አደረገ። ያቺ ከተማ መልካም ነገሮችን ሁሉ የተሰጠች የነበረች ከተማ መሆኗን እና ከዛ በኋላ ግን የአላህን ፀጋ በማስተባበሏ ምክንያት የረሀብና የፍርሃት ቅጣን እንደቀመሰች እንደሚከተለው ይነግረናል። ይህች ከተማ መካ ነች ተብሏል። የመካ ሰዎች የአላህ መልክተኛን ﷺ በማስተባበላቸው ምክንያት አላህ ያቀመሳቸውን የቅጣት አለንጋ የገለፀበት ተምሳሌት ነው። የአላህ መልክተኛ ﷺ ጥሪያቸውን አልቀበል ሲሏቸው አላህን **“የዩሱፍን ህዝቦች 7 አመት**

እንዳስራብካቸው አስርባቸው" ብለው ተራገሙ። አላህም የመልክተኛውን ﷺ ጥሪ በመስማት፣ ለአመፀኞች የአመፃቸውን ውጤት አቀመሳቸው። ይሄ በብዙ የተፍሲር ሊቃውንት የተነገረ ነው። [አድዋኡል በያን፡ 2/456-457]

﴿ وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا قَرْيَةً كَانَتْ ءَامِنَةً مُّطْمَئِنَّةً يَأْتِيهَا رِزْقُهَا رَغَدًا مِّن كُلِّ مَكَانٍ فَكَفَرَتْ بِأَنْعُمِ ٱللَّهِ فَأَذَٰقَهَا ٱللَّهُ لِبَاسَ ٱلْجُوعِ وَٱلْخَوْفِ بِمَا كَانُوا۟ يَصْنَعُونَ ﴿١١٢﴾ ﴾ النحل: ١١٢.

"አላህ ጸጥተኛ፣ የረጋች፣ ሲሳይዋ ሰፊ ሆኖ ከየሰፍራው ይመጣላት የነበረችውን <u>ከዚያ በኋላ ግን በአላህ ጸጋዎች ስለካደች አላህም ይሠሩት በነበሩት ኃጢአት የረኃብንና የፍርሃትን ቅጣቶች ያቀመሳትን ከተማ ምሳሌ አደረገ።</u>" [አን-ነሕል፡ 112]

9.3. ተውሒድ ከጭንቅ መገላገያ ነው።

﴿ وَذَا ٱلنُّونِ إِذ ذَّهَبَ مُغَٰضِبًا فَظَنَّ أَن لَّن نَّقْدِرَ عَلَيْهِ فَنَادَىٰ فِى ٱلظُّلُمَٰتِ أَن لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبْحَٰنَكَ إِنِّى كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٨٧﴾ ﴾ الأنبياء: ٨٧.

"የዓሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በሼደ ጊዜ (አስታውስ)። በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ። (ዓሳም ዋጠው)። <u>በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር በሃቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የለም። ጥራት ይገባህ። እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ በማለት ተጣራ።</u>" [አል አንቢያ፡ 87]

አላህን ትቶ ፍጡራንን ለሚጠራ ሰው ይሄ ከባድ ተግሳፅ ነው። አላህ ነብዩላህ ዩኑስን ከአሳነባሪ ሆድ ውስጥ ሆነው፣ የለመኑትን ልመና ሰምቶ መልስ እንደሰጣቸውና ከጭንቀት እንዳወጣቸው ማስታወስ ዛሬ ህያው አላህን ትተው ሙታንን ለሚጣሩ ሰዎች ጥሩ መገሰጫ ነው። ይሄ በጭንቅም በሰላሙም ጊዜ ወደ አላህ መዞር የነብያት እና

የተከታዬቻቸው ሱንና (ባህሪ) ነው። ኢብራሂም (አለይሂ ሰላም) እሳት ውስጥ ሲወረወሩ ሙሉ ተወኩላቸውን በአላህ ላይ በማድረጋቸው ነው የተረፉት። የኑሕንም እንመልከት፡-

﴿كَذَّبَتۡ قَبۡلَهُمۡ قَوۡمُ نُوحٖ فَكَذَّبُواْ عَبۡدَنَا وَقَالُواْ مَجۡنُونٞ وَٱزۡدُجِرَ ٩ فَدَعَا رَبَّهُۥٓ أَنِّي مَغۡلُوبٞ فَٱنتَصِرۡ ١٠﴾
القمر: ٩ – ١٠.

"ከነርሱ በፊት የኑሕ ህዝብ አስተባበሉ። ባሪያችንን በማስተባበል እብድ ነው ሲሉ ገላመጡ። (እሱም) ፡ እኔ የተሸነፍኩ ነኝና <u>እርዳኝ ሲል</u> ጌታውን ጠራ።"
[አል ቀመር፡ 9-10]

አላህም በበደለኛ ህዝቦች ላይ ረዳቸው። እሳቸውንም ያመኑትንም በመርከቧ ላይ ተንሳፈው በምድርም በሚቀጥለው አለምም ለድል በቁ። **የነብያት ተምሳሌት አላህን በብቸኝነት ማምለክ በእርሱም ላይ ምንንም አለማጋራት ነበር**። በዘመናችን እስልምና ነብዩ ﷺ እንዳሉት ተመልሶ እንግዳ ስለሆነ ሰይጣን እና ሰራዊቶቹ በአላህ ላይ ማጋራትን እንደ ነባሩ እስልምና፣ አላህን በብቸኝነት ማምለክን እንደ መጤ ሃይማኖት አድርገው በያገኙት ሚድያ ሁሉ ይሰብካሉ። ነገ አላህ በባርያዎቹ መሃል በሃቅ ይፈርዳል። እስከ እለተ ሞታችን በያዝነው በነብያት መንገድ ተውሒድ ላይ መፅናት ግድ ነው። አላህ በሀቅ ላይ ከሚፀኑት ያድርገን።

9.4. ተውሒድ ወንጀልን ያስምራል

አንድ ባርያ ከሺርክ ፀድቶ፣ በተውሒድ ላይ ሆኖ ጌታውን ከተገናኘ አላህ በምን አይነት ምህረት እንደሚቀበለው በሐዲሰል ቁድሲይ እንደሚከተለው ተነግሮናል

"يَا ابْنَ آدَمَ لَوْ بَلَغَتْ ذُنُوبُكَ عَنَانَ السَّمَاءِ ثُمَّ اسْتَغْفَرْتَنِي غَفَرْتُ لَكَ، وَلاَ أُبَالِي، يَا ابْنَ آدَمَ إِنَّكَ لَوْ أَتَيْتَنِي بِقُرَابِ الأَرْضِ خَطَايَا ثُمَّ لَقِيتَنِي لاَ تُشْرِكُ بِي شَيْئًا لأَتَيْتُكَ بِقُرَابِهَا مَغْفِرَةً".

“የኣደም ልጅ ሆይ! ወንጀሎችህ የሰማይ ደመና ቢደርሱ ምህረትን ከጠየቅከኝ እምርልህለሁ ደንታ ኣይኖረኝም። የኣደም ልጅ ሆይ! ምድርን ለመሙላት የቀረቡ ወንጀሎችን ሰርተህ ወደኔ ብትመጣ <u>በኔ ላይ ምንም ሳታጋራ ካገኘሽኝ ምድርን ሊሞላ የቀረበ ምህረትን ይዤ እመጣህለሁ።</u>” [አስ-ሶሒሐህ: 200]

ይሄ የሚገኘው ግን ሺርክ ከሌለ ነው። እዚህ ላይ የሐዲሥ ሊቃውንት እንደሚሉት ከትንሹም ከትልቁም የሽርክ ኣይነት ንፁህ ለሆኑ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ሽልማት ነው። ጌታችን እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُۚ وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱفۡتَرَىٰٓ إِثۡمًا عَظِيمًا ٤٨ ﴾ النساء: ٤٨

“<u>ኣላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም ኣይምርም</u>። ከዚህ (ከሺርክ) ሌላ ያለውንም (ኀጢኣት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በኣላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢኣት በእርግጥ ቀጠፈ።” [አን-ኒሳእ፡ 48]

ልብ ሊባል የሚገባው ከሺርክ ውጭ ያለው ወንጀል ከተቀጣ የሚያስቀጣው የወንጀሉን ያህል ብቻ ነው። ከዛም ጀነት ይገባል። **<u>ከሺርክ የከፋ ወንጀል ስለሌለ በኣላህ ላይ እያጋራ የሞተ ሰው ዘላለም እሳት ውስጥ ዘውታሪ ሆኖ ይቀራል</u>**።

9.5. ተውሒድ የኑብዩን ﷺ ምልጃ ያስገኛል

ኣህሉስ-ሱንና ወልጀማዐህ ሸፈዐ ወይንም ምልጃ እንዳለ ያፀድቃሉ። ታላቁ ኣማላጅም ነብዩ ﷺ እንደሆኑ ያምናሉ። ቁርኣን ያማልዳል፣ ልጆች ቤተሰባቸውን ያማልዳሉ፣ ጓደኛ ጓደኛውን ያማልዳል። ይህ ምልጃ የሚሰራው ግን **<u>ኣማላጅም ተማላጅም ከሺርክ ፀድተው</u>** **<u>በተውሒድ ላይ የሞቱ ሰዎች ሲሆኑና የኣላህ ፍቃድ ሲኖር ነው</u>**።

ስለዚህ በቅድሚያ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ምልጃ ሁሉ የአላህ መሆኑ ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ قُل لِّلَّهِ ٱلشَّفَٰعَةُ جَمِيعًا ۖ لَّهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ ثُمَّ إِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٤٤﴾ ﴾ الزمر: ٤٤.

"ምልጃ ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። የሰማያትና የምድር ሥልጣን የእርሱ ብቻ ነው። ከዚያም ወደ እርሱ ትመለሳላችሁ። በላቸው።" [አዝ-ዙመር፡ 44]

ከዚህ በመቀጠል አማላጆች ለተማላጆች ማማለድ የሚችሉት **አላህ ለአማላጅ እንዲያማልድ ሲፈቅድለት ለተማላጅም እንዲማለድለት ሲወድለት ብቻ ነው**። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ ﴾ البقرة: ٢٥٥.

"ያ እርሱ (አላህ) ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን ነው?" [አል በቀራህ፡ 255]

﴿ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ٱرْتَضَىٰ وَهُم مِّنْ خَشْيَتِهِۦ مُشْفِقُونَ ﴿٢٨﴾ ﴾ الأنبياء: ٢٨.

"በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ለወደደውም ሰው እንጅ ለሌላው አያማልዱም። እነርሱም እርሱን ከመፍራታቸው የተነሳ ተጨናቂዎች ናቸው።" [አል አንቢያ፡ 28]

﴿ وَكَم مِّن مَّلَكٍ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ لَا تُغْنِى شَفَٰعَتُهُمْ شَيْـًٔا إِلَّا مِنۢ بَعْدِ أَن يَأْذَنَ ٱللَّهُ لِمَن يَشَآءُ وَيَرْضَىٰٓ ﴿٢٦﴾ ﴾ النجم: ٢٦

"በሰማያት፡ <u>አላህ ለፈለገውና ለወደደው</u> እንዲማለድለት ከፈቀደ በኋላ ካልሆነ በስተቀር ምልጃዎቻቸው የማይጠቅሙ የሆኑ ስንት መላእክት አሉ?" [አን-ነጅም፡ 26]

አላህ እንዲያማልድም እንዲማለድለትም የፈቀደላቸው ብቻ ናቸው ማማለድም፣ መማለድም የሚችሉት። **<u>አላህ ደግሞ ይህንን በኢጋሪያን ላይ እርም አድርጎታል።</u>**

ምልጃ የሚጠየቀው አላህ ብቻ ነው። **<u>ከአላህ ውጭ ያለን አካል ምልጃን መጠየቅ ሺርክ ነው</u>**።

የአላህ መልክተኛ ﷺ አላህ ከፈቀደላቸው በኋላ አማላጅ ቢሆኑም፣ እሳቸውን ግን በቀጥታ ምልጃ እንደማንጠይቃቸው እና አላህን ብቻ እሳቸውን አማላጅ እንዲያደርግልን እንድንጠይቅ እንዲህ ሲሉ ያስተምሩናል።

<u>"አላህ ሆይ! ነብዩን አማላጄ አድርግልኝ።"</u> [ኢማሙ ቲርሚዚ ሀሰኑን ሶሒህ ብለውታል]

በነብዩ ﷺ ምልጃ እድለኛ ለመሆን ከታላላቅ ዋና ዋስትናዎች ውስጥ የተውሒድን ቃል "**<u>ላኢላሃ ኢለላህን</u>**" ጥርት አድርጎ ከልቡ ማለት ነው። ይህንንም የሚጠቁመን የሚከተለው የነብዩ ﷺ ሐዲሥ ነው።

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ أَنَّهُ قَالَ: قِيلَ يَا رَسُولَ اللَّهِ مَنْ أَسْعَدُ النَّاسِ بِشَفَاعَتِكَ يَوْمَ القِيَامَةِ؟ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَقَدْ ظَنَنْتُ يَا أَبَا هُرَيْرَةَ أَنْ لاَ يَسْأَلُنِي عَنْ هَذَا الحَدِيثِ أَحَدٌ أَوَّلُ مِنْكَ لِمَا رَأَيْتُ مِنْ حِرْصِكَ عَلَى الحَدِيثِ أَسْعَدُ النَّاسِ بِشَفَاعَتِي يَوْمَ القِيَامَةِ، مَنْ قَالَ لاَ إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ، خَالِصًا مِنْ قَلْبِهِ، أَوْ نَفْسِهِ».

ከአቡ ሁረይራህ ተይዞ **"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእለተ-ቂያማህ ምልጃዎትን በማግኘት ከሰው ሁሉ እድለኛው ማን ነው?"** ተባሉ። **"አቡ ሁረይራህ ሆይ! ለሐዲሥ ያለህን ጉጉት ከማስተዋሌ የተነሳ ስለዚህ ሐዲሥ ካንተ ቀድሞ ማንም እንደማይጠይቀኝ ገምቼ ነበር።**

በቂያማህ ቀን በምልጃዬ ከሰው ሁሉ እድለኛው ከልቡ ወይም ከነፍሱ ጥርት አድርጎ ‘ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም’ ያለ ነው” አሉ።” [ቡኻሪ፡ 99]

9.6. በተውሒድ የተከተሏቸውን የአንድ ቤተሰብ አባላት አላህ በጀነት ላይ በእኩል ደረጃ ይሰበስባቸዋል

﴿ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱتَّبَعَتۡهُمۡ ذُرِّيَّتُهُم بِإِيمَٰنٍ أَلۡحَقۡنَا بِهِمۡ ذُرِّيَّتَهُمۡ وَمَآ أَلَتۡنَٰهُم مِّنۡ عَمَلِهِم مِّن شَيۡءٖۚ كُلُّ ٱمۡرِيِٕۭ بِمَا كَسَبَ رَهِينٞ ٢١ ﴾ الطور: ٢١.

“እነዚያም ያመኑትና ዝርያቸውም በእምነት የተከተለቻቸው ዝርያቸውን በእነርሱ እናስጠጋለን።[5] ከሥራቸውም ምንም አናንሷልባቸውም። ሰው ሁሉ በሠራው ሥራ ተያዢ ነው።” [አጥ-ጡር 21]

ተመልከቱ የአላህ ባርያዎች፣ የአላህ መልክተኛ ﷺ ጀነት (የተለያየ) ደረጃ እንዳላት ነግረውናል። ቤተሰቦች የተለያየ የጀነት ደረጃ ላይ ቢሆኑም እንኳን ቸሩ፣ እዝነተ ሰፊው አላህ በእምነት እስከተከተሏቸው ድረስ ቤተሰቦችን ያስጠጋቸዋል (ይሰበስባቸዋል)። ጌታችን ምስጋና ይገባውና ምንኛ ያማረ ሰብሳቢ ነው።

[5] ተከታዬቻቸው የቤተሰባቸውን ያህል ስራ ባይሰሩም እንኳን ያው አማኝ እስከሆኑ ድረስ ወይንም የቤተሰቦቻቸውን እምነት እስከተከተሉ ድረስ ከታችኛው ደረጃ ወደ ላይኛው ደረጃ አላህ ያስጠጋቸዋል (ይሰበስባቸዋል)።

9.7. በተውሒድ ከሞት በኋላም የአማኞችን ዱዓ መጎናፀፍ ይቻላል

አምነው ለሞቱት ሰዎች ባናውቃቸውም ዱዓ ስናደርግ፣ ለአጋርያን ግን የቅርብ ዘመድ እንኳን ቢሆኑ ምህርትን እንዳንጠይቅላቸው ተከልክለናል። በአላህ ላይ አምነው ለሞቱ ሰዎች ዱዓ እናደርጋለን።

﴿ وَٱلَّذِينَ جَآءُو مِنۢ بَعۡدِهِمۡ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا وَلِإِخۡوَٰنِنَا ٱلَّذِينَ سَبَقُونَا بِٱلۡإِيمَٰنِ وَلَا تَجۡعَلۡ فِي قُلُوبِنَا غِلّٗا لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ رَبَّنَآ إِنَّكَ رَءُوفٞ رَّحِيمٌ ١٠ ﴾ الحشر: ١٠.

እነዚያም (ከሰሃባዎች) ከበኋላቸው የመጡት "ጌታችን ሆይ! ለእኛም ለእነዚያም <u>በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን</u> <u>ምሕረት አድርግ</u>። በልቦቻችንም ውሰጥ ለእነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ። ጌታችን ሆይ! አንተ ርኀሩህ አዛኝ ነህና ይላሉ።"
[አል ሐሽር፡ 10]

አንቀፁ በዋናነት ሰሃባዎችን ቢመለከትም "**<u>በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምሕረት አድርግ</u>**" እያልን በህይወት ያለነው ጌታችንን እንለምነዋለን።

ሌላው የአላህ መልክተኛ ﷺ **"አንድ ሰው ሙስሊም ሆኖ ሞቶ <u>በእርሱም (ጀናዛ) ላይ 40 በአላህ ላይ ምንንም የማያጋሩ ሰዎች</u> (ሊሰግዱበት) አይቆሙም <u>አላህ ምልጃቸውን ቢቀበላቸው እንጂ</u>"** ብለዋል። ሐዲሱን ኢማሙ ሙስሊም ዘግበውታል።

በተቃራኒው ተውሒድ በሺርክ ሲበከል ግን ምህረት ማድረግ አይፈቀድም። ቢደረግም አይጠቅምም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ مَا كَانَ لِلنَّبِيِّ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَن يَسۡتَغۡفِرُواْ لِلۡمُشۡرِكِينَ وَلَوۡ كَانُوٓاْ أُوْلِي قُرۡبَىٰ مِنۢ بَعۡدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَحِيمِ ١١٣ ﴾ التوبة: ١١٣.

"ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት <u>ለሟገሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች</u> ቢኾኑም እንኳ እነሱ (ከሓዲዎቹ) የእሳት ባለቤቶች መኾናቸው ከተገለጸላቸው በኋላ <u>ምሕረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም</u>።" [አት-ተውባህ፡ 113]

﴿ وَمَا كَانَ ٱسۡتِغۡفَارُ إِبۡرَٰهِيمَ لِأَبِيهِ إِلَّا عَن مَّوۡعِدَةٖ وَعَدَهَآ إِيَّاهُ فَلَمَّا تَبَيَّنَ لَهُۥٓ أَنَّهُۥ عَدُوّٞ لِّلَّهِ تَبَرَّأَ مِنۡهُۚ إِنَّ إِبۡرَٰهِيمَ لَأَوَّٰهٌ حَلِيمٞ ١١٤ ﴾ التوبة: ١١٤.

"የኢብራሂምም ለአባቱ ምሕረትን መለመን ለእርሱ ገብቶለት ለነበረችው ቃል (ለመመላት) እንጂ ለሌላ አልነበረም። <u>እርሱም የአላህ ጠላት መኾኑ ለእርሱ በተገለጸለት ጊዜ ከርሱ ራቀ፤ (ተወው)</u>። ኢብራሂም በእርግጥ በጣም ርኅሩኅ ታጋሽ ነውና።" [አት-ተውባህ፡ 114]

10. የላኢላሃ ኢለላህ መስፈርቶች

የላኢላሃ ኢለላህ ትርጉም፡- "**<u>ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ አምላክ የለም</u>"** ማለት ነው። ላኢላሃ ኢለላህ ሁለት ማእዘኖች (አርካኖች) አሉት። እነሱም፡-

- **ነፍይ (ውድቅ ማድረግ) ፡-** ማለትም አምልኮን ከሁሉም ላይ በጠቅላላ መግፈፍ፣ ውድቅ ማድረግ ነው። ቃሉም "ﻻ ኢላሃ" /ﻻ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም/ የሚለው ቃል ነው።
- **ኢስባት (ማረጋገጥ)፡-** አምልኮ ሁሉ በሃቅ ለሚገባው እውነተኛው አምላክ አላህ ብቻ ማረጋገጥ ነው። ይህም ‹‹ኢለላህ›› /አላህ ሲቀር/ የሚለው ቃል ነው።

ስለዚህ ከአላህ ውጭ ያሉት አለም ላይ የሚመለኩ በጠቅላላ ወደውም ይሁን ያለፍቃዳቸው፣ አምላክ ተብለውም ይጠሩ አይጠሩ፣ ለነሱ የሚፈፀመው አምልኮ በጠቅላላ ውድቅ ነው። **<u>በሃቅ ሊመለክ የሚገባው ብቸኛ ፈጣሪ</u>**፣ **<u>ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ የሆነው</u>**

<u>አንድ አምላክ አላህ ብቻና ብቻ ነው</u>። የላኢላሃ ኢለላህ ዋና ማእዘናት እነዚህ ናቸው። አምልኮን በጠቅላላ ከአላህ ውጭ ካሉት ላይ ውድቅ ማድረግና በሃቅ ለሚመለከው አንድ አላህ ብቻና ብቻ ማፅደቅ።

የላኢላሃ ኢለላህ ስያሜዎች

- ✓ ከሊመቱል-ኢስላም (የኢስላም ቃል) ፡- እሷን ሳይቀበሉ፣ ሳያውቁ እስልምና የለምና፣
- ✓ ከሊመቱ አት-ተቅዋ፡- አላህን የመፍራት ቃል ናት። ባርያን በአላህ ላይ ከማጋራት ትከለክላለች፣
- ✓ ከሊመቱል-ውሥቃ፡- አስተማማኝ ቃል፣ መበጠሻ የሌላት ዘለበታማ ገመድም ተብላለች። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ٢٥٦ ﴾ البقرة: ٢٥٦.

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ (የነብዩ ﷺ) ከጠማማው (ከነ አቡ ጀህልና መሰሎቻቸው) መንገድ በእርግጥ ተገለጠ። <u>በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ</u>። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።"
[አል-በቀራህ፡ 256]

- ✓ ከሊመቱል-ኢኽላስ፡- ማጋራትን ውድቅ የምታደርግ የማጥራት ቃል ናት፣
- ✓ ከሊመቱል-ፋሪቃ፡- በኩፍር እና በኢስላም መሃል የምትለያይ ቃል ተብላለች፣
- ✓ ከሊመቱ አት-ተውሒድ፡- ተውሒድ የሚረጋገጥባት ቃል ተብላለች።

- ✓ ከሊመቱ-ጦይባህ (መልካም ቃል) ፡- ተውሒዱ ያማረለት ሰው የሚሰራቸው ተግባሮቹ ምን ያህል ፍሬ እንደሚያፈሩለት አላህ የተውሒድን ቃል እንዲህ አድርጎ በምሳሌነት ያቀርብልናል።

﴿ أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا كَلِمَةٗ طَيِّبَةٗ كَشَجَرَةٖ طَيِّبَةٍ أَصۡلُهَا ثَابِتٞ وَفَرۡعُهَا فِي ٱلسَّمَآءِ ٢٤ تُؤۡتِيٓ أُكُلَهَا كُلَّ حِينِۭ بِإِذۡنِ رَبِّهَاۗ وَيَضۡرِبُ ٱللَّهُ ٱلۡأَمۡثَالَ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَتَذَكَّرُونَ ٢٥ ﴾ إبراهيم: ٢٤ ــ ٢٥.

"አላህ መልካምን ቃል (ተውሒድን) ሥርዋ (በምድር ውስጥ) የተደላደለች ቅርንጫፍዋም ወደ ሰማይ (የረዘመች) እንደሆኑች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለጸ አላየኽምን? ምግቧን (ፍሬዋን) በጌታዋ ፍቃድ በየጊዜው ትሰጣለች። አላህም ለሰዎች ይገሰጹ ዘንድ ምሳሌዎችን ይገልጻል።" [ኢብራሂም፡ 24-25]

የላኢላሃ ኢለላህ መስፈርቶች

የላኢላሃ ኢለላህ መስፈርቶች ስምንት ናቸው። እነርሱም፡-

- የመሀይምነት ተፃራሪ የሆነው እውቀት፣
- የጥርጣሬ ተፃራሪ የሆነው እርግጠኝነት፣
- የማጋራት ተፃራሪ የሆነው ማጥራት (ኢኽላስ)
- የውሸት ተፃራሪ የሆነው እውነተኝነት፣
- የመጥላት ተፃራሪ የሆነው መውደድ፣
- የመተው ተፃራሪ የሆነው መቀበል፣
- የተቃውሞ ተፃራሪ የሆነው መታዘዝ፣
- ከአላህ ውጭ ባሉ አማልክቶች ሁሉ መካድ ናቸው።[6]

[6] ለእነዚህ ስምንት መስፈርቶች በቂ ማብራርያ የፈለገ በዘርፉ በተፃፉ ኪታቦች ላይ በዝርዝር ማግኘት የሚቻል ሲሆን ለአብነትም በሸይኽ ሙሐመድ ሰዒድ ረስላን የተዘጋጀችዋን "ላኢላሃ ኢለላህ፡ ትርጉሟ፣ መስፈርቶቿ፣ የምታስፈርደው እና ምንዳዋ" የተሰኘች መጠነኛ መፅሐፍ መመልከት ይቻላል።

፲፩. ሺርክ ምንድን ነው? ኣይነቶቹስ?

ሸርክ ማለት?

<u>በቋንቋ ደረጃ</u>፡- ሁለት ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን እኩል ማድረግ ማለት ነው። ወይም በእኩል ማጋራት ነው።

<u>በሸሪዓው</u>፡-

- **ጥቅል (ዓም) ትርጉሙ፣ <u>ከአላህ ውጭ ያለን ማንኛውም ነገር አላህ ብቻ በተለየባቸው ጉዳዮች ላይ ከሱ ጋር እኩል ማድረግ</u>**። ይህ ገለፃ ሶስቱንም የተውሒድ አይነቶች ለማንኛውም አካል አሳልፎ መስጠት እንደማይቻል ይጠቁማል።
- **ኻስ (ልዩ)** ከአላህ ውጭ ያለን አካል **<u>ለአላህ ተቀናቃኝ ማድረግ</u>** ነው።

የሸርክ አይነቶች እንደሚከተሉት ናቸው።

- ትልቁ ሸርክ፡- ከአምልኮ ክፍል አንዱንም ቢሆን ከአላህ ውጭ ላለ አካል መስጠት ሲሆን ይህ የሸርክ ክፍል ከኢስላም ያስወጣል።
- ትንሹ ሸርክ፡- ይዩልኝ፣ ይስሙልኛ ከትንሹ ሸርክ ናቸው።ከኢስላም አያስወጣም።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ١٨ ﴾ الجن: ١٨.

"እነሆ መሰገጃዎች ሁሉ የአላህ ብቻ ናቸው። (በውሰጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ።" [አል ጂን፡ 18]

﴿ وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ﴾ النساء: ٣٦.

"አላህን (በብቸኝነት) አምልኩ በእርሱም ላይ ምንንም አታጋሩ።" [አን-ኒሳእ፡ 36]

አጋሪዎች ሲያመልኳቸው ለነበሩ አካላት ነገ በቂያማ ቀን እንዲህ ይላሉ፡-

﴿ تَٱللَّهِ إِن كُنَّا لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٩٧ إِذۡ نُسَوِّيكُم بِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٩٨ ﴾ الشعراء: ٩٧ – ٩٨.

"በአላህ እንምላለን እኛ በግልፅ መሳሳት ውሰጥ ነበርን። ከአለማቱ ጌታ ጋር ባስተካከልናችሁ (ኢጋር ባደረግናችሁ) ጊዜ።" [አሽ-ሹዐራእ፡ 97-98]

ሺርክ ወይም ባእድ አምልኮ አንዳንዶች እንደሚያስቡት **ነብዩላህ ዒሳን፣ መላእክቱ ጂብሪልን ማምለክ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም**። ተመላኪው ከአላህ ውጭ እስከሆነ ድረስ አምልኮት ለማንም ቢፈፀም ባዕድ አምልኮ ነው። **አላህ በፈጣሪነቱ ብቸኛ እንደሆነው ሁሉ በተመላኪነቱም ብቸኝነቱ ሊጠበቅ ይገባል**።

ስለዚህ አላህ ብቻ ሊለመን ሲገባው ከአላህ ውጭ ያለን አካል አላህ ብቻ ማድረግ በሚችለው ጉዳይ ላይ፣ በህይዎት ያለንም ይሁን የሞተን አካል ልጅ ስጡኝ፣ አከብሩኝ፣ ጤና ስጡኝ እና የመሳሰለውን ብሎ መለመን ሺርክ ነው። ለአላህ ብቻ ስግደት ሊፈፀምለት ሲገባ ከአላህ ውጭ ላሉ አካላት መስገድ ሺርክ ነው። ሊመኩበት የሚገባው አላህ ብቻ ሆኖ ሳለ ከአላህ ውጭ በነብይም ላይ ይሁን በመልአክትም ላይ መመካት ሺርክ ነው።

የማይሞተው ህያው አላህን ትተው ሙታንን የሚያመልኩ ሰዎች "ከአላህ ውጭ ያለን ማንንም ምንንም አትጥሩ፣ አትለምኑ ይህ ተግባራችሁ ሽርክ ነው። አላህ ብቻ ነው በሃቅ ሊመለክ የሚገባው" ሲባሉ አሻፈረን ይላሉ። ዘወትር በሶላታቸው: - "<u>አንተን ብቻ እናመልካለን። በአንተም ብቻ እንታገዛለን</u>" ማለታቸውን ይዘነጋሉ። በዚህ መልኩ ሲገሰጹም "ለምንድን ነው ታድያ ወደ ዶክተር የምትሄዱት" ሲሉ የሚመልሱ አሉ። የእኛ መልስ ግን "<u>ታድያ ለምንድን ነው ወደሞተ ዶክተር የማትሄዱት?</u>" የሚል ነው?

ሙታን አምላኪዎች ተውሒድን አልተረዱም። እንዲህ አይነት የማይገናኝ ጥያቄ እያነሱ ፈተና ውስጥ ይወድቃሉ። እውነትም ከኢብራሂም አለይሂ ሰላም መንገድ ከተውሒድ ያፈነገጠ ቂል ነው።

ሰዎች ሺርክን በሚገባ እንዳይጠነቀቁት የሚያደርጋቸው ጉዳዩን አርቀው መመልከታቸው ነው። እውነታው ግን ከምናስበው የቀረበ ነው። እስኪ ይህንን በርካታ ሙስሊሞች የሚያደምጡትን መንዙማ እንታዘብ፡-

"ያቀመረል መካ አሰላሙ አለይካ፣
<u>ልቤ ባንቱ በእርሶ ተመካ</u>"

ሌላ የሺርክ አዋጅ በስፋት ከሚደመጡ መንዙማዎች ውስጥ

"ሰለፍም ኸለፍም ማወረአል በህር፣
<u>በሁሉም ሸሸሁኝ አንድ እንኳን ሳይቀር፣</u>
ከዛፍ ከቅጠሉ በዝቶብኛል ነውር፣
እሜዳው ላይ ሆኜ ወድቄ በዱር፣
መግቢያ በር አጥቼ ታግቼ ባጥር፣
አልሄድ ወደፊት ወደ ኋላ አልበር፣
በቀኝ በግራዬ እሳት ገደል ባህር፣

<u>አቤት ጠራኋችሁ ጌቶቼ ዱስቱር፤</u>

<u>ረዳቴ ማን ነው ከናንተ በቀር።”</u>

አሁንም ሌላኛው የሽርክ መንዙማ እንዲህ ይላል

“ሀቢቢ ሀቢቢ ሀቢቢ፤

<u>መዲና ና ይበሉኝ።</u>”

ይህን አደጋ ተመልከቱ። **<u>የፍጡራን ሁሉ ረዳት አላህ ብቻ ነው</u>**። **<u>የፍጡራን ሁሉ መጠጊያ አላህ ብቻ ነው</u>**። **<u>አለምን የሚያስተናብረው አላህ ብቻ ነው</u>**። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِكَافٍ عَبۡدَهُۥۖ وَيُخَوِّفُونَكَ بِٱلَّذِينَ مِن دُونِهِۦۚ وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنۡ هَادٍ ﴾ الزمر: ٣٦.

“<u>አላህ ለባሪያው በቂ አይደለምን?</u> በነዚያ ከሱ ሌላ ባሉት (በሚያመልኳቸው) ያስፈራራሃል። አላህ የሚያጠመውንም ለርሱ ምንም አቅኚ የለውም።” [አዝ-ዙመር፡ 36]

አማኞች ሰላት ላይ ሆነው በተደጋጋሚ እንዲህ ሲሉ ቃል ይገባሉ፡-

﴿ إِيَّاكَ نَعۡبُدُ وَإِيَّاكَ نَسۡتَعِينُ ۝٥ ﴾ الفاتحة: ٥.

“<u>አንተን ብቻ እናመልካለን</u>። <u>አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን</u>።” [አል-ፋቲሐ፡ 5]

﴿ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡحَيِّ ٱلَّذِي لَا يَمُوتُ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِهِۦۚ وَكَفَىٰ بِهِۦ بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرًا ۝٥٨ ﴾ الفرقان: ٥٨.

“<u>በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ</u>። ከማመሰገንም ጋር አጥራው። በባሮቹ ኀጢአቶችም ውስጠ ዐዋቂነት በእርሱ ቢቃ።” [አል ፉርቃን፡ 58]

በየትኛውም ዘመን ከአላህ ውጭ የሚመለኩት ሁሉ ይህንን የሚያሟሉ አይደሉም። **<u>ሁሉም የአላህ ፍጡሮች ናቸው</u>፣ <u>ሁሉም ሟቾች ናቸው</u>፣ <u>ሁሉም ጠፍተው የልቅናና የልግሥና ባለቤት የሆነው የጌታ አላህ ፊትም ይቀራል</u>።**

አማኞች በአላህ ላይ ብቻ መመካት እንዳለባቸው አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ إِن يَنصُرۡكُمُ ٱللَّهُ فَلَا غَالِبَ لَكُمۡۖ وَإِن يَخۡذُلۡكُمۡ فَمَن ذَا ٱلَّذِي يَنصُرُكُم مِّنۢ بَعۡدِهِۦۗ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١٦٠ ﴾ آل عمران: ١٦٠.

“አላህ ቢረዳቸሁ ለእናንተ አሸናፊ የለም። ቢያዋርዳቸሁም ያ ከርሱ (ማዋረድ) በኋላ የሚረዳቸሁ ማን ነው? <u>በአላህ ላይ ብቻ ምእመናን ይመኩ</u>።” [አሊ-ዒምራን፡ 160]

ልክ እንዲሁ አላህ ብቻ ሊፈራ ሲገባው ከአላህ ውጭ ያሉ አካላትን መፍራት ለምሳሌ፡- ጂንን ይመታኛል፣ ሸሆች ልጂን ይቀሙኛል፣ ሃብቴን ያወድሙብኛል፣ እንዲህ ያደርጉኛል ብሎ መፍራት ሺርክ ነው።

የሺርክ ምሳሌዎች፡-

11.1. በውዴታ ማጋራት

ውዴታ ከአምልኮ ክፍሎች ውስጥ ነው። አምልኮታዊ ውዴታ ለአላህ ብቻ ነው የሚገባው። ከአላህ ውጭ ያሉትን ለአላህ ስንል ነው የምንወዳቸው። ለምሳሌ መላኢካዎችን ጅብሪልን ይመስል፣ ነብያትን፣ ነብዩ ሙሐመድን ﷺ ይመስል፣ ደጋጎችን

አቡ-በክር፣ ዑመር፣ ዑስማን፣ ዐልይ፣ ሰሃባዎች እና የመሳሰሉትን አማኞች የምንወዳቸው ለአላህ ስንል ነው።

ከሰዎች ግን በውዴታ የሚያጋሩ አሉ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ۗ ﴿١٦٥﴾ ﴾ البقرة: ١٦٥.

"ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን <u>አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አልሉ።</u> <u>እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው።</u>"
[አል-በቀራህ፡ 165]

እዚህ ጋር አንድ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አለ። ውዴታ ሁለት አይነት ነው።

- ✓ አምልኮታዊ ውዴታ፡- አምልኮታዊ ላይ አላህ ብቻ ነው ለዛቱ ሲባል ሊወደድ የሚገባው።
- ✓ ተፈጥሯዊ ውዴታ፡- አላህ የሰው ልጅ ላይ ስሜትና ባህሪን አድርጎለታል። ስለዚህ አንድ ወንድ ሚስቱን ቢወድ ሺርክ ሰራ አይባልም። አንድ ሚስትም ባሏን ብትወደው፣ ቤተሰብ ልጁን ቢወድ፣ ልጆች ወላጆቻቸውን ቢወዱ ሺርክ ሰሩ አይባልም። ምክንያቱም ይሄ ተፈጥሯዊ ህግ ነውና።

ለአላህ እና ለመልክተኛው ﷺ ያለንን ውዴታ የምንገልፀው እነሱ ያዘዙንን በመፈፀም፣ የከለከሉንን በመከልከል ነው። ስለ ውዴታ ከተነሳ አይቀር ከሱና ጋር የተቆራኘችውን የፈተና አንቀፅ እንያት።

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١.

"በላቸው፡- <u>'አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና</u>። ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።' " [አሊ-ዒምራን፡ 31]

11.2. በመታዘዝ ማጋራት

በመታዘዝ ማጋራት የሚለው ላይ መጠቆም የፈለግኩት በብዛት ከጭፍን ተከታይነት የሚመጣውንና ሰዎች ሸይኽ፣ ዑለማ ወይንም አሚር ብለው የወሰዱትን አካል አላህ ሃራም ያደረገውን ሃላል ሲያደርግላቸው አሚን ብለው ይቀበሉታል፣ አላህ ሃላል ያደረገውን ሃራም ሲልላቸው አሚን ብለው ይቀበሉታል። ከዛም አልፎ ይፈፅሙታል። ይሄ በአላህ ላይ ከማጋራት ውስጥ ነው። እስቲ የሚከተለውን ግልፅ መለኮታዊ ቃል በደምብ እንየው፡-

﴿ ٱتَّخَذُوٓاْ أَحۡبَارَهُمۡ وَرُهۡبَٰنَهُمۡ أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُوٓاْ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗاۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ سُبۡحَٰنَهُۥ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٣١ ﴾ التوبة: ٣١.

<u>"ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ</u>። (አላህ) ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።" [አት-ተውባህ፡ 31]

የተሰመረበትን በደምብ መመልከት ይሻል። የታዘዙት አላህ ሃላል ያደረገውን ሃላል በማድረግ፣ አላህ ሃራም ያደረገውን ሃራም በማድረግ፤ ያለ ማጋራት አንድን አምላክ ሊገዙ ነው። እነርሱ ግን ይህን ትተው ከአላህ ውጭ ያሉትን ተገዙ። ይህ ትምህርት በደንብ

እንዲገባን ታላቁ አስተማርያችን ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ዘንድ ዐዲይ ኢብን ሃቲም የተባለ ሰሃባ መጥቶ እሳቸው ይህንን አንቀፅ ሲያነቡ "**እነሱ እኮ አያመልኳቸውም**" አላቸው። ነብዩም ﷺ "**አላህ ሐራም ያደረገውን ሐላል ሲያደርጉላቸው አላህ ሐላል ያደረገውን ሐራም ሲያደርጉባቸው ይቀበሉ የለምን**?" አሉ። እርሱም "**አዎን**" አለ። እሳቸውም፡- "**<u>ታድያ ይህ እኮ ነው እነሱን ማምለክ ማለት</u>**" አሉ። ስለዚህ ከዚህም ኡማ ይህን ተግባር የሚፈፅም ካለ ተመሳሳይ ጥፋት (ማጋራት) ላይ ወድቋል ማለት ነው።

እንግዲህ ነብዩ ﷺ የሺርክን አይነቶች አንድም ሳይቀር እንዲህ ፍንትውና ብትንትን አድርገው አስረድተዋል።

12. የሺርክ አደጋዎች

12.1. ስራዎችን ሁሉ ያበላሻል

መቼም የምርጥም ምርጥ አለው። አላህ የአደምን ልጅ አልቆታል። ከአደም ልጆች ውስጥ ደግሞ መልክተኞቹንና ነብያቱን አብልጧል። ነብያቱና መልክተኞቹ ከሰዎች ጥቅምን ሳይፈልጉ ከአዛኙ አላህ የሚወርድላቸውን መለኮታዊ ራእይ ለፍጡራኑ ለማድረስ በድብቅም በግልፅም፣ በቀንም በማታም ደፋ ቀና ያሉና የለፉ ናቸው። የአላህን መልእክት ለማድረስ ሲሉ ስንት ከባድ አደጋ በህይወታቸው፣ በንብረታቸው፣ በቤተሰቦቻቸው ላይ የደረሰባቸውና ስንት መስዋእት የከፈሉ፣ ስንትና ስንት ገድል የፈፀሙ ናቸው።

ግን ይህ ሁሉ ከመሆኑ ጋር ሺርክ የሚባለውን ነገር ቢፈፅሙ ስራቸው ሁሉ እንደሚታበስ ጌታችን እንዲህ ሲል ነግሮናል፡-

﴿ ذَٰلِكَ هُدَى ٱللَّهِ يَهۡدِي بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦۚ وَلَوۡ أَشۡرَكُواْ لَحَبِطَ عَنۡهُم مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٨٨ ﴾
الأنعام: ٨٨.

“ይህ የአላህ መመሪያ ነው። በእርሱ ከባሮቹ የሚሻውን ሰው ይመራል። <u>ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር።</u>” [አል-አንዓም፡ 88]

የአላህ ባርያዎች ሆይ! ከአንቀፁ በፊት ልብ እንበል አላህ የነዚህን ነብያት ገድል ተናግሮላቸዋል። አላህ እዚህ ጋር <u>**ቢያጋሩም ኖሮ**</u> ይሰሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር ብሎ የጠቀሳቸው 18 ነብያት የሚከተሉት ናቸው፡-

አላህ ፍፁም ወዳጅ አድርጎ የያዛቸው ነብዩላህ **ኢብራሂም**-አልኸሊል፣ ነብዩላህ **ኢስሐቅ**፣ ነብዩላህ **ያዕቁብ**፣ ነብዩላህ **ኑሕ**፣ ነብዩላህ **ዳውድ**፣ ነብዩላህ **ሱለይማን**፣ ነብዩላህ **አዩብ**፣ ነብዩላህ **ዩሱፍ**፣ አላህ ያናገራቸው ነብዩላህ **ሙሳ**፣ ነብዩላህ **ሃሩን**፣ ነብዩላህ **ዘከርያ**፣ ከሳቸው በፊት ሞከሼ የሌላቸው ነብዩላህ **የሕያ**፣ በአላህ ፍቃድ ለምጣምን ያዳኑት፣ የሞተን የቀሰቀሱት የመርየም ልጅ ነብዩላህ **ዒሳ**፣ ነብዩላህ **ኢልያስ**፣ ካዕባን ከአባታቸው ኢብሂራም ጋር የገነቡት፣ ከአባታቸው ጋር ለአላህ ትዕዛዝ እጃቸውን በመስጠት ሊታረዱ የነበሩት ነብዩላህ **ኢስማዒል**፣ ነብዩላህ **የሰዕ**፣ ነብዩላህ **ዩኑስ**፣ ነብዩላህ **ሉጥ** ናቸው። እሺ እኛስ ከዚህ ምን ትምህርት እንወስዳለን?

ምንም አይነት ምድራዊ ጥቅምን ሳያልሙ “**አላህን ብቻ በብቸኝነት አምልኩ ከእርሱ ውጭ ያሉትን ማንንም ይሁን ምንንም ራቁ**” ፣ “**ወገኖቼ ሆይ! አላህን በብቸኝነት አምልኩ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም**” እያሉ ለተውሒድ የተዋደቁ የአላህ ምርጥ ባሮች እንዲህ ከተባሉ እኛስ ምን እንባል? ሌላ ምሳሌ አላህ ሊጨምርልን ነው። የአላህ ውድ፣ የነብያት ሁሉ መደምደሚያ፣ የታላቁ ምልጃ ባለቤት፣ ለአለማት እዝነት የተላኩ፣ የአደም ልጆች ሁሉ ምርጥ፣ ታላቁ የተውሒድ አስተማሪ፣ የኢብራሂም መንገድ ተከታይ፣ ነብዩ ሙሐመድ አበል ቃሲምን ﷺ አላህ እንዲህ አላቸው፡-

﴿ وَلَقَدۡ أُوحِيَ إِلَيۡكَ وَإِلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكَ لَئِنۡ أَشۡرَكۡتَ لَيَحۡبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٦٥ ﴾ الزمر: ٦٥.

"ብታጋራ ሥራህ በእርግጥ ይበላሻል። በእርግጥም ከከሓዲዎቹ ትሆናለህ በማለት ወደ አንተም ወደ እነዚያ ካንተ በፊት ወደነበሩትም በእርግጥ ተወርዷል።" [አዝ-ዙመር፡ 65]

ይሄ እኛን ለማስተማርያ እንጂ እሳቸው ከሺርክ የፀዱ ናቸው። እንዲያውም እኛን በአላህ ፍቃድ ከሺርክ ጨለማ አውጥተው ወደ ተውሒድ ብርሃን (በማስተማር) ሊመሩ የመጡ ናቸው። ግን ሱብሃነላህ ሺርክ ምን ያህል ከባድ እንደሆነና ስራን ሁሉ ድምጥማጡን እንደሚያጠፋ ከእንደዚህ አይነት ምሳሌዎች በላይ ምን ይምጣ?!!!

እስቲ ልብ ብለን እንመልከት ነብዩ ﷺ

- ✓ ለተውሒድ ሲሉ አገር ለቀው ተሰደው፣
- ✓ ሴት ልጆቻቸው ትዳራቸው ተፈቶ፣
- ✓ ጥርሳቸው ተሰብሮ፣
- ✓ እግራቸው ደምቶ፣
- ✓ ማንም ላይ ያልደረሰ ፈተና ደርሶባቸው፣
- ✓ ለአላህ በማመስገን ሰላት ላይ ከመቆማቸው ብዛት የተነሳ እግራቸው ተሰነጣጥቆ፣
- ✓ ስንት መከራዎችን ታግሰው፣
- ✓ ስንት መልካሞችን ሰርተው፣
- ✓ በሰሃባዎች አንደበት "(ከአላህ) የተላከበትን መልክት አድርሰሃል፣ አደራህን ተወጥተሃል፣ ኡማውን መክረሃል" ተብሎላቸው፣...

ይህ ሁሉ ከመሆኑ ጋር አላህ "**<u>ብታጋራ ስራህ ሁሉ ውድቅ ይሆናል</u>**" አላቸው። ታድያ የአላህ ባርያዎች ሆይ! እኛስ ምን ይዋጠን? **<u>ለምንድን ነው ለተውሒድ ትምህርት ተገቢው ትኩረት የማይሰጠው? ለምን ይሆን ስራን ሁሉ አመድ የሚያስገባውን ሺርክ ከምንም በላይ የማንጠነቀቀው?</u>**

አለማዊ ስሌት።

በሂሳብ ትምህርት እንደሚታወቀው ማባዛት የሚባል ነገር አለ። ማንኛውም ቁጥር በዜሮ ከተባዛ እራሱን ዜሮን ነው የሚሰጠው። ለምሳሌ፦

1 X 0 = 0

100 X 0 = 0

100,000 X 0 = 0

1,000,000 X 0 = 0

1,000,000,000 X 0 = 0

1,000,000,000,000 X 0 = 0

የሺርክም መጨረሻው ይህ ነው። ሰውየው እምነቱ ሳይስተካከል ቢለፋ ቢለፋ መጨረሻ ላይ ይኸው ለፍቶ መና መሆን ነው። ሰውየው ሺርክ ሳይቀላቀልበት ተሰርቶ የተቀመጠ መልካም ስንትና ስንት ምንዳ ያለው ስራ ቢኖረውም ትልቁን ሺርክ ሲቀላቅልበት እንዲሁ **<u>ዜሮ</u>** ያስቀረዋል። ሺርክ ስራችንን አመድ እንዳያደርግብን ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ ግድ ይላል። በእምነት መካድ ምን እንደሚያስከትል አላህ እንዲህ ይለናል፦

﴿ وَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلۡإِيمَٰنِ فَقَدۡ حَبِطَ عَمَلُهُۥ وَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٥ ﴾ المائدة: ٥.

"ከእምነትም የሚመለሰ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው።" [አል-ማኢዳህ፡ 5]

አላህ ሆይ! ወደ ውዱ የተውሒድ መንገድ ምራን፣ ከእርኩሱ ሺርክ እኛንም ዝርያዎቻችንንም ጠብቀን። በተውሒድ መንገድ ላይ ግደለን።

12.2.አብዛኛዎቹ የጠፉት ኢጋሪ ስለነበሩ ነው

ሺርክ የአላህን ቁጣ መከናነቢያና የመጥፊያም ሰበብ መሆኑን አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَكُمْ ثُمَّ رَزَقَكُمْ ثُمَّ يُمِيتُكُمْ ثُمَّ يُحْيِيكُمْ ۖ هَلْ مِن شُرَكَآئِكُم مَّن يَفْعَلُ مِن ذَٰلِكُم مِّن شَىْءٍ ۚ سُبْحَـٰنَهُۥ وَتَعَـٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٤٠﴾

"አላህ ያ የፈጠራችሁ፣ ከዚያም ሲሳይን የሰጣችሁ፣ ከዚያም የሚገድላችሁ፣ ከዚያም ሕያው የሚያደርጋችሁ ነው። ከምታጋሯቸው ውስጥ ከዚህ ነገር አንዳችን የሚሠራ አለን? ለአላህ ጥራት ይገባው። (በእርሱ) ከሚያጋሩትም ሁሉ ላቀ።

ظَهَرَ ٱلْفَسَادُ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ بِمَا كَسَبَتْ أَيْدِى ٱلنَّاسِ لِيُذِيقَهُم بَعْضَ ٱلَّذِى عَمِلُوا۟ لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴿٤١﴾

የሰዎች እጆች በሠሩት ኃጢአት ምክንያት የዚያን የሠሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና በባሕር ተገለጠ፤ (ተሰራጨ)። እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና፤

قُلْ سِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَٱنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَـٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلُ ۚ كَانَ أَكْثَرُهُم مُّشْرِكِينَ ﴿٤٢﴾ ﴾

الروم: ٤٠ – ٤٢.

«በምድር ላይ ሺዱ የእነዚያንም በፊት የነበሩትን ሰዎች መጨረሻ እንዴት እንደነበረ ተመልከቱ» በላቸው። <u>አብዛኞቻቸው አጋሪዎች ነበሩ።"</u> [አል ሩም 40-42]

12.3. ሺርክ ዘላለማዊ ህይዎትን ያጠፋል

አላህ በእሱ ላይ እያጋሩ የሞቱ ሰዎች መኖርያቸው የጀሃነም እሳት ውስጥ እንደሆነ ብሎም መውጫ እንደሌላቸው እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ لَقَدۡ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَۖ وَقَالَ ٱلۡمَسِيحُ يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمۡۖ إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢ ﴾ المائدة: ٧٢.

እነዚያ "<u>አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው</u>" ያሉ <u>በእርግጥ ካዱ</u>። አልመሲህም አለ፡- "የእስራኤል ልጆች ሆይ! <u>ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።"</u> <u>እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።"</u> [አል-ማኢዳህ፡ 72]

12.4. ሺርክ ሰላምን ያሳጣል

ነብዩላህ ኢብራሂም ለተላኩባቸው አጋሪያን ምን እንዳላቸው ጌታችን እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ وَكَيۡفَ أَخَافُ مَآ أَشۡرَكۡتُمۡ وَلَا تَخَافُونَ أَنَّكُمۡ أَشۡرَكۡتُم بِٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ عَلَيۡكُمۡ سُلۡطَٰنٗاۚ فَأَيُّ ٱلۡفَرِيقَيۡنِ أَحَقُّ بِٱلۡأَمۡنِۖ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ٨١ ﴾

“<u>በእናንተ ላይ በእርሱ ማሰረጃን ያላወረደበትን እናንተ ማጋራታችሁን የማትፈሩ ሰትሾኑ የምታጋሩትን (ጣዖታት) እንዴት እፈራለሁ! የምታውቁም ብትሾኑ ከሁለቱ ክፍሎች በጸጥታ ይበልጥ ተገቢው ማንኛው ነው? (አለ)።</u>”

﴿ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَمۡ يَلۡبِسُوٓاْ إِيمَٰنَهُم بِظُلۡمٍ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلۡأَمۡنُ وَهُم مُّهۡتَدُونَ ٨٢ ﴾ الأنعام: ٨١ – ٨٢.

<u>እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ</u> እነዚያ ለእነርሱ <u>ጸጥታ (ሰላም)</u> አላቸው። እነሱም የተመሩ ናቸው። [አል-አንዓም፡ 81-82]

12.5. የሺርክ አደጋ አስከፊነት

የሺርክ አደጋው እጅግ ዘግናኝ ስለሆነ ነው ነብዩሏህ ኢብራሂም እኔንም ልጆቼንም ጣኦት ከማምለክ ጠብቀኝ ማለታቸው።

የሺርክን አስከፊነት ለመረዳት ከሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ አንዱ **<u>አላህ ፍፁም ወዳጅ አድርጎ የያዛቸው</u>**፣ የነብያት አባት፣ ነብዩሏህ ኢብራሂም እኔንም ልጆቼንም ከሺርክ (ከጣኦት አምልኮ) አርቀን ማለታቸው ብቻ ይበቃል። ነብዩሏህ ኢብራሂም (አለይሂ ሰላም) ጌታቸውን ከሺርክ እንዲጠብቃቸው እንደለመኑት አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ رَبِّ ٱجۡعَلۡ هَٰذَا ٱلۡبَلَدَ ءَامِنٗا وَٱجۡنُبۡنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعۡبُدَ ٱلۡأَصۡنَامَ ٣٥ رَبِّ إِنَّهُنَّ أَضۡلَلۡنَ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلنَّاسِۖ ٣٦ ﴾ إبراهيم: ٣٥ – ٣٦.

ኢብራሂምም ባለ ጊዜ (አስታውሰ) “ጌታዬ ሆይ! ይህንን አገር (መካን) ጸጥተኛ አድርገው። <u>እኔንም ልጆቼንም ጣዖታትን ከመገዛት አርቀን</u>። ጌታዬ ሆይ! እነርሱ (ጣዖታት) ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና።” [ኢብራሂም፡ 35-36]

ዛሬ አንዳንድ “ዘመናዊ ነን፣ ሰልጥነናል፣ የዱንያ ትምህርት አለን፣ የከተማ ሰዎች ነን” የሚሉ ሸይጧን እና ነፍስያ የተጫወቱባቸው ግለሰቦች “ዘመን ሰልጥኗል” ፣ “እንደኔ የተማሩትን ሽርክ አያስጋንም ወይንም የዚህን ቃል ፅንሰ ሃሳብ የመሰለ የሚናገሩ” ፣ “ሽርክ እኮ ገጠር ያሉ ሰዎች ላይ ነው ያለው” እና የመሳሰለውን ምክንያት በመደርደር የሽርክን ነገር አቅልለው ሲያዩ ይታያሉ። ለነዚህ የዲን እውቀት አልባ ለሆኑ ሰዎች የምንላቸው መጀመርያ ዲንን ጠንቅቃቸሁ እወቁ። አላህ ፍፁም ወዳጅ አድርጎ የያዘው ነብዩላህ ኢብራሂም ***“እኔንም ልጆቼንም ጣዖትን ከመገዛት አርቀን”*** ካለ እኛ ማን ነንና ሽርክን ለነፍሳችን እና ለቤተሰባችን የማንሰጋው? አለማወቅ ከባድ አደጋ ነው። እጥፍ ድርብ የሆነው ከባድ አደጋ ደግሞ እውቀት እንደሌለንም አለማወቃችን ነው።

12.6. ሺርክ ዘላለማዊ የጀሀነም ማገዶ ያደርጋል

ለዚህም ማስረጃው አጋሪያን ጀነት እንደማይገቡና ዘላለማዊ መኖርያቸው ጀሐነም እንደሆነ አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢﴾ المائدة: ٧٢.

“እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።” [አል-ማኢዳህ: 72]

የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ይሉናል፡- “**ከአላህ ሌላ ያለን አካል (አጋርን) እየጠራ (እያመለከ) የሞተ እሳት ገባ።**” (ቡኻሪ ዘግበውታል)

12.7. ሺርክ ከእስልምና ውጭ ያደርጋል

ለዚህም ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ንግግር ነው።

﴿ وَلَا تَدۡعُ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكَ وَلَا يَضُرُّكَۖ فَإِن فَعَلۡتَ فَإِنَّكَ إِذٗا مِّنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٠٦ ﴾ يونس: ١٠٦

"ከአላህም በቀር የማይጠቅምህንና የማይጎዳህን አትገዛ (አታምልክ)። <u>ብትሠራም (ከአላህ ውጭ ያሉትን ብታጋራም) አንተ ያን ጊዜ ከበደለኞቹ (ከአጋሪዎች) ትሆናለህ</u>" (ተብያለሁ በላቸው) ። [ዩኑስ፡ 106]

ታላቁ የተፍሲር ሊቅ ኢብኑ ጀሪር አጥ-ጦበሪይ እና ሌሎችም እንዳብራሩት "**<u>ከበደለኞች</u>**" የሚለው ቃል **<u>ከአጋሪዎች</u>** ማለት እንደሆነ ጠቁመዋል። በዚህም የተነሳ ነው የኢስላም ሊቃውንቶች ሽርክ ከእስልምና ያስወጣል የሚሉት።

12.8. ሺርክ ህይወትና ገንዘብን ሀላል ያደርጋል

የአላህ መልክተኛ ﷺ አንድ ሰው ገንዘቡ እና ህይዎቱ በምን መንገድ ጥበቃ እንደሚነሳበት እንዲህ ሲሉ ይነግሩናል።

"ሰዎችን እንድታገላቸው ታዝዣለሁ። ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ እውነተኛ አምላክ የለም ብለው እስኪመሰክሩ ድረስ። ይህን ካሉ ነፍሳቸው፣ ገንዘባቸው የተጠበቀች ትሆናለች። የእስልምና መብት ሲቀር (የገደለ መገደልን ይመስል) ...."

12.9. ሺርክ ምድርን ያበላሻል፣ ያወድማል

በዋናነት ምድር የምትበላሸው በሽርክ ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይለናል፡-

﴿ وَلَا تُفۡسِدُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ بَعۡدَ إِصۡلَٰحِهَا وَٱدۡعُوهُ خَوۡفٗا وَطَمَعًاۚ إِنَّ رَحۡمَتَ ٱللَّهِ قَرِيبٞ مِّنَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٥٦ ﴾ الأعراف: ٥٦.

<u>በምድርም ውሰጥ ከተበጅች (ከተሰተካከለች) በኋላ (በአላህ ላይ በማጋራት) አታበላሹ።</u> <u>ፈርታችሁና ከጅላችሁም ተገዙት።</u> <u>የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ቅርብ ነውና።</u> አል-አዕራፍ 56

ምድር የምትሰተካከለው ነብያት ይዘውት በመጡት መልክት ነው። ነብያት ይዘውት የመጡት መልክት ደግሞ ተውሒድ ነው። ዛሬ አለም ሰልጥኗል ይባላል ነገር ግን አብዛኛው ሰው ብቸኛውን ፈጣሪ በብቸኝነት ያመልካል ወይ? ብቸኛውን ሲሳይ እና ሌሎች ነገሮች ለጋሽ የሆነውን ብቸኛ አምላክ ያመሰግነዋል ወይ? ፈጣሪውን ይፈራል ወይ? ፈጣሪውን ያውቀዋል ወይ? አላህ ለአለማት እዝነት አድርጎ በላካቸው ነብዩ ﷺ መልክት ይሰራበታል (ይቀበለዋል) ወይንስ ስሜቱን ተከትሎ ያልታዘዘውን ይሰራል? እና የመሳሰለውን ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አሳዛኝ ነው የሚሆነው። ዝሙት፣ ግብረሰዶም፣ ቁማር፣ ወለድ መስፋፋታቸው ምድርን ካበላሸ፣ በአላህ ላይ ማጋራት እማ የባሰ ምድርን ማበላሸት ነው የሚሆነው። አላህ ምድርን ከማበላሸት ይጠብቀን።

13. በችግር ጊዜ አላህን እያመለኩ በሰላሙ ጊዜ ማጋራት ተውሒድ አይባልም።

ከነብዩ ﷺ ጋር የተዋጉት የመካ አጋሪያን በችግር ጊዜ አላህን ብቻ ይጠሩ ነበር። ሆኖም ግን ይህ **<u>በችግር ጊዜ ብቻ እሱን (አላህን ብቻ) መለመናቸው አማኝ አላስባላቸውም</u>**። አላህ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴿٦٥﴾ ﴾ العنكبوت: ٦٥.

<u>"በመርከቦች ውሰጥ በተሳፈሩ ጊዜም</u> <u>አላህን መገዛትን (አምልኮን) ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ሽነው ይጠሩታል።</u> <u>ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ።</u>" [አል ዐንከቡት፡ 65]

በዘመናችን ሺርክ ላይ የወደቁ ሰዎች ግን ጥፋታቸው ቦታና ጊዜ እንኳን አይመርጥም። ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ በሰላሙም ጊዜ በችግርም ጊዜ ከአላህ ውጭ ላሉ አካላት አምልኮን ሲፈፅሙ ይታያሉ። ቀናትን ማምለክ አስመልክቶ እንደ አካባቢው ቢለያይም ዋና ዋና የሆኑት የሚከተሉት ናቸው። ለምሳሌ፦ ሰኞ የኢስነይን፣ ማክሰኞ የመገርገቢያው፣ እሮብ የጀይላኒ፣ ሃሙስ የነቢ ኢድሪስ፣ ቅዳሜ የሰይድና ኸድር፣ እሁድ የፈቂህ አሊ ሙዝ ወዘተ በማለት ያለገደብ ሺርክ ይፈፅማሉ። የተፈጠሩት ግን በሰላሙም በችግሩም ጊዜ አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ነው።

14. "የአባቶቻችን መንገድ"

አብዛኛዎቹ ህዝቦች መልእክተኞች ምን ይዘውላቸው እንደመጡ ገብቷቸዋል። ሆኖም ግን መልክቱን ላለመቀበል ካገዳቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የአባቶቻቸውን ውርስ ለመተው አለመፍቀዳቸው ነው። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ قَالُوٓاْ أَجِئۡتَنَا لِنَعۡبُدَ ٱللَّهَ وَحۡدَهُۥ وَنَذَرَ مَا كَانَ يَعۡبُدُ ءَابَآؤُنَاۖ فَأۡتِنَا بِمَا تَعِدُنَآ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ٧٠ ﴾ الأعراف: ٧٠.

«አላህን ብቻውን እንድንገዛ አባቶቻችንም ይገዙት የነበረውን (አማልክት) እንድንተው መጣህብን? ከውነተኞች ከሆንክ የምታስፈራራብንን (ቅጣት) አምጣብን» አሉ። [አል-አዕራፍ፡ 70]

አባቶቻችንን ተምሳሌት ልናደርግ የሚገባው በተውሒድ፣ በሱንና በሐቅ ላይ ሲሆን ብቻ ነው። የአላህ ነብይ ዩሱፍ ምን እንዳሉ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَٱتَّبَعْتُ مِلَّةَ ءَابَآءِىٓ إِبْرَٰهِيمَ وَإِسْحَٰقَ وَيَعْقُوبَ ۚ مَا كَانَ لَنَآ أَن نُّشْرِكَ بِٱللَّهِ مِن شَىْءٍ ۚ ذَٰلِكَ مِن فَضْلِ ٱللَّهِ عَلَيْنَا وَعَلَى ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَشْكُرُونَ ﴿٣٨﴾

«የአባቶቼንም የኢብራሂምንና የኢስሐቅን፣ የያዕቆብንም ሃይማኖት ተከትያለሁ። <u>ለእኛ በአላህ ምንንም ማጋራት አይገባንም ያ (አለማጋራት) በእኛ ላይና በሰዎቹ ላይ የአላህ ችሮታ ነው</u>። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም።

የታዘዝነው ከሽርክ እና ከቢድዐ የፀዱትን የቀደምቶቹን የነብዩ ﷺ ፣ ሰሃባዎቻቸው፣ እና ሰለፉነ ሷሊሁንን መንገድ እንድንከተል ነው።

15. አማኞቹ ጂኖች በአላህ ላይ አናጋራም ማለታቸው።

አማኝ ጂኖች በነብዩ ሙሐመድ ﷺ ላይ የወረደውን የአላህ ቃል ቁርአን ከሰሙ በኋላ በጌታችን አላህ ላይ አናጋራም በማለት እንዲህ ሲሉ መመስከራቸውን ጌታችን አላህ ይነግረናል፡-

﴿ قُلْ أُوحِىَ إِلَىَّ أَنَّهُ ٱسْتَمَعَ نَفَرٌ مِّنَ ٱلْجِنِّ فَقَالُوٓا۟ إِنَّا سَمِعْنَا قُرْءَانًا عَجَبًا ﴿١﴾ يَهْدِىٓ إِلَى ٱلرُّشْدِ فَـَٔامَنَّا بِهِۦ ۖ وَلَن نُّشْرِكَ بِرَبِّنَآ أَحَدًا ﴿٢﴾ ﴾ الجن: ١ – ٢.

"(ሙሐመድ ሆይ!) በል፡ እነሆ ከጂን የሆኑ ጭፈሮች (ቁርአንን) አዳመጡ። «እኛ አስደናቂ የሆነን ቁርአን ሰማንም» አሉ ማለት ወደእኔ ተወረደ። "ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን) ። በእርሱም አመንን። <u>በጌታችንም አንድንም አናጋራም።</u>" [አል ጂን፡ 1-2]

ቀደም ብለን እንዳሳለፍነው ጂኖችም ልክ እንደ ሰው ልጅ አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው የተፈጠሩት። ልክ ከሰው ልጅ አማኝ፣ ከሃዲ፣ አመፀኛ እንዳለ ሁሉ ከነሱም ውስጥ እንዲሁ አማኝ፣ ከሃዲ እና አመፀኞች አሉ። አማኞቹ ጂኖች ይኸው "<u>በጌታችን ላይ</u>

አናጋራም" ማለታቸውን አላህ ነገረን። በሌላ ቦታ ላይ አማኝ ጂኖች ለህዝቦቻቸው ነብዩን ﷺ እንዲከተሉ እንዲህ ሲሉ ጥሪ ማቅረባቸውን አላህ እንደሚከተለው ይነግረናል፦

﴿ يَٰقَوۡمَنَآ أَجِيبُواْ دَاعِيَ ٱللَّهِ وَءَامِنُواْ بِهِۦ يَغۡفِرۡ لَكُم مِّن ذُنُوبِكُمۡ وَيُجِرۡكُم مِّنۡ عَذَابٍ أَلِيمٖ ٣١ وَمَن لَّا يُجِبۡ دَاعِيَ ٱللَّهِ فَلَيۡسَ بِمُعۡجِزٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَيۡسَ لَهُۥ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءُۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٣٢ ﴾ الأحقاف: ٣١ – ٣٢.

"ወገኖቻችን ሆይ! የአላህን ጠሪ (ነብዩ ሙሐመድን ﷺ) ተቀበሉ። በእርሱም እመኑ[7] (አላህ) ከሃጢአቶቻችሁ ለእናንተ ይምራልና። ከአሳማሚ ቅጣትም ያድናችኋልና። የአላህንም ጠሪ (የአላህን መልክተኛ ﷺ) የማይቀበል ሰው በምድር ውስጥ የሚያመልጥ አይደለም። ከእርሱም ሌላ ለእርሱ ረዳቶች የሉትም። እነዚያ በግልጽ ስሕተት ውስጥ ናቸው (አሉ)።" [አል አሕቃፍ፡ 31-32]

16. አላህ በላጭ ነውን? ወይስ ያ የሚያጋሩት?

ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን?

﴿ قُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ وَسَلَٰمٌ عَلَىٰ عِبَادِهِ ٱلَّذِينَ ٱصۡطَفَىٰٓۗ ءَآللَّهُ خَيۡرٌ أَمَّا يُشۡرِكُونَ ٥٩ ﴾ النمل: ٥٩.

([7]) በመልክተኞች ማመን ከእምነት ክፍሎች ውስጥ አንዱ ስለሆነ ነው። ለዚህም ነው በእርሱም (በነብዩ ሙሐመድ ﷺ) እመኑ በማለት አማኝ ጂኖች ለወገኖቻው ጥሪ ያደረጉት። ነብዩ ﷺ ይዘው የመጡትን የተውሒድ ጥሪ መቀበል ወንጀሎችን ሁሉ ሲያስምር (እስልምና ከእሱ በፊት የነበረውን ያብሳልና)። የአላህ መልክተኛ ﷺ በሄዱበት መንገድ ሄዶ የሞተ ሰው ከአሳማሚ ቅጣት አላህ እንደሚያድነው ከዚህ አንቀፅ እንረዳለን።

"(ሙሐመድ ሆይ) በል፦ ምስጋና ለአላህ ይገባው። በእነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሰላም ይውረድ። አላህ በላጭ ነውን? ወይስ ያ የሚያጋሩት? ።" [አን-ነምል 59]

﴿ أَمَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَنۢبَتْنَا بِهِۦ حَدَآئِقَ ذَاتَ بَهْجَةٍ مَّا كَانَ لَكُمْ أَن تُنۢبِتُوا۟ شَجَرَهَآ ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ بَلْ هُمْ قَوْمٌ يَعْدِلُونَ ﴿٦٠﴾ ﴾ النمل: ٦٠.

"ወይም ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረና ከሰማይም ለእናንተ ውሃን ያወረደው (ይበልጣል ወይስ የሚያጋሩት?) በእርሱም ባለውበት የኾኑትን የታጠሩ አትክልቶችን ዛፍዋን ልታበቅሉ ለናንተ ችሎታ ያልነበራችሁን አበቀልን። ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? (የለም)። ግን እነርሱ (ከእውነት) የሚያዘነብሉ ሕዝቦች ናቸው።" [አን-ነምል፡ 60]

﴿ أَمَّن جَعَلَ ٱلْأَرْضَ قَرَارًا وَجَعَلَ خِلَٰلَهَآ أَنْهَٰرًا وَجَعَلَ لَهَا رَوَٰسِىَ وَجَعَلَ بَيْنَ ٱلْبَحْرَيْنِ حَاجِزًا ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٦١﴾ ﴾ النمل: ٦١.

"ወይም ያ ምድርን መርጊያ ያደረገና በመካከሏም ወንዞችን ያደረገ፣ ለእርሷም ጋራዎችን ያደረገ፣ በሁለቱ ባሕሮችም (በጣፋጩና በጨው ባሕር) መካከል ግርዶን ያደረገ (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት)? ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።" [አን-ነምል 61]

﴿ أَمَّن يُجِيبُ ٱلْمُضْطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكْشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجْعَلُكُمْ خُلَفَآءَ ٱلْأَرْضِ ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴿٦٢﴾ ﴾ النمل: ٦٢.

"ወይም ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣ መከራንም የሚያስወግድ፣ በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደረጋችሁ፣ (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትንም አትገሠጹም።" [አን-ነምል፡ 62]

﴿ أَمَّن يَهۡدِيكُمۡ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَمَن يُرۡسِلُ ٱلرِّيَٰحَ بُشۡرَۢا بَيۡنَ يَدَيۡ رَحۡمَتِهِۦٓۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ تَعَٰلَى ٱللَّهُ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٦٣ ﴾ النمل: ٦٣.

"ወይም ያ በየብስና በባሕር ጨለማዎች ውስጥ የሚመራችሁ <u>ነፋሶችንም ከዝናቡ በፊት አብሳሪ ኾነው የሚልክ</u> (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? አላህ (በእርሱ) ከሚያጋሩዋቸው ሁሉ ላቀ።" [አን-ነምል፡ 63]

﴿ أَمَّن يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَمَن يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٦٤ ﴾ النمل: ٦٤.

"ወይም ያ መፍጠርን የሚጀምር <u>ከዚያም የሚመልሰው</u> <u>ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ</u> አምላክ (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሯቸው?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? «እውነተኞች እንደኾናችሁ፤ አስረጃችሁን አምጡ» በላቸው።" [አን-ነምል፡ 64]

17. አላህ የአደም ልጆችን ሁሉ ከሺርክ፣ ከሰይጣን አምልኮ እንዲርቁ መክሯል።

አላህ የሰው ልጆችን ከእርሱ እዝነት የተባረረውን ሰይጣን እንዳያመልኩ፣ እሱ የሚሾምላቸውን ባዕድ አምልኮ እንዳያመልኩ እንዲህ ሲል መክሯል

﴿ أَلَمۡ أَعۡهَدۡ إِلَيۡكُمۡ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ أَن لَّا تَعۡبُدُواْ ٱلشَّيۡطَٰنَۖ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ٦٠ ﴾ يس: ٦٠.

"የአደም ልጆች ሆይ! ሰይጣንን አትገዙ[8]፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና በማለት ወደ እናንተ አላዘዝኩምን?" [ያሲን፡ 60]

18. ከኢጋሪያን መገለጫ ውስጥ አላህ በብቸኝነት ሲወሳ ልባቸው መሸማቀቁ ነው።

አማኞች የሚደሰቱት ስለ አላህ ሲወሳ ነው። በጣም መስማት፣ ማየት የሚዘገንናቸው በአላህ ላይ ሲጋራ፣ የነብዩ ﷺ ሱና ሲጣስና ቢድዐ ሲነግስ ነው። ውስጥ አዋቂው አላህ የእነዛ በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑ ሰዎች ባህሪ ምን እንደሆነ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ وَإِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَحۡدَهُ ٱشۡمَأَزَّتۡ قُلُوبُ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِۖ وَإِذَا ذُكِرَ ٱلَّذِينَ مِن دُونِهِۦٓ إِذَا هُمۡ يَسۡتَبۡشِرُونَ ٤٥ ﴾ الزمر: ٤٥.

"አላህም ብቻውን በተወሳ ጊዜ የእነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ሰዎች ልቦች ይሸማቀቃሉ፤ (ይደነብራሉ)። እነዚያም ከእርሱ ሌላ የሾኑት (ጣዖታት) በተወሱ ጊዜ እነርሱ ወዲያውኑ ይደሰታሉ።" [አዝ-ዙመር፡ 45]

ይህ እንግዲህ በጣም ከባድ አደጋ ነው። አገራችን ላይ ከአላህ ውጭ የሚመለኩት ሲወሱ በጣም በመነሸጥ እጣኑ እየተጨሰ፣ ጫት እየተቃመ፣ "**መደድ ያ ሪጃለላህ (እናንተ የአላህ ወንዶች ተጨማሪ እርዳታን ለግሱን)**" ፣ **"ያረሱለላህ አልመደድ (የአላህ መልክተኛ ሆይ! እርዱን)"** ፣ **"የበረናው ደግዬ እርዱኝ አባብዬ"** እየተባለ፣ ወደ ግራ ወደ ቀኝ

([8]) የሰው ልጆችን በጠቅላላ በማጥመም ላይ የሚገኙት ሰይጣን እና ሰራዊቶቹ ናቸው። የሰው ልጅ ደጋጎችን፣ መላእክትን፣ ነብያትን፣ ነፍሱን፣ እንስሳትን፣ ዛፍን፣ ጨረቃን፣ ኮከብን፣ ፀሀይን ወዘተ ሲያመልክ ዋናው ጎትጓችና ቀስቃሽ ከአላህ እዝነት የተባረረው ሰይጣን ነው። እሱንም እሺ እንዳንለው እና እንዳንገዛው ቸሩ አዛኝ አምላክ ይኸው በዚህ አንቀፅ መክሮናል። አላህ ከሰይጣን ወጥመዶች ይጠብቀን።

እየተወዛወዙ፣ ድቤ እየተመታ በስሜት ሲጋልቡ ይታያል። አላህ በብቸኝነት ሲወሳ ግን ይጨነቃቸዋል።

“አቡል ጀበል የአደም ጭቃ ነው እጁን ያጠቀረው፣ (የአባታችን አደም አፈጣጠር ላይ) አቡል ጀበል ነበር ያሳመረ ሌሎች ሲያቦኩ”፣ “እገሌ የሚባሉት ሸይኽ መሬቱን ቆርሰው ወሰዱት”፣ “የእንትኑ ሸይኽ ልጅ ላማራት ልጅ ሰጧት”፣ “እገሌ ሸይኽ እህል አዘነቡ”፣ “እገሌ ሸይኽ ከሙሪዳቸው አንዱ ሐጅ መሄድ ፈልጎ ጋቢያቸው ውስጥ አስገብተው ባንዴው ሐረም ጣሉት”፣ “ሸይኽ ሁሴን ጂብሪል እንዲህ ብለው ፈረዱ፣ ሸይኽ ሁሴን ጅብሪል የተናገሩት ሁሉ አንድም አልቀረም ተከሰተ[9]” እና የመሳሰለውን እያሉ **የክህደት፣ በአላህ የማጋራት፣ የቅጥፈትና፣ የዝባዝንኬ ወሬና ተግባር እየፈፀሙ** በዚህ እርኩስ ተግባራቸው ላይ ደግሞ ሲደሰቱ ይታያሉ።

19. ሺርክና ሙሽሪኮች በምሳሌ፡-

19.1. የዝንብ ምሳሌ፡-

ብቸኛው ፈጣሪ አንድ አምላክ አላህ ነው። አዛኙ አላህ በምሳሌ መልክ የሰው ልጆችን እንዲህ ሲል ይገስፃል።

([9]) ትንቢት ሸህ ሁሴን ጂብሪል እየተባለ በሃገራችን መፀሃፍ ሳይቀር ታትሞ ይሸጣል። አላህ ብቻ ነው የሩቅን ሚስጥር የሚያውቀው። የአላህ መልክተኛ ﷺ **የነገን አውቃለሁ ባይ ጋር የሄደ የ40 ቀን ሰላቱ እንደማይቀበለው** ነግረውናል። አሁንም የአላህ መልክተኛ ﷺ **የነገን አውቃለሁ ባይ ያለውን እውነት ነው ብሎ የተቀበለ በእሳቸው ላይ በተወረደው የካደ መሆኑን** ነግረውናል። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ አገራችን ላይ የሸህ ሁሴን ትንቢት እውነት ነው፣ ያሉት አንድም የቀረ የለም ብለው ደፍረው ወደ ኩፍር መንደር የሚንደረደሩም አልጠፉም። አላህ እኛንም ዝርያዎቻችንንም ከሽርክ ይጠብቀን።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَٱسْتَمِعُواْ لَهُۥٓ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخْلُقُواْ ذُبَابًا وَلَوِ ٱجْتَمَعُواْ لَهُۥ ۖ وَإِن يَسْلُبْهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيْـًٔا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ ٱلطَّالِبُ وَٱلْمَطْلُوبُ ﴿٧٣﴾ ﴾ الحج: ٧٣.

"እናንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ። ለእርሱም አድምጡት። <u>እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው ዝንብን ፈጽሞ አይፈጥሩም። እርሱን (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳን (አይችሉም)። አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉትም። ፈላጊውም ተፈላጊውም (ጠያቂም ተጠያቂም) ደከሙ።" [አል ሐጅ፡ 73]

እንግዲህ የአእምሮ ባለቤቶች እስኪ አንቀፁን በአላህ ፍቃድ በደንብ ለማብራራት እንሞክር።

ብቸኛው ፈጣሪ አላህ ብቻ ነው። አላህ ማለት የመላእክት፣ የአርሹ፣ የኩርሲዩ፣ የሰው ልጆች፣ የጂኖች፣ የሰማያትና በውስጡ ያሉ ሁሉ፣ የምድርና በውስጡ ያለው ሁሉ <u>ፈጣሪ</u>፣ ተንከባካቢ፣ ገዳይ፣ ብቻውን ቀሪ ነው። "<u>**አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው።"**</u>

﴿ قُلِ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ شَىْءٍ وَهُوَ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّٰرُ ﴿١٦﴾ ﴾ الرعد: ١٦.

"<u>አላህ ሁለመናውን ፈጣሪ ነው</u>። እርሱም አንዱ አሸናፊው ነው በል።" [አር-ረዕድ፡ 16]

﴿ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ ۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ خَٰلِقُ كُلِّ شَىْءٍ فَٱعْبُدُوهُ ۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ وَكِيلٌ ﴿١٠٢﴾ ﴾ الأنعام: ١٠٢.

"ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። <u>ከእርሱ በቀር በሀቅ የሚመለክ አምላክ የለም። ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው። ስለዚህ ተገዙት።</u> እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው።"
[አል-አንዓም፡ 102]

ዝንብ በጣም ትንሽ ከሚባሉት ፍጥረታት ውስጥ ናት። ከመሆኑም ጋር አላህ **<u>ከእርሱ ውጭ የሰው ልጆች የሚያመልኳቸው የሆኑት በጠቅላላ ቢሰበሰቡ ዝንብን ሊፈጥሩ እንደማይችሉ ገለፀ</u>**።

እንደሚታወቀው የሁዳዎች ዑዘይርን ክርስትያኖች ዒሳን የአላህ ልጅ ብለው አምልኮን ለእነርሱ ይፈፅማሉ። ከዚህም ባለፈ ጂብሪልን፣ ሚካኢልን፣ ነብዩ ሙሐመድን ﷺ ፣ ዐልይን፣ ሁሴንን፣ ፋጢማን፣ ጂኖችን፣ የተለያዩ እንስሳትን፣ ድንጋዮችን ዛፎችን፣ ፀሀይና ጨረቃን፣ እንደ ዐብዱል ቃዲር ጀይላኒ፣ አሕመድ አልበደዊ፣ ኑር ሁሴን፣ አብሬት፣ ቃጥባሬ፣ ዐሊ ጎንደር፣ አባድርና የመሳሰሉ ከዘመናት በፊት የሞቱ ሰዎችን፣ በህይወት ያሉ ፍጡራንንም የሚያመልኩ አሉ። ልክ እንዲሁ ጊዜን የሚያመልኩ (ደህርዬች)፣ ገንዘብን፣ ነፍስያን፣... የሚያመልኩ አሉ።

አላህ እነዚህ ሁሉ ቢሰበሰቡ **"<u>ዝንብን እንኳን አይፈጥሩም</u>"** ብሎናል። መፍጠር ይቅርና ዝንብ **<u>አንዳችን ነገር ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉም።</u>** ይህን ያህል ደካማዎች ናቸው። ስለሆነም ፈላጊውም (አምላኪዎቹ፣ ጠያቂዎቹ) ተፈላጊም (ከአላህ ውጭ ተመላኪዎቹ፣ ተጠያቂዎቹ) ሁሉም ደካማ ናቸው። የአላህ ባርያዎች ሆይ! ድካም የማያገኘውን፣ ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ የሆነውን አላህ እስከ እለተ ሞታችን ድረስ እንድናመልከው ነፍሴንም እናንተንም አደራ እላለሁ።

19.2. የሸረሪት ድር (ቤት) ምሳሌ፡-

ምሳሌ በመስጠት አቻም አምሳያም የሌለው ጌታችን አላህ አሁን ደግሞ ከአላህ ውጭ ረዳቶችን የያዙ ሰዎች ምሳሌያቸው የሸረሪት ቤትን መያዝ እንደሆነ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ مَثَلُ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوۡلِيَآءَ كَمَثَلِ ٱلۡعَنكَبُوتِ ٱتَّخَذَتۡ بَيۡتٗاۖ وَإِنَّ أَوۡهَنَ ٱلۡبُيُوتِ لَبَيۡتُ ٱلۡعَنكَبُوتِۖ لَوۡ كَانُواْ يَعۡلَمُونَ ٤١ ﴾ العنكبوت: ٤١.

"የእነዚያ ከአላህ ሌላ ረዳቶችን (ጣዖታትን) የያዙ ሰዎች ምሳሌ <u>ቤትን እንደ ሠሪች ሸረሪት ብጤ ነው።</u> <u>ከቤቶችም ሁሉ በጣም ደካማው የሸረሪት ቤት ነው።</u> ቢያውቁ ኖሮ (አማልክት አደርገው አይግዚቸውም ነበር)።" [አል ዐንከቡት፡ 41]

19.3. ከሰማይ እንደ ወደቀ ሰው ምሳሌ፡-

﴿ حُنَفَآءَ لِلَّهِ غَيۡرَ مُشۡرِكِينَ بِهِۦۚ وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَكَأَنَّمَا خَرَّ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَتَخۡطَفُهُ ٱلطَّيۡرُ أَوۡ تَهۡوِي بِهِ ٱلرِّيحُ فِي مَكَانٖ سَحِيقٖ ٣١ ﴾ الحج: ٣١.

"ለአላህ ታዛዦች በእርሱ የማታገሩ ሆናችሁ (ከሐሰት ራቁ)። <u>በአላህም የሚያጋራ ሰው፤ ከሰማይ እንደ ወደቀና በራሪ እንደምትነጥቀው፣ ወይም ነፋስ እርሱን በሩቅ ሰፍራ እንደምትጥለው ብጤ ነው።</u>" [አል ሐጅ፡ 31]

አስገራሚ ምሳሌ ነው። ተውሒድ በጣም ታላቅ መሆኗ በሰማይ ተመሰለች። ተውሒድን ትቶ ሺርክ ውስጥ የተዘፈቀ ከሰማይ ላይ እንደተፈጠፈጠ ነው። ሱብሃነላህ! ይሄ የአላህ ቃል የተውሒድን ታላቅነት እና የሺርክን አስከፊነት ከጠቀሱ አንቀፆች ውስጥ ዋና ከሚባሉት ነው። ከሰማይ ላይ የተፈጠፈጠ መትረፊያ እንደሌለው፣ ከተውሒድ

ተፈጥፍጦ ሺርክ ውስጥ የገባና፣ በዛው መንገድ የሞተ መትረፈያም ረዳትም የለውም። ጀነት በእሱ ላይ እርም ናት። መኖርያው እሳት ነው። ለበደለኞች ረዳት የላቸውም።

19.4. የተክል ምሳሌ!

﴿ وَمَثَلُ كَلِمَةٍ خَبِيثَةٍ كَشَجَرَةٍ خَبِيثَةٍ ٱجۡتُثَّتۡ مِن فَوۡقِ ٱلۡأَرۡضِ مَا لَهَا مِن قَرَارٖ ٢٦ ﴾ إبراهيم: ٢٦.

"የመጥፎም ቃል (ፍሬ የማያፈራው ሺርክ) ምሳሌ ከምድር በላይ የተነለሰሰች ለእርሷ ምንም መደላደል የሌላት እንደሆነች <u>መጥፎ ዛፍ ነው</u>።" [ኢብራሂም: 26]

20. ተውሒድ የአንድነት ዋና መሰረት ነው

የሰው ልጆች ሁሉ የፍጡራንን ፈጣሪ አንድ አምላክ አላህን በብቸኝነት በማምለክ በእርሱም ላይ ማንንም ባለማጋራት በአንድ ሃይማኖት ላይ ነበሩ። አላህ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል:-

﴿ كَانَ ٱلنَّاسُ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ فَبَعَثَ ٱللَّهُ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ لِيَحۡكُمَ بَيۡنَ ٱلنَّاسِ فِيمَا ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِۚ وَمَا ٱخۡتَلَفَ فِيهِ إِلَّا ٱلَّذِينَ أُوتُوهُ مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَٰتُ بَغۡيَۢا بَيۡنَهُمۡۖ فَهَدَى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لِمَا ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ مِنَ ٱلۡحَقِّ بِإِذۡنِهِۦۗ وَٱللَّهُ يَهۡدِي مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٍ ٢١٣ ﴾ البقرة: ٢١٣.

<u>"ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ)። አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ። ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ።</u> በእርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አሰረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለሆነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጂ

አልተለያዩበትም። አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለእዚያ ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃዱ መራቸው። አላህም የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል።" [አል-በቀራህ፡ 213]

<u>ከአንድነት በኋላ የተለያዩት በሺርክ ነው</u>። ይህን አስመልክቶ ኢማሙል ቡኻሪ በዘገቡት የመጀመርያው ለምድር ህዝቦች የተላከው መልክተኛ ኑሕ (ዐለይሂ ሰላም) ናቸው። የተላኩበትም ምክንያት እንደሚከተለው ነው፡-

ከላይ እንደተጠቀሰው በአደም እና በኑሕ መካከል የነበሩት ህዝቦች አንድ ሃይማኖት እስልምናን የሚከተሉ ነበሩ። **<u>ኑሕ የተላከባቸው ህዝቦች የፈፀሙት የበደሎች ሁሉ ታላቅ በደል የሆነውን ሺርክ ነው</u>**። ወደ ሺርክ ደግሞ የወሰዳቸው ከአላህ እዝነት የተባረረው ሸይጧን እነሱን ቢድዐ በማሰራት ነው።

የሚከተለው የቁርኣን አንቀፅ ከዚህ በታች ለምናየው ነጥብ አንኳር መግቢያ ይሆነናል።

﴿ وَقَالُواْ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمۡ وَلَا تَذَرُنَّ وَدّٗا وَلَا سُوَاعٗا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسۡرٗا ٢٣ ﴾ نوح: ٢٣.

<u>"አሉም፦ አምላኮቻችሁን አትተዉ። ወድንም፣ ሱዋዕንም፣ የጉሥንም፣ የዑቅንም ነስርንም አትተው።"</u> [ኑህ: 23]

እነዚህ 5 **<u>"አማልክት"</u>** ተብለው የተጠሩ ግለሰቦች እነማን ናቸው? እነዚህ ግለሰቦች በታላቁ ሰሃባ ዐብደላህ ብኑ ዐባስ (ረድየላሁ አንሁማ) ሷሊሆች (መልካም የአላህ ባርያዎች) መሆናቸው የተመሰከረላቸው ናቸው። እነዚህ አምስት ሷሊሆች ሲሞቱ ሸይጧን ለህዝቦቻቸው አዛኝ መስሎ **<u>"ይቀማመጡ የነበረበት ቦታ ላይ ሃውልት ብታደርጉላቸው"</u>** አላቸው። እነሱም እሺ ብለው ተቀበሉት።

ልብ በሉ በዚህ ግዜ አማልክት ተብለውም አልተጠሩም። ሸይጧን ግቡን ለማሳካት ሩቅ ነው የሚያልመው።

ከዛም ይህ ትውልድ አልፎ ሌላ ትውልድ ሲተካና፣ እውቀትም ሲጠፋ **<u>“አባቶቻችሁ ዝናብ ሲቸግራቸው እነሱን ነበር የሚጠይቁት”</u>** ብሎ ታላቁ ወጥመዱ ውስጥ ከተታቸው። ከዛም ተቀበሉት። በዚህም ምክንያት ሃቅ (ተውሒድ) እና ባጢል (ሺርክ) ተለዩ። አላህ ለምድር ህዝቦች የመጀመርያውን መልክተኛ ኑሕን (ዐለይሂ-ስሰላም) ላከ።

ታላቁ መልክተኛ ኑሕ በቀንም በማታም፣ በድብቅም በግልፅም፣ በተለያየ ስልት ህዝባቸውን **<u>“ህዝቦቼ ሆይ! አላህን በብቸኝነት አምልኩት ከእርሱ ውጭ በሃቅ የሚመለክ የለምና”</u>** በማለት 950 አመት ተጣሩ። በጣም ጥቂቶች እንጂ ለጥሪው መልካምን መልስ አልሰጡም።

የእያንዳንዱን መልእክተኛ ጥሪ የተመለከተ፣ በደንብ ያጤነ አንድነትና ጠላትነት የተመሰረተበት ዋናው ጉዳይ ተውሒድ እንደሆነ በደንብ ይገነዘባል።

የአላህ መልክተኛ ﷺ ከዱዐ ሁሉ በላጭ የአረፋ ቀን የሚደረግ ዱዐ ነው። እኔና ከእኔ በፊት የነበሩ ነብያት ያልነው በማለት የሚቀጥለውን የተውሒድ ቃል እሳቸውና ከእርሳቸው በፊት የነበሩ ነብያት እንዳሉት ነገሩን።

"لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحَدْهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ".[1]

“ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ የለም። በብቸኝነት፣ ኢጋር የለውም፣ ንግስና ሁሉ ለእርሱ ነው፤ ምስጋና ሁሉ ለእርሱ ነው፤ እርሱ (አላህ) ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ነው።”

ሐጅ ላይ የተለያዩ ዘሮች፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ይህችን ቃል የነብያትን ፋና በመከተል አንድነታቸውን የምታጠናክረዋን ቃል ይሏታል።

በአላህ ላይ የሚያጋሩ ሰዎች ለሚጠሯቸው (ከአላህ ሌላ ለሚያጋሯቸው) አካላት አምልኮን ይፈፅማሉ። ለምሳሌ በአገራችን በስልጤ፣ በጉራጌ፣ በወሎ፣ በጎንደር፣ በባሌ፣ በሀረር፣ በትግራይ፣... በርካታ በጥፋት የታጀቡ፣ ቀን የተመደበላቸው መጤ ክብረ በዓላት አሉ። **እነዚህ በአብዛሀኛው በሺርክ የሚታጀቡ ድግሶች <u>ኡማውን ለማፍዘዝና ለመለያየት</u> ቀላል የማይባል ድርሻ አላቸው።**

አስገራሚው የአብሬት ተከታዬች ወደ ቃጥባሬ አይሄዱም የቃጥባሬዎቹም ወደ አብሬት አይሄዱም። **<u>ታድያ ሺርክና ቢድዐ ኡማውን እንደሚበታትኑ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ አለን?</u>** በሌላ በኩል ተውሒድ በዘርም፣ በወቅትም ያልተገናኙትን ነብያትና ተከታዬቻቸውን አንድ ማድረጓ ብቸኛዋ መሰባሰቢያ መሆኗን አያሳየንምን? አላሁ አክበር!! ይሄ ለአእምሮ ባለቤቶች ታላቅ ትምህርት አለበት። ተውሒድ ባለቤቶቿን ስትሰበስብ፣ ሺርክና ቢድዐ ግን ኡማውን ይበታትናሉ።

እስቲ ልብ ብለን ይህንን አንድነት እንመልከተው። ተውሒድ አንድ ያደረገችው ከመጀመርያ መልክተኛ እስከ መጨረሻ ድረስ ያለውን ነው።

የአላህ መልክተኛን ﷺ አንድ አመት ያንተን አምላክ እንገዛ፣ አንድ አመት የእኛን አምላክ ተገዛ የሚል ጥያቄ በቀረበላቸው ወቅት አላህ የሚከተለውን አወረደ፡-

﴿ قُلْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿١﴾ لَآ أَعْبُدُ مَا تَعْبُدُونَ ﴿٢﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٣﴾ وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٌ مَّا عَبَدتُّمْ ﴿٤﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٥﴾ لَكُمْ دِينُكُمْ وَلِىَ دِينِ ﴿٦﴾ ﴾ الكافرون: ١ – ٦.

"በላቸው፦ እናንተ ከሓዲዎች ሆይ! ያንን የምታመልኩትን (ጣዖት አሁን) አላመልክም። እናንተም እኔ የማመልከውን (አምላክም አሁን) አምላኪዎች አይደላችሁም። እኔም ያንን ያመለካችሁትን (ወደፊት) አምላኪ አይደለሁም። እናንተም እኔ የማመልከውን (ወደፊት) አምላኪዎች አይደላችሁም። ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ። ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ።" [10] [አል ካፊሩን፡ 1-6]

እንግዲህ ሺርክ ካለ አንድነት እንደሌለ ከአላህ በላይ ማን ይንገረን?

ቁርአን ስሙ ፉርቃን ነው። ፉርቃን ማለት ደግሞ **ሃቅን ከባጢል የሚለይ ማለት ነው**። **<u>ተውሒድና ሺርክ አብረው አይሄዱም</u>**። ሊለያዩ ግድ ይላቸዋል። የጀነት ጓዶችና የእሳት ጓዶች በፍፁም አንድ አይሆኑም። ነብዩ ሙሐመድም ﷺ የሰዎች መለያ (ሃቅ እና ባጢልን የለየ) ነው፤ በሌላ ዘገባ በሰዎች መሃል የለያየ (ሀቅን በተቀበሉና ሀቅን ባልተቀበሉ ሰዎች መካከል የለያየ) ነው ተብሏል።

የነብዩን ﷺ የተውሒድ ጥሪ የተቀበሉትና ለጥሪው ጀርባ ሰጥተው ሺርክ ውስጥ የቀሩት ሰዎች እንዴትስ ነብዩ ﷺ አይለያዩዋቸውም።

21. አንድነት በተውሒድ ከድንቅ ምሳሌ ጋር

በተውሒድ በዘር የማይገናኙ ሰዎች አንድ ይሆናሉ። በሺርክ የአንድ ቤተሰብ ሰዎች ይበታተናሉ።

([10]) ኢብን ነውፈል (ረድየላሁ አንሁ) የአላህ መልክተኛ ﷺ ጋር ሄዶ "ከመተኛቴ በፊት ምን ማለት እንዳለብኝ አስተምሩኝ" አላቸው። የአላህ መልክተኛ ﷺ "በላቸው እናንተ ከሐዲዎች ሆይ (ሱረቱል ካፊሩን) **<u>በእርግጥ ከሺርክ መጠበቂያ ናት</u>**።" ኢማሙል አልባኒ ሶሂህ ብለውታል (ሰሂሁ አት-ቲርሚዚይ 2709)።

ተውሒድ ሰልማንን ከፋርስ፣ ቢላልን ከሀበሻ፣ የያሲርን ቤተሰቦች ከየመን፣ የቆዳ ቀለማቸው፣ የዘር ሀረጋቸው ወይንም የሃብት ደረጃቸው ሳይገድባቸው ሁሉን በአንድነት፣ በፍቅር አሰባስቧል። በሺርክ ሳቢያ የመጀመርያው መልክተኛ ኑሕ (ዐለይሂ-ስሰላም) ከልጃቸው፣ ነብዩላህ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ስሰላም) ከአባታቸው፣ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ከገዛ አጎቶቻቸው ጋር ተለያይተዋል።

<u>ትዝብት፡-</u> ዛሬ የአገራችንንም ይሁን የአለም ሙስሊሞችን እየበታተነ፣ ሃይላቸውን እያዳከመ፣ እያሸመደመዳቸው ያለው የጥፋት አካሄድ ሺርክ እና ቢድዓን እንዳላዩ በማለፍ ላይ ህብረት ፈጥረው፣ ይህንንም የተሳሳተ አካሄድ ኡማውን አንድ ያደርጋል ብለው አጉል የሚደክሙ ሰባኪዎች መበራከት ነው። እውነተኛውን የተውሒድ፣ የሱና እና የመልካም ቀደምቶችን አረዳድ ህብረትን በታታኝ፣ ኋላ ቀር፣ ከዚህ ዘመን ጋር የማይሄድ አካሄድ እንደሆነ በያጋጣሚው ከሚከሱ አጥፊዎች በላይ የተጋረጠ ትልቅ አደጋ የለም። ይህን አካሄድ የመረጡ ሰዎች ሁኔታ ሀያሉ ጌታ "**<u>የተሰባሰቡ ይመስሉሀል። ልቦቻቸው ግን የተለያዩ ናቸው</u>**" ሲል ከገለፃቸው አይሁዶች ጋር የሚያመሳስላቸውን መንገድ መርጠዋል። ይልቁንም ለኡማው አንድነት ያለው እሳቤ ፍሬ እንዲያፈራ የሚሻ ሁሉ አላህ አበክሮ ባዘዘው ተውሒድና ሱና ላይ በርትቶ ሊሰራ ይገባል። ከዚህ ውጭ ግን በአላህ ላይ ከሚያጋሩ፣ ቁርኣን ተቀንሷል ከሚሉ፣ ኢማሞች ከነብያት ይበልጣሉ ከሚሉ፣ የነብያችንን ውድ ባለቤት አኢሻንና ሐፍሷን "ከሀዲ" ከሚሉ፣ እነ አቡበክርንና ዑመርን ከሚራገሙ፣ ሰሃባዎችን ጠላት አድርገው ከያዙ ራፊዳ ሺዐዎች ጋር ህብረት በመፍጠር ምድርን የሚያበላሹ ሰዎች እነሱ አሳማሪዎች ነን ቢሉም አላህ "**አዋጅ እነሱ ምድርን አበላሾች ናቸው**" ካላቸው ውስጥ እንዳይገቡ ሊመለሱ ይገባል።

ያለበለዚያ የተውሒድን መሰረታዊ መርህ በማላሸት አበጀን ብለው ከጥፋት ሃይሎች ጋር የሰሩት ህብረት አመታት ቀርቶ ወራት መዝለቅ አቅቶት በአደባባይ ሲንኮታኮት በገሐድ ተመልከተናል። ስለዚህ ስለ አንድነታችን ስንለፋ በቅድሚያ ተውሒድን ህዝብ ውስጥ ከማስረፅ መሰረት ሊጀመር ይገባል። ያለበለዚያ ልፋታችን የዜሮ ድምር ይሆናል።

22. አማኝ ጦሀራ ነው፣ ሙሽሪክ ነጃሳ ነው

አላህ የአደምን ልጅ አላቀው፣ አከበረውም። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَلَقَدۡ كَرَّمۡنَا بَنِيٓ ءَادَمَ وَحَمَلۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَرَزَقۡنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَفَضَّلۡنَٰهُمۡ عَلَىٰ كَثِيرٖ مِّمَّنۡ خَلَقۡنَا تَفۡضِيلٗا ٧٠ ﴾ الإسراء: ٧٠.

"የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው። በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው። ከመልካምችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው። ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።" [አል ኢስራእ፡ 70]

ይህን ክብሩን ያስጠብቅ ዘንድ በተውሒድ ላይ መፅናት ግድ ይለዋል። ያለበለዚያ ግን የተከበረው የአደም ልጅ በራሱ ጊዜ ክብሩን ያጣል። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّمَا ٱلۡمُشۡرِكُونَ نَجَسٞ فَلَا يَقۡرَبُواْ ٱلۡمَسۡجِدَ ٱلۡحَرَامَ بَعۡدَ عَامِهِمۡ هَٰذَاۚ وَإِنۡ خِفۡتُمۡ عَيۡلَةٗ فَسَوۡفَ يُغۡنِيكُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦٓ إِن شَآءَۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ٢٨ ﴾ التوبة: ٢٨.

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አጋሪዎች እርኩሶች (ነጃሳዎች) ብቻ ናቸው። ከዚህም ዓመታቸው በኋላ የተከበረውን መስጊድ አይቅረቡ። ድህነትንም ብትፈሩ አላህ ቢሻ ከችሮታው በእርግጥ ያከብራችኋል። አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና።" [አት-ተውባህ፡ 28]

ልብ ይበሉ! ርክሰቱ አካላዊ ርክሰት አይደለም። በተውሒድ ብቻ የሚፀዳ መንፈሳዊ ርክሰት ነው።

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ، " أَنَّهُ لَقِيَهُ النَّبِيُّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي طَرِيقٍ مِنْ طُرُقِ الْمَدِينَةِ ، وَهُوَ جُنُبٌ ، فَانْسَلَّ ، فَذَهَبَ فَاغْتَسَلَ ، فَتَفَقَّدَهُ النَّبِيُّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ، فَلَمَّا جَاءَهُ ، قَالَ : أَيْنَ كُنْتَ يَا أَبَا هُرَيْرَةَ ؟ قَالَ : يَا رَسُولَ اللَّهِ ، لَقِيتَنِي وَأَنَا جُنُبٌ ، فَكَرِهْتُ أَنْ أُجَالِسَكَ حَتَّى أَغْتَسِلَ ، فَقَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : سُبْحَانَ اللَّهِ ، ***<u>إِنَّ الْمُؤْمِنَ لَا يَنْجُسُ</u>***"

ከአቡ ሁረይራ ተይዞ ከመዲና መንገዶች ውስጥ በአንዱ ነብዩ ﷺ አገኙት። እሱ ጁኑብ ነበርና ቀስ ብሎ ተሰወረ። ከዚያም ሄዶ ታጠበ። ነብዩ ﷺ ፈልገውት ኖሮ ሲመጣ ጊዜ **"የት ነበር አቡ ሁረይራ ሆይ?!"** አሉ። እሳቸውም **"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! <u>ጁኑብ ሆኜ ነው ያገኘሽይ</u>።** እናም **እስከምታጠብ ድረስ ካንተ ጋር መቀመጥን ጠላሁ።** የአላህ መልእክተኛ ﷺ በዚህን ጊዜ ***<u>"ሙእሚን እኮ ኢይነጀስም!"</u>*** አሉ። [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል]

23. የቀኑ ኸይር ሰራተኛ

የአላህ መልክተኛ ﷺ የቀኑ ኸይር ሰራተኛ ስለሆነው እድለኛ ሲናገሩ የተውሒድን ከሊማ በዚህ መንገድ ያለው ሰው መሆኑን ነግረውናል፡-

"لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحَدْهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ"

“ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ የለም። በብቸኝነት፣ ኢጋር የለውም፣ ንግስና (ባለቤትነት) ለእርሱ ናት፣ ምስጋናም ለእርሱ ነው፣ ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ነው።”

ይህንን የተውሒድ ከሊማ በጠዋቱ ከፍለ ጊዜ 100 ጊዜ ያለ ሰው የቀኑ ኸይር ሰራተኛ ይሆናል አሉ የአላህ መልክተኛ ﷺ ፣ ከሱ በላይ ያለው ሲቀር። [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል]

እንግዲህ ይህንን የተውሒድ ቃል ትርጉሙን አውቆ ላለው ግለሰብ **“የቀኑ ኸይር ሰራተኛ”** የሚለውን ማዕረግ ያሸልመዋል። ምንኛ ያማረ ሽልማት ነው!

24. በተውሒድና በሺርክ የሰዎች ማንነት ሲራራቅ

የተከበረው የአደም ልጅ በሺርክና በክህደት ምን ያክል እንደሚዘቅጥ እንመልከት፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ فِي نَارِ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَآۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ شَرُّ ٱلۡبَرِيَّةِ ٦ ﴾ البينة: ٦.

“እነዚያ ከመጽሐፉ ሰዎች የካዱት፣ ኢጋሪዎቹም በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው፤ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲኾኑ <u>እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ ክፉ ናቸው</u>።” [አል-በይናህ፡ 6]

በሌላ በኩል ደግሞ ተውሒድና መልካም ስራ የሰውን ልጅ ክብር እጅጉን ያልቁታል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ خَيۡرُ ٱلۡبَرِيَّةِ ٧ ﴾ البينة: ٧.

“እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሠሩት፣ <u>እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ ናቸው</u>።” [አል-በይናህ፡ 7]

ስለዚህ ሰዎች ለተውሒድና ለሺርክ ባላቸው ቅርበትና ርቀት የተነሳ **<u>“ከፍጥረት ሁሉ በላጭ”</u>** እና **<u>“ከፍጥረት ሁሉ ክፉ”</u>** ተብለው ክብራቸው የሰማይና የምድር ያክል ይራራቃል።

25. ተውሒድ እና ሐጅ

የመካ አጋሪያን ሐጅ ይፈፅሙ ነበር። ነገር ግን በአላህ ላይ ያጋሩበት ነበር። ከኢብኑ ዐባስ ረዲየላሁ ዐንሁማ ተይዞ እንዲህ ይላሉ፡- “ሙሽሪኮች ለበይከ ለአንተ ተጋሪ የለህም” ይሉ ነበር። ይህን ሲሉ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቀጥሎ የሚሉትን አፍራሽ ሀሳብ ስለተረዱ “ወዮላችሁ በቃ በቃ!” ይሏቸው ነበር። (ሙሽሪኮች ቀጥሎ የሚናገሩት አፍራሽ ሀሳብም የሚከተለው ነበር) **“<u>የምትቆጣጠረው የማይቆጣጠርህ ላንተ የሆነ ተጋሪ ቢሆን እንጂ</u>”** ይላሉ። ይህን የሚሉት ከዕባን እየዞሩ (ጠዋፍ ሲያደርጉ) ነው።” [ሙስሊም]

ሌላው አስገራሚ ነገር የመካ አጋሪያን አመቱን ሙሉ ወንጀል በሰራንበት ልብስ ጠዋፍ አንፈፅምም ብለው ራቁታቸውን ነበር ጠዋፍ የሚሰሩት። ነገር ግን ዲን መልካም ያለው ሲቀር እኛ በስሜታችን ተነስተን ያልነውን ብንል፣ የሰራነውን ብንሰራ መልካም ሊሆን አይችልም። መልካም አስበን ቢሆንም እንኳን። ***<u>መልካም ማለት አንተ መልካም ያልከው ነገር አይደለም። ይልቁንም መልካም ማለት ዲኑ መልካም ያለው ነገር ነው።</u>***

እንደሚታወቀው የአላህ መልክተኛ ﷺ ካዕባ ላይ ያለው “ሀጀረል አስወድ” [11] በመባል የሚታወቀውን ድንጋይ ለቻለ ሰው ሰዎችን ሳይገፋ እንዲስመው፣ ላልቻለ ሰው ደግሞ አላሁ አክበር ብሎ በምልክት ሰላም እንዲለው አስተምረዋል። ታላቁ ሰሃባ አሚረል ሙእሚኒን ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ረድየላሁ አንሁ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተውሒድን እና ሱናን በትክክለኛው መንገድ ተረድተን እንይዝ ዘንድ መመዘኛ የሚሆነን መልእክት ጥለው አልፈዋል። ሐጀረል አስወድን ሲስሙ እንዲህ ብለዋል፡-

---

([11]) ይህ ድንጋይ ከጀነት ነው የወረደው። የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ፡- “**ሐጀሩል አስወድ ከበረዶ የነጣ ሆኖ ነው ከጀነት የወረደው። የሰው ልጆች ወንጀል ነው ያጠቆረው።**” [አሶሒሐ፡ 2618]

“በአላህ ይሁንብኝ እኔ አንተን <u>የማትጎዳ የማትጠቅም</u> ድንጋይ እንደሆንክ አውቃለሁ። <u>የአላህ መልእክተኛ ﷺ ሲሰሙህ ባላይ ኖሮ ባልሰምኩህ ነበር</u>።”

[ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል]

ከዚህ ሐዲሥ ከምንወስዳቸው ቁም ነገሮች ውስጥ፡-

- ከአላህ ውጭ የሚጠቅምም የሚጎዳም እንደሌለ፣

- የአላህ መልክተኛ ﷺ የሰሩትን ልንፈፅም እንደሚገባ። ምክንያቱ ባይገባንም እንኳን። ምክንያቱም እሳቸው አላህ እንዳለው፡-

﴿ وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلْهَوَىٰٓ ۝٣ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْىٌ يُوحَىٰ ۝٤ ﴾ النجم: ٣ – ٤.

“ከልብ ወለድም አይናገርም። እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራሕይ እንጅ ሌላ አይደለም።”

[አን-ነጅም፡ 3-4]

የአላህ መልክተኛ ﷺ ልክ አንቀፁ ላይ እንደተገለፀው ከአላህ የወረደላቸውን መለኮታዊ ራዕይ ይፈፅማሉ፣ ያስተላልፋሉ። እኛም የታዘዝነው እሳቸውን ድካ በድካ እንድንከተል ነው። አላህ እንዳለው መልክተኛውን የታዘዘ አላህን እንደታዘዘ ነው።

26. አማኝና ከሃዲ ከሞት አፋፍ ላይ

26.1. የአማኝ ነፍስ ልትወጣ ስትል

በምድራዊ አኗኗር ላይ አማኝ ከከሃዲ ልዩነት እንደነበራቸው ሁሉ፣ ሞት አፋፍ ላይም ልዩነት አላቸው።

ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ “ሚች ጣእረ-ሞት ላይ እያለ መላእክት ይቀርቡታል። ሰውየው ደግ ከሆነ “**አንቺ ከጥሩ አካል ውስጥ የነበርሽዋ ንፁህ ነፍስ ሆይ! በእረፍትና በመልካም ሲሳይ ካልተቆጣው ጌታ ዘንድም አብሽሪ**” ውጪ ይሏታል። እስከምትወጣ ድረስ እንዲህ ሲባል ይቆያል። ከዚያም ወደ ሰማይ እንድትወጣ ትደረጋለች። እንዲከፈትላት ፈቃድ ይጠየቃል። “**ማነው ይሄ?**” ሲባል ይጠየቃል። “**እገሌ ነው**” ይባላል። “**<u>ከጥሩ አካል ውስጥ የነበረሽዋ ጥሩዋ ነፍስ ሆይ! እንኳን ደህና መጣሽ! ውጪ። በእረፍትና በመልካም ሲሳይ ካልተቆጣው ጌታ ዘንድም አብሽሪ</u>**” ይባላል። የላቀው አላህ ወዳለበት ሰማይ እስከምትደርስ ድረስ እንዲሁ እየተባለ ትቀጥላለች።” [ሶሒሑል ጃሚዕ፡ 1968]

26.2. የከሃዲው ነፍስ አስመልክቶ ደግሞ

“ሰውየው ክፉ ሰው ከሆነ **<u>አንቺ በቆሻሻ አካል ውስጥ የነበርሽ ቆሻሻ ነፍስ ሆይ! የተወገዝሽ ሆነሽ ውጪ! በፈላ ውሃ እና በእዝም አብሺሪ!</u>**” ትባላለች።” “እጅግ እንደሚገማ ጥንብ ሽታ ይዛ ትወጣለች። ወደ ቅርቢቷ ሰማይ ስትደርስ አይከፈትላትም። ነብዩ ﷺ ከዚህ ቀጥለው ይህቺን አንቀፅ አነበቡ፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَٱسۡتَكۡبَرُواْ عَنۡهَا لَا تُفَتَّحُ لَهُمۡ أَبۡوَٰبُ ٱلسَّمَآءِ وَلَا يَدۡخُلُونَ ٱلۡجَنَّةَ حَتَّىٰ يَلِجَ ٱلۡجَمَلُ فِي سَمِّ ٱلۡخِيَاطِۚ وَكَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُجۡرِمِينَ ٤٠ ﴾ الأعراف: ٤٠.

“እነዚያ አንቀጾቻችንን ያስተባበሉ ከእርሷም የኮሩ <u>ለእነርሱ የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላቸውም</u>። ግመል በመርፌ ቀዳዳ እስከሚገባም ድረስ ገነትን አይገቡም። እንደዚሁም አመፀኞች እንቀጣለን።” [አል-አዕራፍ፡ 40]

27. የተዘነጋው አላማ

ልጅ ከሚወለድባቸው ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተውሒድን እንዲረከብ ነው። ነብየላህ ዘከርያ (ዐለይሂስ-ሰላም) ልጅ ለመውለድ የተመኙት የተውሒድን መልክት የሚረከባቸው ልጅ በመፈለግ ሰበብ መሆኑን አላህ እንዲህ ሲሉ ይነግረናል፦

﴿ كٓهيعٓصٓ ۝١ ذِكۡرُ رَحۡمَتِ رَبِّكَ عَبۡدَهُۥ زَكَرِيَّآ ۝٢ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ نِدَآءً خَفِيًّا ۝٣

"(ካፍ ሃ ያ ዓይን ሷድ) (ይህ) ጌታህ ባሪያውን ዘከሪያን በችሮታው ያወሳበት ነው። ጌታውን የምስጢርን ጥሪ በተጣራ ጊዜ (አሰታውሰ)።"

قَالَ رَبِّ إِنِّي وَهَنَ ٱلۡعَظۡمُ مِنِّي وَٱشۡتَعَلَ ٱلرَّأۡسُ شَيۡبٗا وَلَمۡ أَكُنۢ بِدُعَآئِكَ رَبِّ شَقِيّٗا ۝٤

"አለ፦ ጌታዬ ሆይ! እኔ አጥንቴ ደከመ፤ ራሴም በሸበት ተንቀለቀለ፤ አንተም በመለመንę ጌታዬ ሆይ! (ምንጊዜም) ዕድለ ቢስ አልሆንኩም።

وَإِنِّي خِفۡتُ ٱلۡمَوَٰلِيَ مِن وَرَآءِي وَكَانَتِ ٱمۡرَأَتِي عَاقِرٗا فَهَبۡ لِي مِن لَّدُنكَ وَلِيّٗا ۝٥

"እኔም ከበኋላዬ ዘመዶቼን በእርግጥ ፈራሁ። ሚስቴም መካን ነበረች ስለዚህ ከአንተ ዘንድ ለኔ ልጅን ስጠኝ።"

يَرِثُنِي وَيَرِثُ مِنۡ ءَالِ يَعۡقُوبَۖ وَٱجۡعَلۡهُ رَبِّ رَضِيّٗا ۝٦

“የሚወርሰኝ፣ ከያዕቆብ[12] ቤተሰቦችም የሚወርስ የሆነን (ልጅ)። ጌታዬ ሆይ! ተወዳጅም አድርገው።”

﴿ يَٰزَكَرِيَّآ إِنَّا نُبَشِّرُكَ بِغُلَٰمٍ ٱسۡمُهُۥ يَحۡيَىٰ لَمۡ نَجۡعَل لَّهُۥ مِن قَبۡلُ سَمِيّٗا ٧ ﴾ مريم: ١ – ٧.

“ዘከሪያ ሆይ! እኛ በወንድ ልጅ ሰሙ የሕያ በሽነ ከዚህ በፊት ሞክሼን ባላደረግንለት እናበሰርሃለን» (አለው)።” [መርየም 1-7]

የባርያዎቹን ልመና የሚሰማውና የሚቀበለው አላህ፣ የዘከርያን ጥሪ ሰምቶ እንደጠየቀው **የነ ያዕቁብን ቤተሰቦች የሚወርስ**፣ በስሙ ከዚህ በፊት ሞክሼ የለለው የሆነውን፣ **<u>ነብዩላህ የህያን (አለይሂ ሰላም) ሰጠው</u>**።

28. ነብዩ ዒሳ፣ ትእዛዛቸው ክፉኛ የተጣሰው የተውሒድ አስተማሪ

በአለማችን ታላቁን የአላህ ነብይ ዒሳን (አለይሂ ሰላም) ያለ አግባብ የሚያመልኩ ቢሊዮኖች አሉ። አላህ ግን ስለ ዒሳና እናቱ መርየም እውነታ እንዲህ ሲል ይነግረናል፦

﴿ وَإِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ءَأَنتَ قُلۡتَ لِلنَّاسِ ٱتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيۡنِ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ قَالَ سُبۡحَٰنَكَ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ أَقُولَ مَا لَيۡسَ لِي بِحَقٍّۚ إِن كُنتُ قُلۡتُهُۥ فَقَدۡ عَلِمۡتَهُۥۚ تَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِي وَلَآ أَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِكَۚ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ ١١٦ ﴾

[12] ያዕቁብ ነብይ ናቸው። የነብዩላህ ኢስሐቅ ልጅ፣ የነብዩላህ ኢብራሂም የልጅ ልጅ፣ የነብዩላህ ዩሱፍ አባት ናቸው። ነብዩላሁ ዘከርያም ልጅ መውለድ የፈለጉት የነቢያትን ፈለግ እና መልክት ተቀባይ የሆነ ልጅ ፍለጋ ነው። አላህ እኛንም ዝርያዎቻችንም የተውሒድ መልእክትን ወራሾች በሱም ላይ ከሚሞቱት ያድርገን።

“አላህም፦ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፦ <u>እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን?</u> በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል።

﴿ مَا قُلۡتُ لَهُمۡ إِلَّا مَآ أَمَرۡتَنِي بِهِۦٓ أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمۡۚ وَكُنتُ عَلَيۡهِمۡ شَهِيدٗا مَّا دُمۡتُ فِيهِمۡۖ فَلَمَّا تَوَفَّيۡتَنِي كُنتَ أَنتَ ٱلرَّقِيبَ عَلَيۡهِمۡۚ وَأَنتَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ١١٧ ﴾ المائدة: ١١٦ – ١١٧.

“በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል <u>ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም</u>። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ። ባነሳኸኝ ጊዜ አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ ነህ።”
[አል-ማኢዳህ፡ 116-117]

29. ከባድ ጥያቄ ድንቅ መልስ።

ሰው እንዴት ሙሉእ የሆነውን ጌታ ትቶ የሰውነት ባህሪ የተላበሰን ሰዋዊ ባህሪያትን የሚያንፀባርቅን ፍጡር እንደ ፈጣሪ ይቆጥራል?! ጌታችን እንዲህ ይላል፦

﴿ مَّا ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَ إِلَّا رَسُولٞ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِ ٱلرُّسُلُۖ وَأُمُّهُۥ صِدِّيقَةٞۖ كَانَا يَأۡكُلَانِ ٱلطَّعَامَۗ ٱنظُرۡ كَيۡفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ ٱلۡأٓيَٰتِ ثُمَّ ٱنظُرۡ أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٧٥ ﴾ المائدة: ٧٥.

“የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የሆነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት። <u>(ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ።</u>

<u>አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት</u>።[13] [አል-ማኢዳህ፡ 75]

አስተውል! አላህ ዒሳንም መርየምንም አወደሰ። አክብሮት ይገባቸዋል ማለት ነው። ከዚያም ፍጡርነታቸውን የሚያስረዳ ጥቆማ ሰጠ። ይህም አክብሮቱ ወሰን ሊያልፍ እንደማይገባው አስረጂ ነው። ሊመለከ የሚገባው ምን አይነት እንደሆነ ተመልከት፡-

﴿ قُلۡ أَغَيۡرَ ٱللَّهِ أَتَّخِذُ وَلِيّٗا فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَهُوَ يُطۡعِمُ وَلَا يُطۡعَمُۗ قُلۡ إِنِّيٓ أُمِرۡتُ أَنۡ أَكُونَ أَوَّلَ مَنۡ أَسۡلَمَۖ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١٤ ﴾ الأنعام: ١٤.

“ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከኾነው አላህ <u>እርሱ የሚመግብ የማይመገብም ሲሆን ሌላን አምላክ እይዛለሁን?</u>» በላቸው። “እኔ መጀመሪያ ትእዛዝን ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ። ከአጋሪዎችም ፈጽሞ አትሁን (ተብያለሁ)» በላቸው። [አል-አንዓም፡ 14]

<u>ዒሳና እናቱ ሰዎችን መቀለብ ይችላሉን?</u> እንኳን ሌሎችን እራሳቸውንስ መቀለብ ይችላሉን? በፍፁም!! <u>እንዲያውም እራሳቸውም ተቀላቢዎች ናቸው</u>። ታዲያ ፈጣሪን ትቶ እራሱ ወደ ጌታው የሚያንጋጥጥን ፍጡር የሚከጅል ሰው ምንኛ የሚደንቅ ነው?!!

([13]) የሰው ልጅ አፈጣጠር አራት አይነት ሲሆን አምስተኛ የለውም፡፡ የሰው ልጅ አባት አደም ናቸው። እሳቸው የተፈጠሩት ከአፈር ነው። አደም ያለ እናትና ያለ አባት ነው የተፈጠሩት። እናታችን ሃዋ ደግሞ ከአደም የግራ ጎን አጥንት ከወንድ ብቻ ተፈጠሩ። የአላህ ነብይ ዒሳ (አለይሂስ-ሰላም) ደግሞ ያለ አባት ከሴት ብቻ ተፈጠሩ። የተቀሩት የሰው ልጆች ደግሞ ከወንድና ከሴት የዘር ፈሳሽ ተገኙ።

30. የተንሰራፋው የጂን አምልኮ

በሃገራችን "አውልያ፣ ሩሃንያ፣ ዛር፣ ቆሌ፣ የእናት የአባት አምላክ" ወዘተ እያሉ ጂኖችን የሚያመልኩ አሉ። በርግጥ ይሄ ጥንትም የነበረ ጥፋት ነው። አላህ እንዲህ ይጠይቃል፡-

﴿ وَيَوْمَ يَحْشُرُهُمْ جَمِيعًا ثُمَّ يَقُولُ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ أَهَٰٓؤُلَآءِ إِيَّاكُمْ كَانُوا۟ يَعْبُدُونَ ﴿٤٠﴾ قَالُوا۟ سُبْحَٰنَكَ أَنتَ وَلِيُّنَا مِن دُونِهِمْ ۖ بَلْ كَانُوا۟ يَعْبُدُونَ ٱلْجِنَّ ۖ أَكْثَرُهُم بِهِم مُّؤْمِنُونَ ﴿٤١﴾ ﴾ سبأ: ٤٠ – ٤١.

"ሁሉንም በሚሰበሰባቸውና ከዚያም ለመላእክቶቹ "<u>እነዚህ እናንተን ይግዙ ነበሩን?</u>" በሚላቸው ቀን (የሚሆነውን አስታውስ) ። (መላእክቶቹም) ጥራት ይገባህ ከእነርሱ ሌላ ረዳታችን አንተ ብቻ ነህ። (እንደሚሉት) አይደለም <u>ይልቁንም ጂንን ይግዙ ነበሩ</u>። አብዛኞቻቸው በእነርሱ አማኞች ናቸው ይላሉ።" [ሰበእ፡ 40-41]

ከዚህ አንቀፅ የምንረዳው፡-

- መላእክት እራሱ አላህን ***<u>"አንተ ብቻ ነህ ረዳታችን"</u>*** እንደሚሉ። ይህም የተውሒድ ቁንጮ ነው፣

- መላእክቶች ለአላህ ተዋራጅና ተናናሽ መሆናቸው፣

- ለነሱ ተፈፅሟል የተባለውን አምልኮ እንደማይቀበሉና፣ የተፈፀመው አምልኮ ለጂኖች መሆኑን ሲጠየቁ እንደሚመልሱ፣

- ጂን አምላኪዎች ከከሳሪዎች መሆናቸውን፣ ወዘተ

31. ኢብራሂም በተውሒድ ምክንያት “ኢማም (መሪ)” ተብሎ ተጠርቷል

ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ إِبۡرَٰهِيمَ كَانَ أُمَّةٗ قَانِتٗا لِّلَّهِ حَنِيفٗا وَلَمۡ يَكُ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١٢٠ ﴾ النحل: ١٢٠.

“ኢብራሂም ለአላህ ታዛዥ ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘንባይ <u>ሕዝብ (14) ነበር። ከሊጋሪዎቹም አልነበረም።</u> [አን-ነሕል፡ 120]

አላህ መልክተኛውን ﷺ የኢብራሂምን መንገድ ተከተል ሲል አዟቸዋል። ኢብራሂም እንዲህ ከሳቸው በኋላ ለመጡ ኢማም (መሪ) ነበሩ። አላህ ለኸሊሉ ኢብራሂም ያደላቸው ምንኛ ያማረ ሽልማት ነው?! አላህ የአባታችንን የኢብራሂምን መንገድ ተከታይ የሆነውን የሙሐመድን መንገድ ከሚከተሉት ያድርገን።

32. ተውሒድ የኢብራሂም ጎዳና

ዛሬ በዚህ “ሰልጥኗል” በሚባለው አለም ተውሒድን የያዘ ሰው እንደ ቂል (ሞኝ) ነው የሚታየው። ነገር ግን ዘመን በማይሽረው የአላህ ቃል ቁርአን ውስጥ የእውነት ቂል ማን እንደሆነ ተገልጿል። ይሔውና፡-

﴿ وَمَن يَرۡغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبۡرَٰهِـۧمَ إِلَّا مَن سَفِهَ نَفۡسَهُۥۚ ﴾ البقرة: ١٣٠.

---

(14) በአንቀፅዋ የተጠቀሰችዋ ቃል (ኡማሕህ) አብዛኛዎቹ የተፍሲር ሊቃውንት ማብራርያ ኢማም (መሪ) ማለት ነው። በጥቅሉ ቃሏ 4 የተለያየ ትርጉሞች አሏት። አንዱ ኢማም (መሪ) የሚለው ነው።

“ከኢብራሂምም ሕግጋት (ከተውሒድ) ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልሆነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማን ነው? በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ መረጥነው። በመጨረሻይቱም ዓለም እርሱ ከመልካሞቹ ነው።” [አል-በቀራህ፡ 130]

ጌታችን አላህ መልክተኛውን ﷺ የኢብራሂምን መንገድ እንዲከተሉ እንዲህ ሲል ያዛቸዋል፡-

﴿ ثُمَّ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ أَنِ ٱتَّبِعۡ مِلَّةَ إِبۡرَٰهِيمَ حَنِيفٗاۖ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١٢٣ ﴾ النحل: ١٢٣.

“ከዚያም ወደ አንተ የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲኾን ተከተል፤ ከአጋሪዎቹም አልነበረም ማለት አወረድን።” [አን-ነሕል፡ 123]

የአላህ ባርያዎች ሆይ! ንቁ ሚዛናችንን እናስተካከል። **መቼም ቢሆን አጋሪ እና ከሃዲ ከአማኝ በላይ ሊሆን አይችልም። <u>የሰው ልጅ መለኪያው ዲን ነው</u>።** አላህ ዘንድ ደግሞ ዲን ማለት እነ ኢብራሂሙል ኸሊል የተጓዙበት እና የነበሩበት ሐኒፍያ (ቀጥተኛ) እስልምና ነው። ከእስልምና ውጭ አላህ አይቀበልም። ከእስልምና ውጭ ያለ በዱንያ መለኪያ የደረሰውን ያህል ቢደርስ መሃይም እና ቂል ነው። እንዴትስ መሃይም እና ቂል አይሆን? ብቸኛ ፈጣሪና ቀላቢውን ትቶ ፍጡራንን ሲያመልክ። አላህ ከቂልነት ይጠብቀን።

33. ትዳር ሊመሰረት የሚገባው ተውሒድ ካለው ሰው ጋር ነው።

ነብዩ ﷺ ትዳር ለአራት ነገሮች ሲባል እንደሚመሰረት ተናግረዋል። እኛ የትኛውን መምረጥ እንዳለብን አዛኙና ታማኙ መካሪ ገልፀውልናል።

" تُنْكَحُ الْمَرْأَةُ لِأَرْبَعٍ: لِمَالِهَا، وَلِحَسَبِهَا، وَلِجَمَالِهَا، وَلِدِينِهَا، فَاظْفَرْ بِذَاتِ الدِّينِ تَرِبَتْ يَدَاكَ "

“ሴት ልጅ ለ አራት ነገር ሲባል ትገብባለች። ለመልኳ፣ ለዘሯ፣ ለገንዘቧና ለዲኗ። <u>ዲን ያላትን ምረጥ አለበለዚያ እጅህ አፈር (አመድ አፋሽ) ትሆናለህ</u>።”

የዲን ቁንጮው ደግሞ ተውሒድ ነው።

ስለዚህ ተውሒድ የትዳር መመስረቻ አስኳል ነው። ዐቂዳዋ የተስተካከለ ሴት ምረጥ። እህቴ ሆይ! እምነቱ የተስተካከለ ቁርኣን እና ሐዲሥን መመርያው ያደረገ፣ የሰለፉነስ ሷሊሒን አረዳድ የተረዳ ሰው ምረጭ።

34. በተውሒድ ላይ ፅናት

عَنْ سُفْيَان بْنِ عَبْدِ اللَّهِ قَالَ: "قُلْت: يَا رَسُولَ اللَّهِ! قُلْ لِي فِي الْإِسْلَامِ قَوْلًا لَا أَسْأَلُ عَنْهُ أَحَدًا غَيْرَك؛ قَالَ: قُلْ: آمَنْت بِاَللَّهِ ثُمَّ اسْتَقِمْ" . رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከሱፍያን ኢብኑ ዐብዲላህ ረዲየላሁ ዐንሁ ተይዞ፦ **“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በኢስላም ውስጥ ካንተ ውጭ ሌላን የማልጠይቅበትን ነገር ንገረኝ” አልኳቸው። እሳቸውም “<u>በአላህ አመንኩ በልና ከዚያም ቀጥ በል</u>” አሉኝ።** [ሙስሊም ዘግበውታል]

በአላህ ዲን በተውሒድ ላይ ፀንተው የሞቱ ሰዎች፣ ሊሞቱ ሲሉ ሸልማታቸው እና ብስራታቸው ምን እንደሆነ አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፦

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ قَالُواْ رَبُّنَا ٱللَّهُ ثُمَّ ٱسۡتَقَٰمُواْ تَتَنَزَّلُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَلَّا تَخَافُواْ وَلَا تَحۡزَنُواْ وَأَبۡشِرُواْ بِٱلۡجَنَّةِ ٱلَّتِي كُنتُمۡ تُوعَدُونَ ٣٠ ﴾ فصلت: ٣٠.

"እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ <u>ከዚያም ቀጥ ያሉ አትፍሩ፤ አትዘኑም፤ በዚያችም ተሰፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ</u> በማለት በነሱ ላይ መላእክት ይወርዳሉ።"
[ፉሲለት፡ 30]

ይህ እንግዲህ ከተውሒድ ሽልማቶች ውስጥ አንዱ ነው። አላህ ደግሞ ብዙ ሽልማቶችን አምነው ቀጥ ብለው በዛው መንገድ ላይ ለሞቱ አስቀምጧል።

35. የተውሒድ አደራ!

ከአላህ በስተቀር ለማንም የማይቀረው ጥፍጥና ቆራጭ የሆነው ሞት በመጣ ጊዜ ወላጅ ለልጆቹ ምን ብሎ መምከር እንዳለበት አላህ የነብዩላህ ያዕቁብን ምሳሌ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ وَوَصَّىٰ بِهَآ إِبۡرَٰهِـۧمُ بَنِيهِ وَيَعۡقُوبُ يَٰبَنِيَّ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰ لَكُمُ ٱلدِّينَ فَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٣٢ ﴾

"በርሷም (በሐግጋቲቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ። ያዕቁብም (እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ) ። <u>ልጆቼ ሆይ! አላህ ለናንተ ሃይማኖትን መረጠ። ሰለዚህ እናንተ ሙሰሊሞች ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ</u> (አላቸው)።"

﴿ أَمۡ كُنتُمۡ شُهَدَآءَ إِذۡ حَضَرَ يَعۡقُوبَ ٱلۡمَوۡتُ إِذۡ قَالَ لِبَنِيهِ مَا تَعۡبُدُونَ مِنۢ بَعۡدِي قَالُواْ نَعۡبُدُ إِلَٰهَكَ وَإِلَٰهَ ءَابَآئِكَ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗا وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ ١٣٣ ﴾ البقرة: ١٣٢ – ١٣٣.

"ያዕቁብን ሞት በመጣበት ጊዜ ለልጆቹ <u>ከኔ በኋላ ማንን ትገዛላችሁ</u>? ባለ ጊዜ ቀራቢዎች ነበራችሁን? (እነርሱም) አምላክህንና የአባቶችህን የኢብራሂምን የኢስማዒልንና

የኢሰሐቅንም አምላክ አንድ የኾነውን አምላክ እኛ ለርሱ ፍፁም ታዛዦች ኾነን እናመልካለን አሉ።" [አል-በቀራህ፡ 132-133]

የጠቢቡ ሉቅማን አባታዊ ምክር!

መልካም የአላህ ባርያ በመባል የሚታወቁት ሉቅማን ለልጃቸው ብዙ ምክርን መክረውታል። ከምንም በፊት ምክራቸውን የጀመሩት ግን ልጃቸውን አላህ ዘንድ ከታላቁ የበደሎች ሁሉ ታላቅ በደል የሆነውን ሺርክ በማስጠንቀቅ ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَإِذۡ قَالَ لُقۡمَٰنُ لِٱبۡنِهِۦ وَهُوَ يَعِظُهُۥ يَٰبُنَيَّ لَا تُشۡرِكۡ بِٱللَّهِۖ إِنَّ ٱلشِّرۡكَ لَظُلۡمٌ عَظِيمٞ ١٣ ﴾ لقمان: ١٣.

"ሉቅማንም ለልጁ እርሱ የሚገሥጸው ሲኾን <u>ልጄ ሆይ! በአላህ (ጣዖትን) አታጋራ። ማጋራት ታላቅ በደል ነውና</u> ያለውን (አሰታውሰ)።" [አል ሉቅማን፡ 13]

እንግዲህ የአላህ ደግ ባርያ የሆኑት ሉቅማን ልጃቸውን ብዙ ነገሮች ነው የመከሩት። የምክሮቹን አይነት ለመመልከት የፈለገ ሱረቱ ሉቅማን ላይ ይመልከት። ግን በዋናነት ልብ ሊባል የሚገባው ከምንም በፊት ምክራቸውን የጀመሩት **"<u>ልጄ ሆይ! በአላህ (ጣዖትን) አታጋራ። ማጋራት ታላቅ በደል ነውና</u>" በማለት ነው።** ይሄ ለአእምሮ ባለቤቶች ትልቅ ትምህርት ይሰጣል። ምክንያቱም **<u>ከመዋዋብ በፊት መጀመርያ መፅዳት ይቀደማል</u>**። አንድ ሰው ሺርክን ተሸክሞ 1000 አመት ሰላት ቢሰግድ፣ የኡሁድ ተራራን የሚያክል ወርቅ በአላህ መንገድ ላይ ቢለግስ እና የመሳሰለውን አላህ አይቀበለውም። ምክንያቱም ቀደም ብለን እንዳየነው ሺርክ ስራዎችን ሁሉ ድምጥማጣቸውን ያጠፋልና (ዶግ አመድ ያደርገዋልና) ።

አላህ ዘንድ ሺርክ የታላቆች ሁሉ ታላቅ በደል መሆኑን የሚነግረንም የሚቀጥለው የነብዩ ﷺ ሐዲሥ ነው፡-

ታላቁ ሶሐባ ኢብኑ መስዑድ ረዲየላሁ ዐንሁ **"ከወንጀል ሁሉ በላጩ የትኛው ነው?"** ብለው ነብዩን ﷺ ሲጠይቋቸው **"<u>የፈጠረህ እሱ ሆኖ ሳለ ለአላህ ላይ ባላንጣ ማድረግህ ነው</u>"** አሉ። **"ይሄ በርግጥም ከባድ ነው!! ከዚያስ የትኛው ነው?"** በማለት ደግመው ሲጠይቋቸው **"<u>አንተ ጋር መብላቱን በመስጋት ልጅህን መግደልህ ነው</u>"** አሉ። ደገሙና **"ከዚያስ የትኛው ነው?"** ሲሉ **"<u>በጎረቤትህ ሚስት ላይ ዝሙት መፈፀምህ ነው</u>"** አሉት። [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል]

36. ፍፃሜህ በተውሒድ ላይ ይሁን!!

ጌታችን አላህ ሙስሊሞች ሆነን ኖረን ሙስሊሞች ሆነን እንድንሞት አዞናል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل عمران: ١٠٢.

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት። <u>እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ</u>።" [አሊ-ኢምራን፡ 102]

ስንት መከራ የደረሰባቸው **<u>ነብይ</u>** **<u>የነብይ ልጅ</u>** **የኢብራሒም ዘር** የሆኑት ዩሱፍ (ዐለይሂ ሰላም) እንዲህ ይላሉ፡-

﴿ رَبِّ قَدۡ ءَاتَيۡتَنِي مِنَ ٱلۡمُلۡكِ وَعَلَّمۡتَنِي مِن تَأۡوِيلِ ٱلۡأَحَادِيثِۚ فَاطِرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ أَنتَ وَلِيِّۦ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ تَوَفَّنِي مُسۡلِمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّٰلِحِينَ ١٠١ ﴾ يوسف: ١٠١.

"ጌታዬ ሆይ! ከንግሥና በእርግጥ ሰጠኸኝ። ከሕልምችም ፍች አሰተማርከኝ። የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ። <u>ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ</u>። <u>በመልካሞቹም አሰጠጋኝ (አለ)።"</u> [ዩሱፍ፡ 101]

37. የእምነት ጥያቄና መልሶች

የተለያዩ ኡለማዎች የተውሒድን ፅንሰ ሀሳብ ለሙስሊሙ ለማስጨበጥ በጥያቄና መልስ ያስተምራሉ። ከነዚህም መካከል ታላቁ አሊም ሸይኽ ሙሐመድ አብድልወሃብ (ረሂመሁላህ) የእምነት መሰረቶች ለአጠቃላይ ሙስሊም ማህበረሰብ በሚል እንደሚከተለው አዘጋጅተዋል።

تلقين أصول العقيدة العامة

የእምነት መሰረቶችን ለአጠቃላይ ሙስሊም ማህበረሰብ ማስገንዘብ

بسم الله الرحمن الرحيم

እጅግ በጣም ርህሩህ እና እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም እጀምራለሁ።

إذا قيل لك: من ربك؟

ጌታህ ማን ነው? ከተባልክ

فقل: ربي الله

"ጌታዬ አላህ ነው" በል።

فإذا قيل لك: ما معنى الرب؟

"ጌታ ማለት ምን ማለት ነው?" ከተባልክ

فقل: المعبود المالك المتصرف.

“የሚመለከ (ተመላኪ)፤ የሁሉ ነገር ባለቤትና አስተናባሪ ማለት ነው” በል።

فإذا قيل لك: ما أكبر ما ترى من مخلوقاته؟

“ከምታያቸው የአላህ ፍጡራን ውስጥ ትልቁ ምንድን ነው?” ከተባልክ

فقل: السموات والأرض.

“ሰማያት እና ምድር ናቸው” በል።

فإذا قيل لك: بماذا تعرف ربك؟

“ጌታህን በምንድን ነው የምታውቀው?” ከተባልክ።

فقل: أعرفه بآياته ومخلوقاته.

“በፍጡራኖቹ እና በተአምራቶቹ (በምልክቶች) አውቀዋለሁ” በል።

وإذا قيل لك: ما أعظم ما ترى من آياته؟

“ከምታያቸው ተአምራቶቹ (ምልክቶቹ) ትልቁ ምንድን ነው?” ከተባልክ

فقل: الليل والنهار،

“ለሊት እና ቀን ናቸው” በል።

والدليل على ذلك قوله تعالى:

የዚህም ማስረጃ የላቀ ከፍ ያለው የአላህ ቃል ነው፡-

﴿إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٥٤﴾﴾ الأعراف: ٥٤

"ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው። ከዚያም ከአርሽ በላይ ሆነ። (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲ ኾን ይሸፍናል። ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲ ኾኑ (ፈጠራቸው)። ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው። የዓለማት ጌታ አላህ (ከብሩ) ላቀ።"

فإذا قيل لك: ما معنى الله؟

"አላህ የሚለው ቃል ፍቺው ምንድን ነው?" ከተባልክ

فقل: معناه ذو الألوهية والعبودية على خلقه أجمعين.

"የአምላክነት ባለቤት እና ከፍጡራኑ ዘንድ የተመላኪነት ባለቤት የሆነው ነው" በል።

فإذا قيل لك: لأي شيء الله خلقك؟

"አላህ ለምንድን አላማ ነው የፈጠረህ?" ከተባልክ።

فقل: لعبادته.

"እሱን ለማምለክ (ለመገዛት) ነው" በል።

فإذا قيل لك: أي شيء عبادته؟

"እሱን ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው?" ብትባል

فقل: توحيده وطاعته.

“እሱን በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ እና እሱን መታዘዙ ነው” በል።

فإذا قيل لك: ما هو الدليل على ذلك؟

በዚህ ላይ ማስረጃው ምንድን ነው? ከተባልክ።

فقل: قوله تعالى ﴿ وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦ ﴾ الذاريات: ٥٦

“ሰውንም ሆነ ኢጋንንትን እኔን በብቸኝነት ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም” የሚለው የላቀው የአላህ ቃል ነው በል።

وإذا قيل لك: أي شيء أول ما فرض الله عليك؟

የመጀመሪያ አላህ ባንተ ላይ ግዴታ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? ብትባል።

فقل: كفر بالطاغوت وإيمان بالله،

በጣዖት መካድ እና በአላህ ማመን ነው በል።

والدليل على ذلك قوله تعالى

ለዚህም ማስረጃው ከፍ ያለው የላቀው አላህ ቃል ነው።

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ٢٥٦ ﴾ البقرة: ٢٥٦.

“በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ። <u>በጣዖትም የሚክድና</u> <u>በአላህ የሚያምን</u> ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።”

فإذا قيل: ما هو العروة الوثقى؟

ጠንካራዋ ዘለበታማ ገመድ ማለት ምን ማለት ናት? ብትባል።

فقل: لا إله إلا الله.

ላኢላሃ ኢለላህ (ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ የለም) (የተውሒድ ቃል) ናት በል።

ومعنى "لا إله" نفي و " إلا الله " إثبات.

“ላኢላሃ” የሚለው ትርጉም በእውነት አምልኮ የሚገባው እንደሌለ፤

“ኢለላህ” የሚለው ቃል ደግሞ እውነተኛ አምልኮ ለአላህ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጥ ነው።

فإذا قيل لك: ما هو أنت نافي، وما هو أنت مثبت؟

አንተ ውድቅ የምታደርገው ምንድን ነው? የምታረጋግጠውስ ምንድን ነው? ብትባል።

فقل: نافي جميع ما يعبد من دون الله، ومثبت العبادة لله وحده لا شريك له.

ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ነገሮችን ባጠቃላይ ውድቅ አደርጋለሁ። አጋር ለሌለው እና ብቸኛ ለሆነው አላህ አምልኮን አፀድቃለሁ።

فإذا قيل لك: مالدليل على ذلك؟

በዚህ ላይ ማስረጃው ምንድን ነው? ብትባል።

فقل: قوله تعالى: ﴿ وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوْمِهِۦٓ إِنَّنِى بَرَآءٌ مِّمَّا تَعْبُدُونَ ﴿٢٦﴾ ﴾ الزخرف: ٢٦.

ከፍ ያለው የአላህ ቃል ነው በል፡- ***"(ሙሐመድሆይ!) ኢብራሂም ለአባቱ እና ለህዝቦቹ ያለውን አውሳላቸው፤ <u>እኔ እኮ ከምታመልኩት ነገር ሁሉ የጠራሁኝ ነኝ።</u>"***

هذا دليل النفي،

ይሄ ውድቅ የማድረግ ማስረጃ ነው።

ودليل الإثبات ﴿إِلَّا ٱلَّذِى فَطَرَنِى ﴿٢٧﴾﴾ الزخرف: ٢٧.

(አምልኮን ለአላህ ብቻ) የማፅደቅ ማስረጃው፡- ***"<u>ያ የፈጠረኝ ጌታ ሲቀር</u> (ብቸኛው ፈጣሪ ብቸኛው ተመላኪ ነው)"***

فإذا قيل لك: ما هو الفرق بين توحيد الربوبية وتوحيد الألوهية؟

(አላህን) በጌትነቱ ብቸኛ ማድረግ እና በአምላክነቱ ብቸኛ ማድረግ ልዩነቱ ምንድን ነው? ብትባል

فقل: توحيد الربوبية إفراد الله بأفعاله، مثل الخلق والرزق، والإحياء، والإماتة، وإنزال المطر وإنبات النبات، وتدبير الأمور ...

(አላህን) በጌትነቱ ብቸኛ ማድረግ ማለት ጌታችን በሚሰራቸው ስራዎች ብቸኛ ማድረግ ነው። ለምሳሌ መፍጠር፤ ሲሳይ መስጠትን፤ ህያው ማድረግን፤ መግደልን፤ ዝናብ ማውረድን፤ ቡቃያ ማብቀልን፤ በጥቅሉ ነገራቶችን ማስተናበርን

وتوحيد الإلهية إفراد الله تعالى بأفعال العباد، مثل الدعاء والخوف والرجاء والتوكل والإنابة والرغبة والرهبة والنذر والاستغاثة، وغير ذلك من أنواع العبادة.

አላህን በአምላክነት ብቸኛ ማድረግ ማለት አንተ የአላህ ባርያ ሆይ! አምልኮህን በጠቅላላ ለአንድ አላህ ብቻ ማድረግ ነው። ለምሳሌ ፀሎት (ዱዓ)፣ ፍራቻ፣ ክጃሎት፣ መመካት፣

በንስሃ መመለስ፣ ተስፋ ማድረግ፣ ስጋት፤ ስለት፣ የጭንቅ ግዜ ፀሎት (ረድኤት)፣ እና የመሳሰሉትን የአምልኮ ክፍሎች።

فإذا قيل لك ما دينك؟

እምነትህ (ሃይማኖትህ) ምንድን ነው? ከተባልክ።

فقل: ديني الإسلام، وأصله وقاعدته أمران :

እምነቴ (ሃይማኖቴ) እስልምና ነው በል። የእስልምና መሰረቱ እና መርሆዎቹ 2 ናቸው።

الأول: الأمر بعبادة الله وحده لا شريك له، والتحريض على ذلك، والموالاة فيه، وتكفير من تركه،

የመጀመርያው ተጋሪ የሌለው እና ብቸኛ የሆነውን አላህ በማምለክ (ጉዳይ ላይ) ማዘዝ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ማነሳሳትና መቀስቀስ ፣ በሱም ላይ መሰረት አድርጎ መዋደድ ነው። ይህንን እውነታ (ተውሒድን) የተወን ሰው ከሃዲነቱን ማረጋገጥ።

والإنذار عن الشرك في عبادة الله، والتغليظ في ذلك، والمعاداة فيه، وتكفير من فعله .

(ሁለተኛ) በአላህ አምልኮ ላይ ከማጋራት ማስጠንቀቅ፣ ጉዳዩ ከባድ መሆኑን አክብዶ መግለፅ፣ በሱም ጠላት አድርጎ መያዝ፣ የፈፀመውን ሰው ከሃዲነቱን ማረጋገጥ።

وهو مبني على خمسة أركان :

እሱም (እስልምና) በአምስት መዓዘናት የተገነባ ነው።

شهادة أن لا إله إلا الله، وأن محمدا رسول الله، وإقام الصلاة، وإيتاء الزكاة، وصوم رمضان، وحج البيت مع الاستطاعة.

(የእስልምና ማዕዘናት የሚከተሉት ናቸው) ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ እንደሌለ መመስከር እና ሙሃመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ማቋቋም፤ ዘካን መክፈል፣ የረመዳንን ወር መፆም፣ ከአቅም ጋር ሃጅን መፈፀም ናቸው።

ودليل الشهادة قوله تعالى: شَهِدَ ٱللَّهُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَأُوْلُواْ ٱلْعِلْمِ قَآئِمَۢا بِٱلْقِسْطِ ۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ

የሁለቱ የምስክርነት ቃል ማስረጃ የላቀው የአላህ ቃል ነው

አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲ ኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ) ። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።

ودليل أن محمدا رسول الله قوله تعالى: مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ

ሙሐመድ ﷺ የአላህ መልክተኛ መሆናቸው ማስረጃው

ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው።

والدليل على إخلاص العبادة والصلاة والزكاة قوله تعالى:

وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعْبُدُواْ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤْتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ ۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلْقَيِّمَةِ

የበጎ ስራ፤ የስግደት፤ የዘካ ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡-

"አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።"

ودليل الصوم قوله تعالى:

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ

تَتَّقُونَ

የፆም ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡-

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነገ) ልትጠነቀቁ ይከጅላልና።"

ودليل الحج قوله تعالى: وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلۡبَيۡتِ مَنِ ٱسۡتَطَاعَ إِلَيۡهِ سَبِيلٗاۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ

የሀጅ ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡- ***"ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።"***

وأصول الإيمان ستة: أن تؤمن بالله وملائكته وكتبه ورسله وباليوم الآخر وبالقدر خيره وشره.

የእምነት መሰረቶች (ምሶሶዎች) 6 ናቸው።

በአላህ፤ በመላእክቶቹ፤ በመፀሃፍቱ፤ በመልክተኞቹ፤ በመጨረሻዋ ቀን፤ ጥሩንም መጥፎንም አላህ ነው የወሰነው ብሎ ማመን ነው።

والإحسان أن تعبد الله كأنك تراه، فإن لم تكن تراه فإنه يراك.

በአምልኮ ላይ ማሳመር ማለት፤ አላህን ልክ እንደምታየው አድርገህ መገዛት፤ የምታየው ባትሆን እሱ ያይሃል።

فإذا قيل: من نبيك؟

ነብይህ ማን ነው? ከተባልክ

فقل: محمد بن عبد الله بن عبد المطلب بن هاشم، وهاشم من قريش وقريش من العرب والعرب من ذرية إسماعيل ابن إبراهيم الخليل على نبينا وعليه أفضل الصلاة والسلام .

ሙሐመድ ኢብን አብደላህ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ ኢብን ሀሺም፣ ሀሺም ከቁረይሾች ነው። ቁረይሾች ከአረቦች ናቸው። አረቦች የኢስማኢል ዝርያዎች ናቸው። ኢስማኢል ደግሞ አላህ ፍፁም አድርጎ የያዘው የኢብራሂም ልጅ ነው፣ በነብያችን እና አላህ ፍፁም ወዳጅ አድርጎ በያዛቸው ኢብራሂም ላይ በላጭ የሆነ ሰላት እና ሰላም ይውረድ።

بلده مكة،

የትውልድ አገራቸው መካ ናት፤

وهاجر إلى المدينة .

ወደ መዲና ተሰደዱ፤

وعمره ثلاث وستون سنة :

እድሜያቸው 63 ነው።

منها أربعون قبل النبوة،

40ው ከነብይነት በፊት፤

وثلاث وعشرون نبيا رسولا .

ሃያ ሶስቱን ነብይ እና መልክተኛ ሆነው፤ ጨረሱ

نُبئ باقرأ،

“አንብብ” በሚለው (በኢቅራ) ነብይ ሆኑ፤

وأرسل بالمدثر.

በሙደሲር መልክተኛ ሆኑ፤

فإذا قيل: هل مات أو ما مات؟

ሞተዋል ወይንስ አልሞቱም? ተብለህ ከተጠየቅክ፤

فقل: مات،

ሞተዋል በል።

والدليل قوله تعالى: ﴿ إِنَّكَ مَيِّتٌ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ ﴿٣٠﴾ ثُمَّ إِنَّكُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ عِندَ رَبِّكُمْ تَخْتَصِمُونَ ﴿٣١﴾ ﴾ الزمر: ٣٠ - ٣١.

ለዚህም ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡- ***“(ሙሐመድ ሆይ! ﷺ) <u>አንተ ሟች ነህ</u>፤ እነሱም (ካሃዲያን) ሟቾች ናቸው።”***

ودينه ما مات (ولن يموت) إلى يوم القيامة،

እሳቸው ይዘውት የመጡት (የነብያት ሁሉ ሃይማኖት ኢስላም) አልሞተም፤ እስከ ትንሳኤ ድረስም ወደፊትም አይሞትም

وهل الناس إذا ماتوا يبعثون؟

ሰዎች በሞቱ ጊዜ ይቀሰቀሳሉን?

فقل: نعم،

አዎን በል።

والدليل قوله تعالى: ﴿ مِنۡهَا خَلَقۡنَٰكُمۡ وَفِيهَا نُعِيدُكُمۡ وَمِنۡهَا نُخۡرِجُكُمۡ تَارَةً أُخۡرَىٰ ٥٥ ﴾ طه: ٥٥.

ለዚህም ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡- ***"ከእርሷ ከአፈር ፈጠርናችሁ፤ ወደ አፈርም እንመልሳችኋለን፣ በሌላም ጊዜ ከሷም እናወጣችኋለን።"***

والذي ينكر البعث كافر،

ከሞት በኋላ መቀስቀስን የሚያስተባብል ሰው ካፊር ነው።

والدليل قوله تعالى: ﴿ زَعَمَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَن لَّن يُبۡعَثُواْۚ قُلۡ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبۡعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلۡتُمۡۚ وَذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ٧ ﴾ التغابن: ٧.

ለዚህም ማስረጃው የላቀው አላህ ቃል ነው፡- ***"እነዚያ የካዱትን በፍጹም የማይቀሰሱ መኾናቸውን አሰቡ። አይደለም በጌታዬ እምላለሁ። በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ። ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ። ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው። በላቸው።"***

38. ተውሒድን ለልጆች ማስተማር

የተውሒድ አንገብጋቢነት፣ አስፈላጊነት በጥያቄ እና መልስ

السلام عليكم و رحمة الله

አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላህ (የአላህ ሰላም እና እዝነቱ ባንተ ላይ ይሁን)

የተውሒድ አንገብጋቢነት

ልጆቻችሁን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በየእለቱ በመደጋገም ተውሒድን አስተምሩዋቸው። የእምነት መሰረቶችን አለማወቅና ከልጅነት ጀምሮ ልጆች ላይ አለመትከል አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ እየተንሰራፋ ላለው አፈንጋጭነት አንዱ መንስኤ ነው።

ተውሒድን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

س1/ من أين نأخذ عقيدتنا ؟

ጥ. 1፡- እምነታችንን ከምንድን ነው የምንወስደው?

من القرآن والسنة.

ከቁርአን እና ከነብዩ (ﷺ) ሱና። ይህ ሲባል ቁርአን እና ሐዲሥን መልካም ቀደምቶች በተረዱት አረዳድ መሆን ግድ ይላል።

س2/ أين الله ؟

ጥ. 2፡- አላህ የት ነው?

في السماء على العرش.

ሰማይ ላይ ከአርሽ በላይ ነው።

س3/ ما الدليل من القرآن على أن الله على العرش ؟

ጥ. 3፡- አላህ ከአርሽ በላይ ለመሆኑ ማስረጃው ከቁርአን ምንድን ነው?

{ الرحمن على العرش استوى} .

አዛኙ ጌታ ከአርሹ በላይ ከፍ አለ።

س4/ ما معنى (استوى) ؟

ጥ. 4፡- ኢስተዋእ የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

علا وارتفع.

ከፍ አለ፣ የበላይ ሆነ።[15]

س5/ لماذا خلق الله الجن والإنس ؟

ጥ. 5፡- አላህ ጅንንና ሰውን ለምንድን ነው የፈጠራቸው?

لعبادته وحده لاشريك له.

ያለ አጋሪ እሱን ብቻ ለመገዛት (ለማምለክ)።

س6/ ما الدليل من القرآن على أن الله خلق الجن والإنس لعبادته ؟

ጥ. 6፡- አላህ ጂኖችን እና የሰው ልጆችን የፈጠራቸው እሱን ለመገዛት ለመሆኑ ከቁርአን ምንድን ነው ማስረጃው?

وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ

"ጂንንና ሰውንም ሊ ግገዙኝ (ሊያመልኩኝ) እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።"

س7/ ما معنى (يعبدون) ؟

ጥ. 7፡- "ሊያመልኩኝ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

يوحدون.

አንድ አድርገው ሊያመልኩኝ።

س8/ ما معنى لا إله إلا الله ؟

ጥ. 8፡- የላኢላሃ ኢለሏህ ትርጉም ምንድን ነው?

لا معبود بحق إلا الله.

ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚመለክ አምላክ የለም።

س9/ ما أعظم عبادة ؟

ጥ. 9፡- ከአምልኮ ሁሉ ታላቁ የትኛው ነው?

---

[15] ሰለፎቹ በዚህ ተርጉመውታል። ከነሱም ውስጥ አቡል አልያ እና ሌሎችም። የአቡል አልያን ኢማሙ ቡኻሪ ሰሂሃቸው ላይ ዘግበውላቸዋል።

التوحيد.

ተውሒድ (አላህን በብቸኝነት በአምልኮ መነጠል) ።

س10/ ما أعظم معصية ؟

ጥ. 10፡- ታላቁ ሀጢያት ምንድን ነው?

الشرك.

በአላህ ላይ ማጋራት ነው። (ለአላህ ብቻ የሚገባውን አምልኮ ለሌሎች ለማንም ይሁን ለምንም አሳልፎ መስጠት) ።

س11/ ماهو التوحيد ؟

ጥ. 11፡- ተውሒድ ማለት ምን ማለት ነው?

إفراد الله بالعبادة.

አላህን በአምልኮ ብቸኛ አድርጎ መነጠል።

س12/ ماهو الشرك ؟

ጥ. 12፡- ሺርክ ማለት ምን ማለት ነው?

عبادة غير الله مع الله.

ከአላህ ውጭ ያለን አካል (ማንም ይሁን ምን) ከአላህ ጋር አብሮ ማምለክ።

س13/ كم أقسام التوحيد ؟

ጥ. 13፡- የተውሒድ ክፍሎች ስንት ናቸው?

ثلاثة.

ሶስት ናቸው።

س14/ ما هي أقسام التوحيد ؟

ጥ. 14፡- የተውሒድ ክፍሎች እነማን ናቸው?

الربوبية، والألوهية، والأسماء والصفات.

- የጌትነት ተውሒድ

- የአምላክነት ተውሒድ

- የመልካም ስሞችና (የላቁ) መገለጫዎች ተውሒድ ናቸው።

س15/ ما تعريف توحيد الربوبية ؟

ጥ. 15፡- የጌትነት ተውሒድ ማለት ምን ማለት ነው?

افراد الله في أفعاله مثل الخلق والرزق.

አላህን በተግባራቱ መነጠል፤ ለምሳሌ መፍጠሩና ሲሳይን መለገሱ።

س16/ ما تعريف توحيد الألوهية ؟

ጥ. 16፡- የአምላክነት ተውሒድ ማለት ምን ማለት ነው?

إفراد الله بأفعال العباد مثل الدعاء، والذبح، والسجود.

አላህን በባሮች ተግባር መነጠል፤ ለምሳሌ ዱዓ፣ እርድ፣ ስግደት።

س17/ هل لله أسماء وصفات ؟

ጥ. 17፡- ለአላህ ስም እና መገለጫዎች አሉትን?

نعم.

አዎን።

س18/ من أين نأخذ أسماء الله وصفاته ؟

ጥ. 18፡- የአላህን ስም እና መገለጫዎች ከየት ነው የምንይዘው (የምንወስደው)?

من القرآن والسنة.

ከቁርአን እና ከሱና

س19/ هل تشبه صفات الله صفاتنا ؟

ጥ. 19፡- የአላህ መገለጫዎች የእኛን (የፍጡራኑን) መገለጫዎች ይመስላሉን?

لا.

በፍፁም አይመስሉም።

س20/ ما الدليل من القرآن على أن صفات الله لا تشبه صفاتنا ؟

ጥ. 20፡- የአላህ መገለጫዎች የእኛን መገለጫዎች ላለመምሰላቸው ከቁርኣን ማስረጃው ምንድን ነው?

لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ

"(አላህን) የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።"

س21/ القرآن كلام من ؟

ጥ. 21፡- ቁርኣን የማን ንግግር ነው?

الله.

የአላህ።

س22/ منزل أم مخلوق ؟

ጥ. 22፡- ከአላህ ዘንድ የወረደ ነው ወይንስ ፍጡር ነው?

منزل و هو كلامه حقيقة بحرف و صوت.

ከሱ (ከአላህ) የተወረደ ነው። በፊደልም በድምፅም በእርግጥ የአላህ ቃል ነው።

س23/ ما هو البعث ؟

ጥ. 23፡- መቀስቀስ (ትንሳኤ) ማለት ምን ማለት ነው?

إحياء الناس بعد موتهم.

ሰዎች ከሞቱ በኋላ ህያው መሆናቸው ነው።

س24/ ما الدليل من القرآن على كفر من أنكر البعث ؟

ጥ. 24፡- ከሞት መቀስቀስን የካደ ሰው ከሃዲ (ካፊር) ለመሆኑ ከቁርኣን ማስረጃው የቱ ምንድን ነው?

﴿زَعَمَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَن لَّن يُبۡعَثُواْ﴾.

"እነዚያ ከሃዲያን እንቀሰቀስም ብለው ሞገቱ።"

س25/ ما الدليل من القرآن على أن الله سيبعثنا ؟

ጥ. 25፡- አላህ እኛን እንደሚቀሰቅሰን ከቁርኣን ማስረጃው ምንድን ነው?

﴿قُلۡ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبۡعَثُنَّ﴾.

በላቸው፡ እንዴታ በጌታዬ ይሁንብኝ ትቀሰቀሳላችሁ።

س26/ كم أركان الإسلام ؟

ጥ. 26፡- የእስልምና ማዕዘናት ስንት ናቸው?

خمسة.

አምስት ናቸው።

س27/كم أركان الإيمان ؟

ጥ. 27፡- የእምነት ማእዘናት ስንት ናቸው?

ستة.

ስድስት።

س28/كم أركان الإحسان ؟

ጥ. 28፡- የኢሕሳን ማእዘናት ስንት ናቸው?

واحد.

አንድ ነው።

س29/ ماتعريف الإسلام ؟

ጥ. 29፡- ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?

الاستسلام لله بالتوحيد والانقياد له بالطاعة والبراءة من الشرك وأهله.

ለአላህ በተውሒድ ሙሉ ታዛዥ መሆን፣ ለእርሱ ትዕዛዝን በማከበር መጓዝ፣ ከሺርክ እና ከሺርክ ባላቤቶች መጥራት ነው።

س30/ ما تعريف الإيمان ؟

ጥ. 30፡- እምነት ማለት ምን ማለት ነው?

قول باللسان واعتقاد بالقلب وعمل بالجوارح يزيد بالطاعة وينقص بالمعصية.

በምላስ የሚነገር፣ በቀልብ የሚቋጠር፣ በአካላት የሚተገበር ሲሆን፣ ትእዛዛትን በመፈፀም የሚጨምር፣ አመፅን በመፈፀም የሚቀንስ ነው።

س31/ لمن نذبح ونسجد ؟

ጥ. 31፡- ለማን ነው የምናርደው? ለማንስ ነው የምንሰግደው?

لله وحده لاشريك له.

አጋር ለሌለው ለአላህ ብቻ ነው።

س32/ هل يجوز الذبح والسجود لغير الله ؟

ጥ. 32፡- ከአላህ ውጭ ላለ አካል ማረድ እና መስገድ ይቻላልን?

لا.

በፍፁም አይገባም።

س33/ ماحكم الذبح والسجود لغير الله ؟

ጥ. 33፡- ከአላህ ውጭ ላለ አካል ማረድ እና ሱጁድ (ስግደት) መፈፀም ብይኑ ምንድን ነው?

شرك أكبر.

ታላቁ ማጋራት ነው።

39. ማጠቃለያ

ይህችን ከቁርኣን ከሐዲሥና ከተለያዩ የተውሒድ ምንጮች እና መፀሀፎች የተቀዳች አጭር ማስታወሻ በዚሁ ፈፅሚያለሁ። የአላህ ባርያዎች ሆይ! በቅድሚያ እራሴን በማስከተልም እናንተን አላህን በመፍራት ላይ አስታውሳለሁ። በሁለት አገር ለስኬት የሚያበቃው ተውሒድ እና ሱና ነው። ሁለት አገር የሚያዋርደው ደግሞ ሺርክ እና ቢድዐ ነው። ኡመተል ኢስላም ከገባበት መከራ መውጣት ከፈለገ የሁለት አገር የስኬት ቁልፍ

የሆነውን ተውሒድ ማወቅ፣ መተግበር፣ ለሌሎች ማስተላለፍ ግድ ይለዋል። አላህ እውቀት የሰጣቸው፣ ወደ አላህ መንገድ እንጣራለን የሚሉ ሁሉ ሃቅን ሳይደብቁ ሃላፊነታቸውን ባግባቡ ሊወጡ ይገባል። የእውቀት ባለቤቶች በእውቀታቸው ሲሰሩበት ታላቅ ደረጃ እንደሚያገኙት ሁሉ፣ ልክ እንደ የሁዳዎች ሃቅን አውቀው ቢደብቁ ብሎም ለየትኛውም አላፊ ጥቅም ሲሉ ሃቁን እና ጥመቱን ቢደበላልቁ አላህ ልክ እንደ አይሁዶች እውቀትን የደበቀ ሁሉ አይቀጡ ቅጣት እንደቀጣው ሳይቀጣቸው አይቀርም።

ሴቶች ሆይ! እናንተ የልጆቻችሁ ታላቅ አስተማሪ ናችሁና እናንተ ከምንም በፊት ተውሒድን ተማሩ። ምንም የሌለው ምንም መስጠት አይችልም እንደሚባለው፣ አንቺ የተከበርሽ እህቴ ሆይ! ተውሒድን ካላወቅሽ ለልጆችሽ ምንም መስጠት አትችይም። ሴቶች ሆይ! ልጆቻችሁን በልጅነታቸው ተውሒድ አስተምሩ። ወጣቶች ሆይ! ከምንም እውቀት በፊት የተውሒድ እውቀት ይቀደማልና ቅድሚያ ስጡት።

ባለሀብቶች ሆይ! ገንዘባችሁን በሃይማኖት ስም ለማይረባ ነገር ለሚጠይቋችሁ ሰዎች አትስጡ። ይልቁንስ አላህ የሰጣችሁን ገንዘብ የተውሒድ ትምህርቶችን አስፋፉበት። ይህ ሲሆን ገንዘባችሁም በጣም ፍሬያማ ይሆናል። የተውሒድ ጥሪና ተጣሪዎቿንም በገንዘባችሁ ደግፉ። ታላቁ የተውሒድ አስተማሪ፣ አላህ ፍፁም ወዳጅ አድርጎ የያዛቸው፣ የነብያት ሁሉ አባት ኢብራሂም (አለይሂ ሰላም) ከልጃቸው ኢስማኢል (አለይሂ ሰላም) ጋር ካዕባን እየገነቡ ያደረጉትን የሚከተለውን ዱዓ እኔም የሳቸውን ፈለግ በመከተል እንዲህ ስል እደግመዋለሁ።

﴿رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧﴾ البقرة: ١٢٧.

“ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል። አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና።”

ነፍሴንም እናንተንም እስከ ህይወት ፍፃሜ ድረስ አደራ በተውሒድ፣ አደራ በሱና፣ አደራ የመልካም ቀደምቶቻችንን መንገድ አጥበቆ በመያዝ እላለሁ። **<u>አላህ ሆይ! መጨረሻችን አሳምርልን።</u>**

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላም በነብያት ሁሉ መደምደሚያ በሙሐመድ፣ በቤተሰባቸው፣ በባልደረባዎቻው እና ሃቅን በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን።